ያልታተሙ የሰበር ውሳኔዎች በአንድ ተሰብስበው የተዘጋጁ

ቅፅ - 6

በዳንኤል ፍቃዱ (ጠበቃና የህግ አማካሪ)

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

ሰመ/ቁ፡-210020

ቀን፡-08/03/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ሮ ትዕግስት ታደሰ- ቀረቡ

ተጠሪ፡- ፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የከባድ አካል ጉዳት ማድረስ የወንጀል ክስን የሚመለከት ነው፡፡የሰበር አቤቱታ የቀረበው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው ፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት መፅናቱ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይህ ውሳኔ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ስላመለከቱ ነው፡፡

ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የወንጀል ህግ አንቀፅ 555(ለ) ን በመጥቀስ ባቀረበው ክስ በክሱ ላይ በተመለከተው ጊዜና ቦታ የግል ተበዳይ አስቴር ደገፉን በቦክስ ሰንዝራ ፊቷ ላይ በመምታት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የላይኛው የፊት ለፊት በቀኝ በኩል ያለው አንድ ጥርስ እና የፊት ለፊት በግራ በኩል ያለው ጥርሶቿ በከፍተኛ ደረጃ እንዲነቃነቁ አድርጋለች በዚህም ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ፈፅማለች በማለት ከሷል፡፡

ተከሳሽ ክሱ ተነቦላት እንድትረዳው ከተደረገ በኋላ መቃወሚያ የለኝም ድርጊቱን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዳ ስለተከራከረች የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው የተሰሙ ሲሆን 1ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር በክሱ ላይ በተመለከተው ጊዜና ቦታ ከአመልካች በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት አመልካች በቦክስ አፏን በመምታት አፏ እንዲደማና የላይኛው በቀኝ እና በግራ በኩል ያሉት ሁለት ጥርሶቿ እንደተነቃነቁ ስላስረዳች 2ኛ እና 3ኛ ምስክሮች አመልካችና የግል ተበዳይ ተጣልተው ያገላገሏቸው መሆኑን በወቅቱ የግል ተበዳይ አፍ ይደማ የነበረ መሆኑን ስላስረዱ ይህንን የምስክርነት ቃል ከህክምና የምስክር ወረቀቱ ጋር በመመርመር አመልካች እንዲከላከሉ ብይን ቢሰጥም አመልካች የመከላከያ ማስረጃ የሌላቸው መሆኑን ስለገለፁ በቀረበባቸው ክስ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቶ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከግምት ውስጥ በማስገባት አመልካች በሁለት አመት ከስድስት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ያፀናው ሲሆን ቅጣትን በተመለከተ በአመልካች የቀረቡት ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች አላግባብ በስር ፍርድ ቤት ውድቅ መደረጋቸውን በመጥቀስ እነዚህን የቅጣት ማቅለያ ምክንያች ከግምት ውስጥ በማስገባት የስር ፍርድ ቤትን የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል አመልካች በሁለት አመት ቀላል እስራት እንድትቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ባቀረበቸው የሰበር አቤቱታም በወ/ህ/ቁ.555(ለ) አንድ ሰው ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው የሌላውን ሰው አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብልቶች አንዱን ያጎደለ፣እንዳያገለግሉት ያደረገ ወይም በሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ መልኩን ያበላሸ ሲሆን በግል ተበዳይ ላይ ደረሰ የተባለው ጉዳት የጥርስ መነቃነቅ በመሆኑ የአካል ጉዳት ተደርጎ የሚወሰድ ባለመሆኑ ፣የግል ተበዳይም ችሎት ቀርባ የተነቃነቀው ጥርስ የዳነ መሆኑን የገለፀች በመሆኑ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባው በወ/ህ/አ.556(1) ስር ሆኖ ቅጣቱም በዚሁ አግባብ ሊወሰን ሲገባ የስር ፍርድ ቤት በወ/ህ/አ.555(ለ) ስር የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ውሳኔ ይሻርልኝ፣የእስራ ቅጣቱ እንዲገደብላት ጠይቃ ፍርድ ቤቱ ውድቅ ማድረጉ አላግባብ ስለሆነ ውሳኔው ይሻርልኝ በማለት አመልክታለች፡፡

በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው ጉዳት የጥርስ መነቃነቅ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ በተመለከተበት በከባድ የአካል ጉዳት አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበትን አግባብ ከወ/ህ/አ.23(2) እና 555(ለ) አንፃር ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ለተጠሪ መጥሪያ ደርሶት መልሱን አቅርቧል፡፡

ተጠሪ በዚህ መልሱም በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ደረጃ የጥርስ መነቃነቅ በመሆኑና እነዚህ ጥርሶችም በሽቦ ታስረው ወደ ቦታው መመለስ ስለማይችሉ ተነቅለው በሰው ጥርስ መተካት ያለባቸው ስለመሆኑ በህክምና ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ በመጥቀስ የሰጠው ውሳኔ ሊፀና ይገባል፣ገደብን አስመልክቶም የስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የተወሰነው የእስራት ቅጣት ቢገደብ አመልካች ወንጀል ከማድረግ የሚታገዱ አለመሆኑን ስለፀባያቸው መሻሻልም አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ በቂ መሆኑን ባለማመኑ የተነሳ የገደብ ጥያቄውን ውድቅ ያደረገው በህጉ አግባብ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካቾች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች ከተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ አንፃር የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት ከመነሻውም የጥርስ መነቃነቅ አካል ጉዳት አለመሆኑን፣የግል ተበዳይ ጥርስ የዳነ መሆኑን የግል ተበዳይ የገለፁ በመሆኑ የደረሰ የአካል ጉዳት ባለመኖሩ በወ/ህ/አ.555(ለ) ስር ጥፋተኛ ልባል አይገባም በማለት ነው፡፡በመሰረቱ የሌላን ሰው አካል ማጉደል ወይም እንደያገለግሉት ማድረግ ታስቦ በሚፈፀም ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ጥፋተኛ ለማለት በቂ መሆኑን የወ/ህ/አ.555(ለ) በግልፅ ያመለክታል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካች በቦክስ በመምታት እንዲነቃነቁ ካደረጓቸው የግል ተባዳይ ጥርሶች መሃል የቀኝ መንጋጋ የፊት ለፊት የቀኝ በኩል አንድ ጥርስ በከፍተኛ ሁኔታ መነቃነቁን በግራ በኩል ያሉት ጥርሶች ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ የሚነቃነቁ መሆኑን፣ጥርሶቹ በሽቦ ታስረው ወደ ቦታቸው ሊመለሱ ስለማይችሉም መነቀል ያለባቸው መሆኑን በስር ፍርድ ቤት የቀረበው የሕክምና ወረቀት የሚያሳይ ሲሆን አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ የግል ተበዳይ ጥርሳቸው የዳነ መሆኑን መግለፃቸውን በማመልከት የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡ ቢሆንም የግል ተበዳይ በዚህ አግባብ ማስመዝገባቸውን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡ከዚህ ይልቅ የህክምና የምስክር ወረቀቱ በአመልካች ቦክስ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው የግል ተበዳይ የሰውነት አካል የሆኑት ጥርሶች መነቀል ያለባቸው መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ በወ/ህ/አ.555(ለ) ስር ታስቦ በሚፈፀም ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ጥፋተኛ ማለቱ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ገደብን አስመልክቶ አመልካች በስር ፍርድ ቤት የካቲት 24 ቀን 2013 ዓም በተፃፈ ባቀረቡት የቅጣት ማቅለያ አስተያየት የገደብ ጥያቄ ያላቀረቡ በመሆኑ በዚህ አግባብም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ገደብን አስመልክቶ የሰጠው ብይን የሌለ ሲሆን አመልካች የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ሲያቀርቡ የገደብ ጥያቄ ያቀረቡ ቢሆንም ቅጣቱን ለመገደብ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች ተሟልተው አለመገኘታቸውን፣ቅጣቱን ለመገደብ የሚያስችል በቂ ምክንያት አለመቅረቡን በመጥቀስ ፍርድ ቤት የገደብ ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡በመሰረቱ ጥፋተኛው

የተፈረደበትን ቅጣት ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ቅጣቱ ታግዶለት አመለ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግ የሚታገድ መሆኑንና ስለጠባዩም መሻሻል አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑ ፍርድ ቤቱ ያመነበት እንደሆነ ቅጣቱን ከወሰነ በኋላ የተወሰነ የፈተና ጊዜ በመስጠት የቅጣቱ አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ለማዘዝ የሚችል መሆኑን የወ/ህ/አ.192 ይደነግጋል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካች በግል ተበዳይ ላይ ለወንጀል ክሱና የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረት የሆነውን ከባድ የአካል ጉዳት ያደረሱት በቂም በቀል ሳይሆን በዕለታዊ ግጭት መሆኑን መሆኑን የግል ተበዳይ በስር ፍርድ ቤት ከሰጡት የምስክርነት ቃል እና ግራ ቀኙ ጥር 26 ቀን 2012 ዓም ካደረጉት የእርቅ ስምምነት ለመረዳት የሚቻል ሲሆን፣አመልካች በግል ተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ካደረሱ በኋላ ከግል ተበዳይ ጋር የተፈጠረውን አለመግባባት በእርቅ መፍታታቸው በድርጊታቸው መፀፀታቸውንና ከዚህ በኋላም በተመሳሳይ ድርጊት ከመሰማራት የሚታቀቡ ለመሆኑ ያሳዩትን ጥረት የሚያሳይ በመሆኑ እንዲሁም የአራዳ ክ/ከ/ወረዳ 5 ዋና ስራ አስፈፃሚ ፅ/ቤት ጥር 09 ቀን 20123 ዓም በሰጠው መግለጫ አመልካች አባት የሌላቸውን ልጆች ብቻቸውን የሚያሳድጉ መሆኑን መግለፁ አመልካች ያለባቸውን ተደራራቢ ሀላፊነት የሚያሳይ ሆኖ እያለ እነዚህ ዝርዝር ሁኔታዎች የእስራት ቅጣቱ ከሚፈፀም ይልቅ ቢገደብ መልካም ውጤት የሚያመጣ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የስር ፍርድ ቤቱ ይህንን በተመለከተ የሰጠውን የውሳኔ ክፍል ብቻ በመሻር በአመልካች ላይ የተጣለው የእስራት ቅጣት በሁለት አመት የፈተና ጊዜ ሊገደብ ይገባል ብለናል፡፡ስለሆነም የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ 1ኛ ይግባኝ ችሎት በመ/ቁ.006623 በ12/09/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.191068 የካቲት 25 ቀን 2013 ዓም በዋለው ችሎት በአመልካች ላይ የሠጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በማፅናት የቅጣት ውሳኔውን በማሻሻል የሰጠው የውሳኔ ክፍል በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.195(2)(ለ)(2) መሰረት ፀንቷል፡፡ገደብን አስመልክቶ የሠጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

ትዕዛዝ

1.አመልካች ለገደብ ስርዓቱ አፈፃፀም በፊተናው ጊዜ ውስጥ በወንጀል ድርጊት ላለመሰማራት ግዴታ ገብተው እንዲፈርሙና ዋስትና ብር 5,000.00(አምስት ሺህ ብር) እንዲያሲዙ ታዟል፡፡

2.አመልካች የእስራት ቅጣቱ ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ ያስያዙት የዋስትና ገንዘብ ለገደብ ዋስትና አፈፃፀም ተመጣጣኝ ስለሆነ በዚሁ አግባብ ተቀይሮ በዋስትናነት እንዲቆይ ታዟል፡፡

3.የስር ፍርድ ቤት መዝገብ በመጣበት አኳኃን ይመለስ፡፡

<u>ጉዳዩ እልባት ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሂ/መ

የሰ/መ/ቁጥር 210037

ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ ኪዳኔ ኃይለማርያም ገብረስላሴ፡- አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- 1ኛ. ወ/ሮ ሳራ ወልደገሪማ ፡- ጠበቃ ሠለሞን መንግስቱ ቀረቡ

2ኛ. አቶ ያሬድ ኃይለስላሴ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ክርክሩ የብድር ውልን መነሻ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች 1ኛ ተከሳሽ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ ጥር 1 ቀን 2011 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት ክስ ከአመልካች ጋር ባለን መቀራረብ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ መኖሪያ ቤት እንዲገዛልኝ ተስማምተን ጥር 8 ቀን 2007 ዓ.ም በቼክ ቁጥር ኤ0272693 ብር 2,773,306.57 ከከሳሽ የሂሳብ ቁጥር ወጪ ሁኖ ተከፍሎታል፡፡ ነገር ግን አመልካች የፌደራል ፍርድ

አፈጻፀም ዳይሬክቶሬት ጨረታ ያወጣበትን በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 312 የሆነ ቤት ዋጋ ጥር 8 ቀን 2007 ዓ.ም በሲፒኦ ቁጥር 218762 ገቢ አድርጎ በራሱ ስም ገዝቷል፡፡ በዚህ ምክንያት ለእዳው መተማመኛ እንዲሆንና ስመ ሀብቱ ሲዛወር የሚቀደድ የብድር ውል እናድርግ ብሎኝ ጥር 8 ቀን 2007 ዓ.ም ለቤቱ መግዣ የሰጠውትን የገንዘብ መጠን ብር 2,773,316.57 ላይ የብድር ውል ተፈራርመናል፡፡ አመልካች ስመ ሀብቱን ሳያዛውርልኝ 1ኛ ተጠሪ ነሐሴ 6 ቀን 2007 ዓ.ም ጋብቻቸው መፍረሱን ጠቅሰው መጋቢት 29 ቀን 2008 የንብረት ክፍፍል ክስ አቅርበው ቤቱን እኩል እንዲካፈሉ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ቤቱ ያንተ ነው ወይም እዳው የጋራ እዳቸው ነው እንዲባልልኝ በሚል ጣልቃ ገብቼ የተከራከርኩ ሲሆን የብድር ውሉን መሰረት በማድረግ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ የማቅረብ መብቱ ተጠብቆልኛል፡፡ ስለሆነም ቤቱ የተገዛው በጋራ እዳ ነው እንዲባልልኝ እና አመልካች የተበደሩትን ብር 2,773,316.57 ከተበደሩበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ወጪ እና ኪሳራ ጋር ከ1ኛ ተጠሪ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አመልካች የካቲት 1 ቀን 2011 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው መልስ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 312 የሆነው ቤት በ2ኛ ተጠሪ ገንዘብ የተገዛ ነው፤ ቤቱ በስሜ ተገዝቶ ወደ 2ኛ ተጠሪ ሳይዞር የተከሳሾች የጋራ ሀብት ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡ በአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ መካከል ያለው ጋብቻ ሳይፈርስ በፊት ጥር 8 ቀን 2007 ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ባደረኩት የብድር ውል ብር 2,773,316.57 የተበደርኩ ስለሆነ እዳው የጋራ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

1ኛ ተጠሪ በበኩሏ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርባለች፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አከራካሪ የሆነው ቤት የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43905 ሰኔ 21 ቀን 2010 ዓ.ም ውሳኔ ስለተሰጠ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 መሰረት ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው የሚል ሲሆን ፍርድ ቤቱ በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በፍሬ ነገር ላይ በሰጠችው መልስ ቤቱ የተገዛው በ2ኛ ተጠሪ ገንዘብ ሳይሆን በጋራ ንብረታችን ነው፡፡ የተገዛውም መጀመሪያ ለጨረታ ብር 56,683.83 ካስያዝን በኋላ ጥር 1 ቀን 2007 ዓ.ም ተጨማሪ ብር 2,773,316.57 ከፍለን ሲሆን ይህም 2ኛ ተጠሪ ባለው የገንዘብ መጠን አለመገዛቱን ያመላክታል፡፡ አመልካች በቼክ የተሰጠውውን ገንዘብ ከባንክ ወጪ ያደረገው ጥር 8 ቀን 2007 ዓ.ም ነው፡፡ ገንዘብ ተበድሯል ከተባለም ለግል ጥቅሙ ስለሆነ የተጠየቀው ዳኝነት አይመለከተኝም በማለት ተከራክራለች፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር፣ የሰው እና የሰነድ ማስረጃ መርምሮ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ባልና ሚስት የነበሩ መሆኑ፤ ጋብቻቸው በመዝገብ ቁጥር 30152 ነሐሴ 6 ቀን 2007 ዓ.ም መፍረሱ፤ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 የሚገኝ የቤት ቁጥር 312 የሆነውን ቤት እኩል እንዲካፈሉ መወሰኑ እና ቤቱን ከፌደራል ፍርድ አፈጻፀም ዳይሬክቶሬት በጨረታ የገዙት መሆኑ አላከራካረም፡፡ በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ በኩል የቀረቡት 2 የጋራ ምስክሮች 2ኛ ተጠሪ አመልካች በጨረታ ቤት እንዲገዛለት መጠኑ ብር 2,773,316.57 የሆነ ቼክ ወጪ አድርጎ ሰጥቶታል፡፡ አመልካች ጨረታውን አሸንፌያለው ብሎ የቤቱ ስም ወደ 2ኛ ተጠሪ

እስኪዞር የብድር ውሉ ለመተማመኛ ተፈርሟል፡፡ ውሉ ሲደረግ 1ኛ ተጠሪ አልነበሩም በማለት አስረድተዋል፡፡ ከአንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ በቁጥር አአባ/የቅ/650/08 ግንቦት 12 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈና በ2ኛ ተጠሪ በኩል የቀረበው ማስረጃም አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ የሂሳብ ቁጥር 001100311322 በቼክ ቁጥር ኤ027693 እ.ኤ.አ. 16/01/2015 ወጪ ያደረገው ብር 2,773,316.57 በሲ.ፒ.ኦ ቁጥር 218762 ተሰርቶ ለፌደራል ፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ገቢ የተደረገ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ የቀረበው የሰው እና የሰነድ ማስረጃ የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ሀብት ነው ተብሎ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቦሌ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 43905 ውሳኔ የተሰጠበት ቤት በ2ኛ ተጠሪ ገንዘብ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ እያሉ የተገዛ መሆኑን የሚያረጋግጥ ስለሆነ ከጠቅላላው ብር 2,773,316.57 ላይ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የድርሻቸው ብር 1,386,658.29 ከጥር 8 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9በመቶ ወለድ ጋር እንዲሁም ለዳኝነት የተከፈለ ብር 30,583.16፣ የጠበቃ አበል ብር 80,000 በድምሩ ብር 110,583.16 ላይ አመልካች ብር 55,291.58፤ 1ኛ ተጠሪም ብር 55,291.16 ለ2ኛ ተጠሪ ይክፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

1ኛ ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበች ሲሆን ግራ ቀኙን አከራክሮ ውል አስገዳጅነቱ በተዋዋዮች መካከል ብቻ መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1731 ላይ ተመላክቷል፡፡ በ3ኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው በፍ/ሕ/ቁጥር 1952 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች በተመላከተው ልዩ ሁኔታ ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ጥር 8 ቀን 2008 ዓ.ም የተደረገው የብድር ውል አስገዳጅነቱ በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል እንጂ በወቅቱ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በትዳር ስለነበሩ ወይም እዳው ለትዳር ጥቅም የዋለ እና የጋራ እዳ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ በመኖሩ ብቻ 1ኛ ተጠሪ ላይ 2ኛ ተጠሪ ክስ አቅርቦ የሚያስወስንበት አግባብ የለም፡፡ የተበደረውን ገንዘብ እንዲከፍል ሊወሰንበት የሚገባው አመልካች ብቻ ነው፡፡ ተዋዋይ በሆነው ተጋቢ ላይ የተሰጠው ውሳኔ የጋራ እዳ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ክርክር ሊነሳ የሚችለው በአፈፃጸም ወቅት ብቻ ነው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ/መ/ቁጥር 22891 እና 132518 ላይ ይህን በማጠናከር የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠበትን ገንዘብ እንዲሁም ወጪና ኪሳራ ሊከፍል የሚገባው አመልካች ብቻ ነው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ሰኔ 24 ቀን 2014 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው ይህን የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡

የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ 1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በአፈፃፀም የሚታይ መሆኑን ገልጸው መከሰሳቸውን በመቃወም ያቀረቡት ክርክር በሌለበት ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ በይግባኝ ደረጃ የቀረበውን ይህን የ1ኛ ተጠሪ አዲስ ክርክር ተቀብሎ መወሰኑ የፍ/ሕ/ቁጥር 182(2)፣ 329(1) እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅፅ 8 በሰ/መ/ቁጥር 37761 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ይቃረናል፡፡ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ብር 2,773,316.57 የተበደርኩት ጥር 8 ቀን 2007 ዓ.ም መሆኑ እና በዚህ ገንዘብ

በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 312 የሆነው ቤት የተገዛው ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያለን ጋብቻ ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ሲሆን ንብረት የጋራ ነው ተብሎ ጋብቻችን ከፈረሰ በኋላ እኩል እንድንካፈል ውሳኔ መሰጠቱ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ይህን በማስተባበል ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ የብድር ስምምነቱም እንዲፈርስ አላደረጉም፡፡ በአንደኛው ተጋቢ የተደረገ የብድር ውል ለጋራ ጥቅም የዋለ መሆኑ ከተረጋገጠ እዳው የጋራ እንደሚሆን በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 70 እና 71 የተመላከተ ሲሆን ይህን የአመልካችን ክርክር በማጠናከር የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 10 በሰ/መ/ቁጥር 45202 እና ቅጽ 11 ሰ/መ/ቁጥር 56184 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ በ1ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ በአፈፃፀም ጊዜ የሚታይ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ የአሁን አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጸና ጋብቻ በነበሩበት ጊዜ ብር 2,773,316.57 ከ2ኛ ተጠሪ ተበድሮ ቤት መግዛቱን አስረድቶ ባለበትና በተቃራኒ 1ኛ ተጠሪ ብሩ ለትዳር ጥቅም ያልዋለ መሆኑን ባላስረዱበት ወይም ውሉን ባላስፈረሱበት ሁኔታ የጋራ እዳ አይደለም ተብሎ የተወሰነበትን አግባብ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 45202 እና 56184 ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር ለመመርምር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ታዟል፡፡

1ኛ ተጠሪ ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት መልስ የብድር ውል የተባለውን ስምምነት የማላውቀው፣ ያልፈረምኩበት እና ልጠየቅበት የማይገባ መሆኑን በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠውት መልስ እንዲሁም በማጠቃለያ ክርክሬ የሰ/መ/ቁጥር 132518ን ጠቅሼ የተከራከርኩ ስለሆነ ይህን በመቃወም አመልካች ያነሱት ክርክር ተገቢነት የለውም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ለመካፈል በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍረድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43905 አመልካች ላይ ክስ አቅርቤ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብተው የተከራከሩ ሲሆን ፍርድ ቤቱ አመልካች ቤቱን ሲገዙ ብር 56,683.83 የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዛቸውን፤ ከአንበሳ ኢንትርናሽናል ባንክ በቼክ ቁጥር ኤ027693 ገንዘቡን ወጪ ያደረጉት ጥር 8 ቀን 2007 ሳይሆን ግንቦት 8 ቀን 2007 መሆኑን ይህም ቤቱን በጨረታ ጥር 1 ቀን 2007 ዓ.ም ገዝተው የቤቱን ዋጋ ጥር 8 ቀን 2007 ዓ.ም ከፍለው ጥር 26 ቀን 2007 ዓ.ም ቤቱን ከተረከቡ በኋላ መሆኑን እና ቤቱን ከ2ኛ ተጠሪ በተበደሩት ገንዘብ አለመግዛታቸውን እና ክርክራቸው በማስረጃ አለመደገፉን ጠቅሶ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህንንም ውሳኔ በማስረጃነት ጠቅሼ በስር ፍርድ ቤት የተከራከርኩ ቢሆንም ማስረጃውን ወደ ጎን በመተው ውሳኔ በመሰጠቱ ይህንን በመቃወም ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ቅሬታዬን አቅርቤያለው፡፡ ነገር ግን ይህን ቅሬታ መመርመር አስፈላጊ ባለመሆኑ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ አልታየም፡፡ በመሆኑም አመልካች የብድር ገንዘቡ ለጋራ ጥቅም ውሏል በማለት ያቀረበው ክርክር እና በሰበር አጣሪው የተያዘው ጭብጥ ተገቢነት የለውም፡፡ ጥር 8 ቀን 2007 ዓ.ም የተደረገው ውል 2ኛ ተጠሪ ቤት እንዲገዛለት ለአመልካች በቼክ ገንዘብ የሰጠው መሆኑን የሚገልጽ ለ2ኛ ተጠሪ ጥቅም የተደረገ በመሆኑ የብድር ውል ሊባል አይችልም፡፡ የጋራ መሆኑ የተረጋገጠው ቤትንም አይመለከትም፡፡ ስምምነቱ የተደረገው ቤቱን ለማሸሽ ነው፡፡ ይህንንም በመጥቀስ በስር ፍርድ ቤቶች መከራከሪያ ያቀረብኩ ሲሆን ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ይህን መመርምር ሳያስፈልገው የፍ/ሕጉ ድንጋጌዎችን

እና የሰበር መዝገብ ቁጥር 132518ን በመጥቀስ የሰጠው ውሳኔ በአመልካች በተጠቀሱት የኋለኛዎቹ ውሳኔዎች ላይ ገገርነት ያለው በመሆኑ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ሰኔ 24 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በነበራቸው የንብረት ክፍፍል ክርክር መዝገብ ላይ 2ኛ ተጠሪ የብድር ውሉን መሰረት አድርጌ ክስ የማቅረብ መብቴ ተጠብቋል። በዚሁ መሰረት 2ኛ ተጠሪ ያቀረብኩትን ክስ የመረመረው የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት ነው በማለት ውሳኔ ያሰጡበትን ቤት የገዙበት ገንዘብ ከ2ኛ ተጠሪ የግል ሒሳብ ወጪ የተደረገ መሆኑን ከአንበሳ ኢነትርናሽናል ባንክ የቀረበውን ማስረጃ፤ ጥር 8 ቀን 2007 ዓ.ም የተደረገውን የብድር ውል ስምምነት፣ ገንዘቡ ለፍርድ አፈጻፀም ገቢ የተደረገበትን ሲፒኦ እንዲሁም የቀረቡትን ምስክሮች ቃል መሰረት በማድረግ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የብድር ገንዘቡን፣ ወለዱንና ወጪ እና ኪሳራን ጭምር እንዲከፍሉ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው። ቤቱን የገዙት በ2ኛ ተጠሪ ገንዘብ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ በቤተሰብ ሕጉ አንቀፅ 70(2) መሰረት በጋራ እንዲከፍሉ መወሰኑ አግባብ ነው። 1ኛ ተጠሪ ስምምነቱን አልተቃወሙም። ከዚህ በተቃራኒ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ለጉዳዩ ተገቢነት የሌለውን የሰበር መዝገብ ቁጥር 132818 ጠቅሶ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክረዋል።

አመልካችም 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ላይ ጥቅምት 3 ቀን 2014 ዓ.ም የተፃፈ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ላይ ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሳቸውን ያቀረቡ ሲሆን የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል።

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ በስር ፍርድ ቤት ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል።

እንደመረመርነው 2ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በዋናነት ክስ የመሰረቱት ከአመልካች ጋር ባለን መቀራረብ በአዲስ አበባ ከተማ የመኖሪያ ቤት እንዲገዛልኝ ተስማምተን በቼክ ቁጥር ኤ0272693 ብር 2,773,306.57 ከከሳሽ የሂሳብ ቁጥር ወጪ ሁኖ ተከፍሎታል። ነገር ግን አመልካች የፌደራል ፍርድ አፈጻፀም ዳይሬክቶሬት ጨረታ ያወጣበትን በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 312 የሆነ ቤት ዋጋ ጥር 8 ቀን 2007 ዓ.ም በሲፒኦ ቁጥር 218762 ገቢ አድርጎ በራሱ ስም በመግዛቱ ስመ ሀብቱን ወደ እኔ እስኪያዛውር ዋስትና እንዲሆነኝ ጥር 8 ቀን 2007 ዓ.ም የብር 2,773,306.57 የብድር ውል ስምምነት አድርገናል። ስመ ሀብቱ ሳይዛወርልኝ በ1ኛ ተጠሪ እና አመልካች መካከል ያለው ጋብቻ መፍረሱን ተከትሎ ቤቱ የጋራ ንብረታቸው ነው ተብሎ ስለተወሰነ እዳው የጋራ ነው ተብሎ ይወሰንልኝ በሚል ነው። የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ በመጀመሪያ የሰማው ፍርድ ቤትም 2ኛ ተጠሪ በክስ አቀራረባቸው መሰረት ስላስረዱ እዳው በጋብቻ ውስጥ የተወሰደ እና ለጋራ ጥቅም የዋለ ነው በሚል አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በጋራ እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቷል።

ከብር 500 በላይ ለመበደር ወይም ለማበደር ወይም ዋስ ለመሆን የተጋቢዎቹ የጋራ ስምምነት የሚያስፈልግ መሆኑን፤ አንደኛው ተጋቢ ይህን ክልከላ በመተላለፍ የውል ግዴታ የገባ እንደሆነ ሌላኛው ተጋቢ ለፍርድ ቤት በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት ግዴታው ሊፈርስ የሚችል መሆኑ ነገር ግን እዳው ለጋብቻ ጥቅም የዋለ መሆኑ ከተረጋገጠ የተጋቢዎች የጋራ እዳ ነው ተብሎ ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ አንቀፅ 68(1)(መ)፤ 70(2) እና 71 ላይ ተመላክቷል። ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ አመልካች ቤት እንዲገዛላቸው በማሰብ በቼክ ቁጥር ኤ0272693 ብር 2,773,306.57 ወጪ አድርገው የሰጡ መሆኑን፤ ይህም ገንዘብ ከአንበሳ ኢንትርናሽና ባንክ ወጪ ተደርጎ ሲፒኦ ተሰርቶ በፌደራል ፍርድ አፈፃፀጸም ዳይሬክቶሬት አካውንት ገቢ ተደርጎ የጋራ ነው ተብሎ ውሳኔ የተሰጠበት ቤት መገዛቱን በማረጋገጥ ገንዘቡ ለጋራ ጥቅም የዋለ ስለሆነ የጋራ እዳ ነው በሚል ውሳኔ ሰጥቷል።

በሌላ በኩል ይግባኝ ሰሚው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ በብድር ውሉ ስላልፈረሙ እና ውል ተፈጻሚነቱ በተዋዋዮች መካከል ብቻ ነው። እንዲሁም እዳው የጋራ ነው አይደለም የሚለው ሊነሳ የሚችለው በአፈጻጸም ወቅት ስለሆነ 1ኛ ተጠሪ በእዳው ሊጠየቁ አይገባም በሚል የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሯል። እኛም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ የተያዘውን ክርክር ይዘት ያገናዘበ መሆኑን ወይም አለመሆኑን እንደሚከተለው ተመልክተናል። ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ ነሐሴ 06 ቀን 2007 ዓ.ም ፈርሶ የንብረት ክፍፍል ውሳኔ ተሰጥቷል። የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት ነው በሚል የክፍፍል አካል ከሆኑ ንብረቶች ውስጥ አንዱ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 የሚገኝ የቤት ቁጥር 312 ነው። ይህ ቤት ለንብረት ክፍፍል ውሳኔ አፈጻጸም ሲባል የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት እንዲሸጥ ጨረታ አውጥቶበታል። 2ኛ ተጠሪ ለክሳቸው መሰረት ያደረጉት ይህ ቤት የተገዛበት ገንዘብ ለአሁን አመልካች በሰጡት የብድር ገንዘብ የተገዛ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ የቤቱ ተጠቃሚ ከሆኑ የተገዛበትን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው በሚል ነው። የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ የንብረት ክፍፍል ክርክር በሂደት ላይ እያለ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ለመግባት አመልክተው ፍርድ ቤቱ የብድር ውሉን መሰረት በማድረግ የመክሰስ መብት ጠብቆላቸዋል። 2ኛ ተጠሪ ይህ ቤት የተገዛው በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ የጋራ እዳ ነው ተብሎ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በጋራ እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት የጠየቁትም በዚህ መነሻነት እንደሆነ ይታመናል። በእርግጥ ቤቱ የተገዛው አመልካች በብድር ውል ከ2ኛ ተጠሪ በወሰዱት ገንዘብ መሆኑ ከተረጋገጠ እና በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ ሊከሰሱ አይገባም የሚባል ከሆነ ሁለት አሉታዊ ውጤቶችን ያስከትላል። አንደኛው አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በጋራ ባፈሩት ገንዘብ ሳይሆን በ2ኛ ተጠሪ ገንዘብ የተገዛውን ቤት ግማሹን 1ኛ ተጠሪ እንዲወስዱ የሚያደርግ ሲሆን በዚህም 1ኛ ተጠሪ ያላግባብ እንዲበለጽጉ ምክንያት ይሆናል። ሁለተኛ አመልካች በአንድ በኩል እዳውን በግላቸው እየከፈሉ በሌላ በኩል ለእዳው ምክንያት በሆነው ገንዘብ የተገዛውን ቤት ግማሹን 1ኛ ተጠሪ እንዲወስዱ በማድረግ አመልካች አላግባብ እንዲጎዱ ምክንያት ይሆናል። ስለዚህ ለክርክሩ መሰረት የሆነው ቤት የተገዛበት ገንዘብ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ በተበደሩት ገንዘብ መሆኑ ከተረጋገጠ 2ኛ ተጠሪ አላግባብ ሊበለጽጉ ስለማይገባ

በፍ/ሕ/ቁጥር 2062 መሰረት 1ኛ ተጠሪ የብድር ገንዘቡን ከአመልካች ጋር በጋራ የመመለስ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

በዚህ አግባብ አጠቃላይ የክርክሩ ሂደት ሲታይ የአመልካች ኃላፊነት መሰረቱ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት የብድር ውል ሲሆን የ1ኛ ተጠሪ ደግሞ በብድር ገንዘቡ ተገዝቷል የተባለውን ቤት ግማሽ ተጋሪ በመሆናቸው ከውል ውጪ የሆነ ኃላፊነት ሊኖርባቸው ይችላል፡፡ አመልካች ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ የሚያቀርቡት ክርክር ይዘትም ሲታይ ከ2ኛ ተጠሪ የወሰዱትን ገንዘብ 1ኛ ተጠሪ የግማሽ ድርሻ ባለቤት የሆኑበትን ቤት ለመግዛት ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑን በመግለጽ ኃላፊነቱን ብቻዬን ልሸከም አይገባም የሚል ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች በቀረበላቸው የፍትሐ ብሔር ክርክር ላይ ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት ትክክለኛውን ጭብጥ መያዝ እንዳለባቸው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 246/1 ላይ ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ ጭብጥ የሚያዘው እንደየአግባብነቱ ግራ ቀኙ በጽሁፍ ያቀረቡትን ክርክር፤ ክሱ በሚሰማበት ጊዜ ያቀረቡት ሀሳብ እንዲሁም ያቀርቡትን ማስረጃዎች መሰረት በማድረግ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 248 ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ክርክሮችን በአግባቡ በመምራት፤ የግራ ቀኙን ክርክር መሰረታዊ ባህሪ ያገናዘበ ጭብጥ በመያዝ፤ ለትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑ ፍሬ ነገሮች ነጥረው እንዲወጡ በማድረግ ጉዳዮችን አጣርቶ መወሰን የፍርድ ቤቶች ሃላፊነት መሆኑ አያከራክርም፡፡ በዚህም መሰረት ከተያዘው ጉዳይ መሰረታዊ ባህሪ የተነሳ በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት መያዝ የሚገባው ትክክለኛ ጭብጥ 2ኛ ተጠሪ በክሳቸው የገለጹት እና 1ኛ ተጠሪ በግማሹ ላይ ባለቤት የሆኑበት ቤት የተገዛው አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ በተበደሩት ገንዘብ መሆን አለመሆኑ ነው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን በጭብጥነት በመያዝ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን አግባብነት ይህንን ጭብጥ መሰረት በማድረግ መመርመር ሲገባው ከተያዘው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይነት በሌለው የፍሬ ነገር ክርክር ላይ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር መዝገብ ቁጥር 22891 እና 132518 የተሰጠ ውሳኔን በመጥቀስ 1ኛ ተጠሪ በአፈጻጸም ከሚጠየቁ በቀር ክስ ሊቀርብባቸው አይገባም በሚል ውሳኔ መስጠቱ የተያዘውን ክርክር ባህሪ ያላገናዘበ የክርክር አመራር ግድፈት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍመዝገብ ቁጥር 188535 ሰኔ 11 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቁጥሩ 188535 የሆነውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ለክርክሩ መሰረት የሆነው እና 1ኛ ተጠሪ በግማሹ ላይ ባለቤት የሆኑበት ቤት የተገዛው አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ በተበደሩት ገንዘብ መሆን ወይም አለመሆኑን? ከግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ጋር አገናዝቦ ተገቢውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ን

የሰበር መ/ቁ/210256

ግንቦት 1 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች ፡1ኛ/ ተማሪ የውብዳር ጫካ
2ኛ/ ተማሪ ያሬድ ጫካ } አልቀረቡም

ተጠሪ፡ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን -- ነ/ፈጅ መቅደስ ኮርሜ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የሥራ ላይ ጉዳት ካሳ ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች ከሳሽ በመሆን በአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ወላጅ አባታችን ሟች አቶ ጫካ ሰቦቃ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ የዶዘር ኦፕሬተር ሆነው በማገልገል በስራ ላይ እያሉ ህይወቱ በቀን 30/01/2001 ዓ.ም ያለፈ በመሆኑ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 110(3)(ለ) መሰረት የጉዳት ካሳና ለቀብር ማስፈፀሚያ የወጣ ወጪ ጨምሮ በድምሩ ብር 130,000.00 እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቋል፡፡ተጠሪ በበኩሉ በሰጠው መልስ የአመልካቾች አባት የሞቱት በተጠሪ መ/ቤት ስራ ላይ እያለ ሳይሆን ሲሰሩበት የነበረው ዶዘር በጉራጌ ዞን ወልቂጤ ከተማ ካምፕ ውስጥ አቁመው ውቤ በሚባል ወንዝ ውስጥ ነው፤የአመልካቾች አባት የሞቱት በስራ ላይ እያሉ ነው ቢባል እንኳን የሟች ደመወዝ 2000 ብር ሳይሆን ብር 1273 መሆኑን ሊከፈላቸው የሚገባ ካሳ

በአንቀጽ110(3)(ለ) መሰረት በ10% መጠን ለእያንዳንዳቸው ብር 7,650 ሲሆን ለቀብር ማስፈፀሚያ የሁለት ወር ደመወዝ ብቻ ነው በማለት መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ ፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ የአመልካቾች ምስክሮች ሟች በስራ ላይ እያለ የሞት አደጋ እንዳጋጠማቸው የገለፁ ቢሆንም ምስክሮቹ የሟች የስራ ባልደረባ እንዳልነበሩና በሌላ የድንጋይ ማምረቻ ፕሮጀክት ላይ እያለ የጩሄት ድምጽ ሰምተው የመጡ መሆናቸው፤ከፖሊስ ምርመራና የዳግማዊ ሚኒልክ ሆስፒታል አስከሬን ምርመራ ውጤት የሟቹ ሞት ምክንያት ወንዝ ውስጥ ሰምጠው መገኘት ነው ከሚለው የህክምና ማስረጃ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌለው በመሆኑ የአመልካች ምስክሮች የሰጡት ቃል ሚዛን የሚደፋ ሆኖ አላገኘነውም በማለት የአመልካቾች አባት በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 107 መሰረት በስራ ቦታና በስራ ላይ እያለ ስለመሞታቸው አመልካቾች አላስረዱም እንዲሁም ሟች የሞቱት ውኃ ውስጥ ሰምጠው መሆኑ በህክምና ማስረጃ በመረጋገጡ አመልካቾች የጉዳት ካሳና የቀብር ማስፈፀሚያ ክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የሚያስለውጥ በቂ ምክንያት አላገኘነውም በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኝ ሰርዞባቸዋል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ሲታይ፡-አባታችን የሞት አደጋ የደረሰባቸው ለስራ እየተጠቀሙበት ያለው ዶዘር መኪና አጠገብ በሥራ ላይ ባሉበት ወቅት ወድቀው የተገኙ እና የሞቱ መሆናቸው በስር ፍ/ቤት የዓይን ምስክሮችን በማስቀረብ አስረድተናል፤ይህንን የምስክሮች ቃል የሚያስተባብል በተጠሪ በኩል አልቀረበም፤ ከዳግማዊ ሚኒሊክ የተሰጠው የኤክስፐርት ማስረጃ ሟች ወንዝ ገብተው የሞቱ መሆናቸውን የሚገልፅ እንጂ ሟች በስራ ላይ እያለ ወይም ከሥራ ውጪ እያለ መሞታቸውን የሚያስረዳ ማስረጃ አይደለም፣ በተጨማሪም የአስከሬን ምርመራ በሳንባና ከልብ ጡንቻቸው ላይ ቁስልና የመድማት እንደተገኘ የሚገልጸዉ ሟች በሌላ 3ኛ አካል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ያሳያል፣ተጠሪ የአመልካቾች ማስረጃ የሚያስተባብል ማስረጃ ሳያቀርቡ የአመልካቾች ክስ ውድቅ የሚያደርግበት ምንም አይነት ማስረጃ ሳይኖር ክሱን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ የአመልካቾች መብት ተጠብቆ ውሳኔ እንዲሰጥልን በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የአመልካቾች አባት የተጠሪ ድርጅት ሰራተኛ መሆናቸው ባልተካደበትና ሞተው የተገኙት በስራ ቦታ ይሰሩበት በነበረ መሳሪያ ወይም ማሽን አጠገብ መሆኑ በሰው ምስክር አስረድተው ሳለ የስር ፍ/ቤቶች ይህን አልፈው በስራ ላይ ስለመሞታቸው አላስረዱም ያሉበትን ከማስረጃ ምዘና አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

ተጠሪ በቀን 3/05/2014ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ ተጠሪ ጉዳዩን የሚያስረዱለትን የሰነድ ማስረጃ ከዳግማዊ ሚኒሊክ የባለሙያ ምስክር ማስረጃ ያቀረበ መሆኑን፣የአመልካቾች አባት በስራ ላይ እንዳልሞቱ እና ወንዝ ውስጥ ገብተው መሞታቸውን የህክምና ማስረጃ በቂ ስለሆነ የሰው ምስክር ባለማሰማቱ ጉዳዩን አላስተባበለም የሚለው አቤቱታ የህግ መሰረት የለውም፡፡በተቃራኒ አመልካቾች በተጠሪ የቀረበውን በባለሙያ የተረጋገጠ ጉዳይ ለማስተባበል በቂ ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤት ጥያቄያቸውን ውድቅ አድርጎባቸዋል፡፡ስለዚህ የስር ፍ/ቤቶች የማስረጃ ምዘና የህግ ስህተት ያልተፈጸመ በመሆኑ ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲጸና በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካቾች አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበትን ጭብጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ አመልካቾች ሐምሌ 10 ቀን 2010ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት አድርገዉ ባቀረቡት ክስራ አባታቸዉ የተጠሪ ሰራተኛ ሆኖ በስራ ላይ መሞታቸዉን ገልጸዉ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መሰረት የጥገኛ ካሳ እና የቀብር ማስፈጸሚያ ወጪ እንዲከፈላቸዉ እንዲወሰን የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የአመልካቾች አባት የሞቱት በስራ ላይ አይደለም ወንዝ ዉስጥ ገብተዉ ነዉ በሚል ሃላፊነት እንደሌለበት መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡

በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ እንደተደነገዉ ሰራተኛዉ በስራ ምክንያት በደረሰበት ጉዳት የሞተ እንደሆነ ለጥገኞቹ ካሳ እና የቀብር ማስፈጸሚያ ወጪ አሰሪዉ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110 ይመለከታል፡፡ከድንጋጌዉ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ አሰሪ ለሰራተኛዉ ጥገኞች ካሳ እንዲከፍል የሚገደደዉ ሰራተኛዉ የሞተዉ በስራ ላይ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ጥገኞቹ ካሳ እንዲከፈላቸዉ ሲጠይቁ ሰራተኛዉ የሞተዉ በስራ ላይ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ስለመሆኑ የማስረዳት ግዴታ

አለባቸዉ፡፡የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2001 እና የፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር 258-259 የተደነገገዉ ይህንኑ ያመላክታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ማስረጃ የመመዘን እና የክርክሩን ፍሬነገር የማረጋገጥ ሃላፊነት የተሰጣቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች በግራቀኙ የቀረበዉን ማስረጃ መርምረዉና አመዛዝነዉ የአመልካቾች አባት የሞቱት ወንዝ ዉስጥ ሰምጠዉ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ይህ ደግሞ ከስራዉ ጋር የሚያያዝበት ሁኔታ ስለመኖሩ የተገለጸ ምክንያት የለም፡፡አመልካቾች አሁንም አጥብቀዉ የሚከራከሩት አባታቸዉ የሞቱት ስራ ቦታ ላይ ስለመሆኑ ምስክሮች አስረድተዉ እያለ የስር ፍርድ ቤት የማስረጃ ምዘና ስህተት ፈጽሟል በማለት ነዉ፡፡

በመሰረቱ ሰበር ችሎቱ ማስረጃ የመመዘንና እና ፍሬነገር የማረጋገጥ ስልጣን የለዉም፡፡እንደሚታወቀዉ የሰበር ስርዓት የተዘረጋበት ዋና ዓላማ በህግ አተገባበር ወይም አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም ወጥ የህግ አተረጓጎም እና አተገባበር እንዲኖር ማስቻል ነዉ፡፡የሰበር ችሎቱ ስልጣንም የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠባቸዉ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ይህንኑ በማረም ላይ የተገደበ መሆኑን ከሰበር ስርዓት መሰረታዊ ዓላማ የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ ይዘትና መንፈስ ይህንኑ የሚያመለክት ሲሆን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በሰበር ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሚያሰኙት ሁኔታዎች ምንድናቸዉ ለሚለዉ ትርጉም መሰጠቱ (አንቀጽ 2/4/ ይመለከታል) ሰበር ሰሚ ችሎት የተቋቋመበትን ዓላማ ማለትም ወጥ የህግ አተረጓጎም እንዲኖር እና የዉሳኔዎችን ተገማችነት በማረጋገጥ ረገድ አገራዊ ፋይዳ ያላቸዉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት እንዲሰራ የሚያስችል ነዉ፡፡መሰረታዊ ህግ ስህተት ምንድነዉ? ለሚለዉ በአዋጁ አንቀጽ 4 ስር ከሀ-ሸ የተመለከተ ሲሆን በሰበር ችሎቱ ሊታዩ የሚችል የመጨረሻ ዉሳኔ፣ ፍርድ፣ብይን ወይም ትእዛዝ ላይ ህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ህግን አለ አግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣በፍርድ አፈጻጸም ሂደት ከዋና ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትእዛዝ የተሰጠበት፣ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ዉሳኔ ጉዳይ ስለመሆኑ

ተደንግጓል፡፡ስለዚህም ለሰበር የቀረበዉ ጉዳይ ከእነዚህ ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

በተያዘዉም ጉዳይ ምንም እንኳን በአመልካቾች አባት እና በተጠሪ መካከል በቅጥር ላይ የተመሰረተ አሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት መኖሩ አከራካሪ ባይሆንም የአመልካቾች አባት የሞቱት በስራ ላይ በደረሰባቸዉ ጉዳት መሆን አለመሆኑ ግራቀኙን የተለያዩበት ፍሬነገር ጉዳይ ነዉ፡፡አከራካሪዉን ፍሬነገር የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ያላቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾች አባት የሞቱት ወንዝ ዉስጥ ገብተዉ እንጂ ከስራቸዉ ጋር በተያያዘ በደረሰባቸዉ ጉዳት ወይም ምክንያት አለመሆኑን ድምዳሜ ላይ መድረሳቸዉን ተገንዝበናል፡፡በፍትሓብሔር ጉዳይ የምንከተለዉ የማስረጃ ምዘና መርህ አከራካሪዉ ፍሬነገር መኖር/አለመኖሩ ወይም መፈጸም/አለመፈጸሙን ከግራቀኙ በተሻለ ደረጃ ``preponderance of evidence`` የትኛዉ ወገን ማስረጃ አስረድቷል የሚለዉን በመመርመር እና በማመዛን እንደሆነ ይታወቃል፡፡በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ችሎት በተለያዩ መዝገቦች የሰተዉ ዉሳኔ ይህንኑ ያሣያል፡፡(በሰበር መ/ቁ/37105፣29861፣47551፣49660 እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ መመልከት ይቻላል)፡፡ከዚህ አኳያ በዚህ መዝገብ በቀረበዉ ክርክር በማስረጃ ምዘና ረገድ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት መኖሩን የሚያሳይ ጉድለት አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ የጥገኛ ካሳ ለአመልካቾች ለመክፈል ሃላፊነት አለበት ወይ የሚለዉን በመወሰን ረገድ ግራቀኙን ያከራከረዉ ጉዳይ የአመልካቾች አባት የሞቱት በስራ ላይ በደረሰባቸዉ ጉዳት ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉ ጭብጥ በመመርመርና ማስረጃ በመመዘን ጉዳቱ የደረሰዉ ከስራ ጋር በተገኘ አለመሆኑን በማረጋገጥ የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ሃላፊነት የለበትም በማለት የሰጡት ዉሳኔ የማስረጃ ምዘና መርህ መሰረት ያደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4/ እና 10(1) ድንጋጌዎች መሰረት ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን አንጻር ሲታይ በዉሳኔዉ ላይ ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

1ኛ/በዚህ ጉዳይ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/250255 ላይ በቀን 30/07/2013ዓ.ም የሰጠዉ ብይን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡ይጻፍ

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

አ/መ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 210328

ህዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- ሳንቱ የህክምና ማዕከል-- ጠበቃ ዜና ደባሉ ቀርበዋል

ተጠሪ- ወ/ሮ ህይወት ጌትነት - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ስንብትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረውም በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ በቀን 04/03/2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በፋርማሲስት የስራ መደብ ላይ ከቀን 11/04/2011 ዓ.ም ጀምሮ በወር ብር 11,200.00 እየተከፈለኝ እስከ ቀን 30/12/2012 ዓ.ም ድረስ ሳገለግል ብቆይም አመልካች በወቅቱ በነበረው የኮቪድ 19 ወረርሺኝ ምክንያት ያለማስጠንቀቂያ እና ካሳ የስራ ውሌን አቋርጦታል፡፡ ስለሆነም ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ተብሎ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የሁለት ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የስድስት ወር ደሞዝ ካሳ፣ ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት የሶስት ወር ደሞዝ፣ የ2011 ዓ.ም የ14 ቀን እና የ2012 ዓ.ም የ15 ቀን የዓመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በበኩሉ በሰጠው መልስ የተጠሪን ደመወዝ፣ የቅጥር ዘመን እና የስራ መደብ ያመነ ሲሆን ስንብቱን በሚመለከት ተጠሪ እንደሚሉት የስራ ውላቸው የተቋረጠው በህገ-ወጥ መንገድ ሳይሆን ለገሃር አካባቢ ይገኝ የነበረው የአመልካች የጤና ማዕከል አካባቢው ለልማት በመፈለጉ ምክንያት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እንዲፈርስ ሲደረግ በርካታ ሰራተኞች ተሰናብተዋል፤ ተጠሪ ስራ እንዳይፈቱ በሚል ምክያት በተቋሙ ስር በሚተዳደረው ሳንቴ ዲያግኖስቲክ ላባራቶሪ ተዘዋውረው በፋርማሲ ግምጃ ቤት ውስጥ እንዲሰሩ ተደርጓል፤ ይሁን እንጂ ተጠሪ ያሳዩት የስራ ውጤት እና መሻሻል አጥጋቢ ስላልነበረ ከአስተዳደር ኃላፊው ጋር ተነጋግረው የስራ ውላቸው እንዲቋረጥ የተስማሙ፣ ክፍያን በሚመለከት ክሊራንስ ካዞሩ በኋላ በህጉ መሠረት እንደሚከፈላቸው ተገልፆላቸው ማስፈረም ጀምረው የአስተዳደር ውሳኔ እና ፊርማ ሲቀራቸው ያቆሙ በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው፤ የዓመት እረፍት ክፍያን በሚመለከት ተጠሪ ያላቸውን ጊዜ ተጠቅመው ጨርሰው ተጨማሪ የ8.5 ቀን እረፍት የተጠቀሙ በመሆኑ እንዲያውም ለአመልካች ብር 3,173.33 ሊከፍሉ ስለሚገባ ይህኑ ገንዘብ ይክፈሉ ተብሎ ይወሰንልን፤ የምስክር ወረቀትን በመተመለከተ ደግሞ ለመስጠት ዝግጁ ነን በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ምን እንኳን አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለን የስራ ውል ግንኙነት በስምነት የተቋረጠ ነው ቢልም ይህንኑ የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረበ ከመሆኑ በላይ የስራ ውሉ በተቋረጠበት ወቅት የኮቪድ 19 ወረርሽኝን ለመከላከል በወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012 እና ደንብ ቁጥር 446/2012 አንቀጽ 33(9) መሠረት የስራ ውልን ማቋረጥ በተከለከለበት ጊዜ በመሆኑ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው፤ አመልካች ለተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የሁለት ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የስድስት ወር ደሞዝ ካሳ በጠቅላላው ብር 103,156.00 እንዲከፍልና የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ፤ የዓመት እረፍት ክፍያን እና ለገዘየ ክፍያ ቅጣት እንከፈላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ በሚመለከት ደግሞ ተጠሪ ያልተጠቀሙት ጊዜ ስለመኖሩ በማስረጃ ያረጋገጡ እና ክፍያው የዘገየውም ክሊራንስ አዙረው ያልጨረሱ በመሆኑ ስለሆነ ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያ የለም፤ እንዲሁም አመልካች ተጠሪዋ ካላቸው የዓመት እረፍት ውጪ የተጠቀሙ በመሆኑ የተጠቀሙበት ጊዜ በገንዘብ ተቀይሮ ይክፈሉኝ ሲል ያቀረበውን ጥያቄ በዚህ መዝገብ የሚስተናገድ አይደለም በማለት ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኘው አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ይግባኙ ተሠርዞበታል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 30/10/2013 ዓ.ም በተፃፈ 03 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያላቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙለት ጠይቋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገውን መግባባት እና የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ፤ አመልካች በስራ አጋጣሚ ያጎደሉትን ንብረት ቀርበው መተማመኛ እንዲሰጡ ተጠይቀው እምቢተኛ ሆነው እያለ፤ እንዲሁም ተጠሪ ስንብቱ የተደረገበትን የቃል ስምምነት በመቀበል ለተግባራዊነቱም ክሊራንስ ማዞር መጀመራቸው የስራ ውሉ ተቋርጦ ጥቅማጥቅም ለመስጠት የነበረውን መግባባት የሚያሳይ ሆኖ እያለ ስምምት ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ የለም ተብሎ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው መባሉ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረበውን እና ተጠሪ የስራ ውላቸውን ያቋረጡት በስምምነት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ የስር ፍርድ ቤቶች ከተቀበሉት

በኋላ ማስረጃውን ያለፉበት፣ ስምምነት አይደለም፣ ስንብቱም ህገ-ወጥ ነው ያሉበት አግባብነት ተጠሪ ባሉበት መጣራት አለበት በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል። በዚሁም መሠረት ተጠሪ በቀን 28/11/2013 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኞችንን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍ ባለመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል። አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቶ ተከራክሯል።

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ከተያዘው ጭብጥ፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረዉም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት በኮቪድ ወረርሽኝ ወቅት ሠራተኛን ከስራ ማሰናበት የሚከለክለዉን ህግ በመተላለፍ አመልካች የወሰደባቸዉ የስራ ማሰናበት እርምጃ ህገ ወጥ መሆኑን ሲሆን፣ አመልካች በሰጠዉ መልስ የስራ ዉሉ መቋረጡን ሳይክድ ሊቋረጥ የቻለዉ ለገሐር የነበረዉ የአመልካች የጤና ማዕከል በልማት ምክንያት በመፍረሱ ብዙ ሠራተኞችን ያሰናበተ ሲሆን ተጠሪ ስራ እንዳይፈቱ በማሰብ በጤና ማዕከሉ ስር በሚተዳደረዉ ሳንቴ ዲያጎኖስትክ ላብራቶሪ በመድሃኒት ሻጭነት የመደባቸዉ ቢሆንም የስራ አፈፃፀማቸዉ አጥጋቢ ባለመሆኑ ከአስተዳደሩ ጋር ዉይይት ተደርጎ ዉሉ በስምምነት ነዉ በማለት ይከራከራል።

የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ይህንኑ በጭብጥነት በመያዝ አመልካች የስራ ዉሉ የተቋረጠዉ በስምምነት ነዉ በማለት የሚከራከር ቢሆንም በህግ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 25 መሠረት በጽሑፍ የተደረገ ስምምነት መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረቡን፣ አመልካች ተጠሪ በተመደቡበት ስራ ያሳዩት አፈፃፀም አጥጋቢ መሆኑን ገልፆ የሚከራከር ቢሆንም ይህን የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረቡን ከድምዳሜ ላይ ደርሷል። አዋጅ ቁጥር 1156 ከአንቀጽ 23 ጀምሮ ባሉት አንቀጾቹ የስራ ዉል የሚቋረጥባቸዉን ሁኔታዎች የሚደነግግ ሲሆን፣ የተቋረጠዉ የስራ ዉል ህጋዊ መሆን ያለመሆኑ አጣርቶ በመወሰን ረገድ የስራ ዉሉ የተቋረጠበት ምክንያት እንደየጉዳዩ ባህርይ በእነዚህ ድንጋጌዎች ላይ ከተመለከቱት ሁኔታዎች አንፃር መመርመር ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ፣ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉ ተጠሪ በተመደቡበት ስራ ያሳዩት አፈፃጸም አጥጋቢ ባለመሆኑ ዉይይት ተደርጎ ዉሉ በስምምነት የተቋረጠ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ። በአዋጁ አንቀጽ 25 (2) ላይ ከተመለከተዉ ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የስራ ዉልን በስምምነት ማቋረጥ ህጋዊ ዉጤት የሚኖረዉ ስምምነቱ በጽሑፍ የተደረገ ሲሆን ነዉ። አመልካች በጽሑፍ የተደረገ ስምምነት ያላቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን ለማጣራት ስልጣን ባለዉ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል። ከላይ እንደተመለከተዉ ተጠሪ በተመደቡበት ስራ ያሳዩት አፈፃፀም አጥጋቢ አለመሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አመልካች አለማቅረቡ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በእርግጥም የስራ አፈፃፀማቸዉ አጥጋቢ አለመሆኑ እንደነገሩ ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ 27(1/ሠ) ወይም በአንቀጽ 28(1/ሀ) መሠረት አመልካች በእራሱ አነሳሽነት ዉሉን ማቋረጥ እንዲችል ምክንያት ሊሆን ይችላል፤ ከዚህ ዉጭ ዉሉን ለማቋረጥ ተጠሪ መስማማታቸዉን የሚያሳይ በጽሑፍ

የተደረገ ስምምነት ባልቀረበበት ሁኔታ የተጠሪ ስራ አፈፃፀም አጥጋቢ የነበረ መሆን ያለመሆኑ እንዲሁም ተጠሪ ክሊራንስ ያዞሩ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባዉ ነጥብ አይደለም፡፡ አመልካች እንደሚለዉ ተጠሪ ያጎደሉት መድሃኒት መኖሩ እና የክሊራንስ ሂደት ማጠናቀቅ አለማጠናቀቃቸዉ በጽሑፍ ያልተደረገን ስምምነት ህጋዊ የማድረግ ዉጤት ስለማይኖረዉ አመልካች በዚህ ረገድ የሚያነሳዉም ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ የስራ ዉል የሚቋረጥበትን አግባብ በተመለከተ አዋጁ የተለያዩ ምክንያቶችን የሚደነግግ ሲሆን አመልካች የስራ ዉሉ የተቋረጠዉ በህጋዊ መንገድ ነዉ በማለት የሚከራከረዉ ዉሉ በስምምነት የተቋረጠ መሆኑን በመጥቀስ ሆኖ ነገር ግን ስምምነቱ በጽሑፍ የተደረገ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረበ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስንብቱ ህጋዊ ነዉ በሚል መወሰኑም ሆነ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ይህንኑ በትዕዛዝ በማጽናቱ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁጥር 80236 ላይ የካቲት 15 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 250562 ላይ ግንቦት 26 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንተዋል፡፡
2. የሰበር አጣሪ ችሎት ሐምሌ 02 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

ማ/አ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ.መ.ቁ.210420
ሕዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- እሸቱ ይመር- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- መብራቱ ታደሰ- ጠበቃ ልጅአለም ባልቻ ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 02 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 118021 በመጋቢት 10 ቀን 2013 ዓ.ም አመልካች በጉዳዩ ላይ አስቀድሞ የተሰጠውን ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 በመቃወም አቤቱታ ከሚያቀርብ በቀር አዲስ ክስ ማቅረብ አይችልም በማለት የሰጠው ብይን፤ ይህንኑ ብይን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 270575 በግንቦት 24 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ውስጥ የሚገኝ አዋሳኙ በክሱ ላይ የተገለጸውን ይዞታ ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ያለማቋረጥ ግብር እየከፈሉ የሚጠቀሙበት መሆኑን፤ ሆኖም ተጠሪ ምንም ዓይነት መብት ሳይኖራቸው ከጥር 15 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የያዙባቸው መሆኑን በመግለጽ ይዞታውን ለቀው እንዲያስረክቧቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በሰጡት መልስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ይዞታ አስመልክቶ በፌዴራል በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 73198 እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር መነሻነት በተሰጠ ውሳኔ በአፈጻጸም የተረከብት መሆኑን፤ አመልካች ፍርዱን ከመቃወም በቀር አዲስ ክስ ለማቅረብ የማይችሉ መሆኑን በመግለጽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ተጠሪ ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ይዞታውን የተረከቡት በፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ መነሻነት በአፈጻጸም ነው፤ አመልካች በፍርዱ መብቴ ተነክቷል የሚሉ ከሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት ፍርዱን ከሚቃወሙ በቀር አዲስ ክስ ማቅረባቸው ሥነ-ሥርዓታዊ አይደለም በማለት የአመልካችን ክስ በብይን ውድቅ አድርጓል፡፡ ይህም ብይን በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ ጸንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- በተጠሪ እና በአቶ ባሕረዲን መክታር መካከል በነበረው ክርክር አመልካች ተሳታፊ አልነበርኩም፤ በጉዳዩ ላይ ፍርድ ማረፉን እና መፈጸሙን ያወኩትም በስር ፍርድ ቤት ላቀረብኩት ክስ ተጠሪ በሰጠው መልስ ነው፤ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት ፍርዱን ከመቃወም በቀር አዲስ ክስ ማቅረብ አትችልም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በፍርድ አረጋግጦ በአፈጻጸም በተረከበው ንብረት ላይ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ ከማቅረብ በቀር አዲስ ክስ ማቅረብ አይችልም በማለት የሰጠው ብይን አግባብነት ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ነጥብ በመያዝ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ፍርድ ባረፈበት ንብረት ላይ ክርክር ሲካሄድ የማያውቅ መሆኑን አላስረዳም፤ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ንብረት ውሳኔ ያረፈበት እና ውሳኔውም የተፈጸመ በመሆኑ አመልካች አዲስ ክስ ማቅረብ አይችልም፤ ስለሆነም ይህንኑ መሠረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይን ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ክስ ያቀረቡበት ይዞታ በተጠሪ እና በሌላ ግለሰብ መካከል በተደረገ ክርክር መነሻነት ውሳኔ አርፎበት ተጠሪ በአፈጻጸም የተረከቡት መሆኑን እና ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ይህንኑ መሠረት በማድረግ አመልካች በፍርዱ መብቱ ተነክቷል የሚሉ ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት ፍርዱን ከሚቃወሙ በቀር አዲስ ክስ ማቅረብ አይችሉም በማለት የአመልካችን ክስ በብይን ውድቅ ያደረገው መሆኑን ነው፡፡ ይህም ይዞታውን በሚመለከት በአሁን ተጠሪ እና በሌላ ግለሰብ መካከል አስቀድሞ የተደረገው ክርክር መነሻነት የተሰጠው ውሳኔ የተፈጸመ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በአንድ ንብረት ላይ መብት አለኝ፣ በክርክሩ ሂደት አልተካተትኩም በሚል ምክንያት መብቱ ተነክቷል የሚል ወገን መብቱን ሊያስከብር የሚችልበትን ሥርአት በየደረጃው ዘርግቷል፡፡ ለዚህም ጉዳዩ በክርክር ሒደት ላይ ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41 መሠረት የጣልቃገብነት አቤቱታ በማቅረብ፤ ውሳኔው ከመፈጸሙ በፊት ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሰረት የመቃወም አቤቱታ በማቅረብ፤ ውሳኔው በአፈፃፀም ሂደት ላይ ሆኖ ንብረቱ ያለአግባብ ተይዞብኛል የሚል ወገን ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 418 መሰረት መብቱን ማስከበር የሚችልበት አግባብ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በዚህ አግባብ መብቱን ማስከበር የማይችል እና በንብረቱ ላይ የተሻለ መብት አለኝ የሚል ተከራካሪ ወገን ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 421 ወይም እንደነገሩ ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 455 መሰረት ክስ መሥርቶ መብቱን ማረጋገጥ የሚችል መሆኑን በድንጋጌዎቹ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በዚህ ረገድ በሰ.መ.ቁ 50835 እና በሌሎችም መዛግብት በየትኛውም እርከን ላይ የሚገኙ ፍርድ ቤቶችን አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶአል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ክስ ያቀረቡበት አከራካሪ የሆነው ይዞታ አመልካች ተከራካሪ ባልሆኑበት መዝገብ ውሳኔ አግኝቶ አፈፃጸሙ ተጠናቅቆ ተጠሪ ይዞታውን በተረከቡበት ሁኔታ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት ፍርዱን ሊቃወሙ የሚችሉበት አግባብም አይኖርም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች አስቀድሞ የተሰጠው ፍርድ መብታቸውን የሚነካው ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ ከሚያቀርቡ በቀር አዲስ ክስ ማቅረብ አይችሉም በማለት የሰጠው ወሳኔ የድንጋጌውን ይዘት እና ዓላማ ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 118021 በመጋቢት 10 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ብይን፤ ይህንኑ ብይን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 270575 ግንቦት 24 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

2. **የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ አመልካች ያቀረቡትን ክስ እና ተጠሪ በጉዳዩ ላዩ የሰጡትን መልስ መሠረት በማድረግ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ በተቀመጠው የሙግት አመራር መሠረት ክርክሩን መርቶ ተገቢውን እንዲወስን በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡፡**
3. **በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡**
   - **መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሠ/መ/ቁጥር 210481
የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች ፡-አቶ መሳረክ ከድር፡- ጠበቃ፡- ፋሲል ገብሬ ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡-1.ሚ/ር ሙዋንዳ ሴሪል

2. ወ/ሮ አሰለፈች ሰኢድ

3. አቶ መሃመድ ሺበሺ -ወራሽ መሳ መሃመድ፡- ቀረቡ

4. አቶ አወል ሺበሺ፡- በሌለበት

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለአንድ ጉዳይ የወጣ ወጪ ወይም ኪሳራ ለማስከፈል ዳኝነት በተጠየቀ ጊዜ የኪሳራዉን ልክ በማስረጃ በማረጋገጥና በርትዕ የሚወሰንበትን አግባብ የሚመለከት ነዉ፡፡አመልካች በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ በመሰረቱት ክስ በሥር 1ኛ ተከሳሽ ከነበሩት ከወ/ሮ አስቱር ጉግሳ ጋር በቀን 12/01/1999ዓ/ም ባደረጉት የቤት ሽያጭ ዉል በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ ዉስጥ የሚገኘዉን ቤት

በብር 500,000.00 የሸጡላቸዉ ቢሆንም የአሁን ተጠሪዎች በቤቱ ላይ መብት አለን በማለት ባቀረቡት ክስ መነሻ የቤት ሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስ ተወስኗል፡፡አመልካች ቤቱን ለማስጠገን እና ለመገንባት ብር 1,398,000.00 ወጪ አድርጌያለሁ፡፡ስለሆነም 1ኛ ተከሳሽ የሸያጩን ገንዘብ እንዲመልሱልኝ እና ተጠሪዎች ቤቱን ለማስጠገን እና ለመገንባት ያወጣሁትን ወጪ ከነወለዱ እንዲተኩ ይወስንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ(የሥር 2ኛ ተከሳሽ) እና ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ አመልካች ቤቱን አላደሱም፡፡ወጪም አላወጡም፡፡ለግንባታ ወጪ አዉጥቻለሁ በማለት ያቀረቡት ሰነድ ሀሰተኛ ነዉ፡፡ቤቱን አድሰዋል ቢባል እንኳን ቤቱን እስካሁን እየተጠቀሙበት ስለቆዩ ሊጠይቁን አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በማቅረብ አመልካች ቤቱን ሲገለገሉ ለቆዩበት ጊዜ ኪራይ ብር 60,000.00 እንዲከፍሉ እና ቤቱን እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡የአሁን 3ኛ ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ አመልካች በቤቱ ላይ ምንም ተጨማሪ ግንባታ አላደረጉም፡፡በቤቱ ላይ ከ1999ዓ/ም ጀምሮ በተሰጠዉ እግድ ታግዶ ስለቆየ ግንባታ ያከናዉናሉ ተብሎ አይጠበቅም፡፡አመልካች ለግንባታ አወጣሁኝ ያሏቸዉ ወጪዎች የተጋነኑ፣ሀሰተኛ እና ለግንባታዉ የማያስፈልጉ ናቸዉ በማለት ተከራክረዋል፡፡ሌሎች ተጠሪዎች በመጥሪያ ተጠርተዉ ስላልቀረቡ ክርክሩ በሌሉበት ተሰምቶ እንደተወሰነ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 190914 ላይ የቀረበለትን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 16/03/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አስቀድሞ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 92681 ላይ በቀን 30/01/2009ዓ/ም በተሰጠዉ ዉሳኔ ዉሉ እንዲፈርስ ሲወሰን በዉሉ ላይ የተመለከተዉን ብር 120,000.00 የስር 1ኛ ተከሳሽ ለአመልካች እንዲመልሱና ሌላ አመልካች የከፈሉት ገንዘብ ካለና አወጣሁኝ የሚሉት ወጪ ካለ ክስ በማቅረብ መጠየቅ እንዲችሉ መብታቸዉን በጠበቀዉ መሰረት ብር 120,000 ዉሳኔ ያገኘ ሆኖ እያለ በድጋሚ አካተዉ ማቅረባቸዉ ተገቢ አይደለም በማለት ቀሪዉን ለቤቱን ሽያጭ የከፈሉትን የተቀበሉት የስር 1ኛ ተከሳሽ ናቸዉ በማለት ብር 380,000.00 የስር 1ኛ ተከሳሽ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡አመልካች በቤቱ ላይ ተጨማሪ ግንባታ ለማድረግና ለማስጠገን አወጣሁኝ ያሉት ወጪዎች እንዲተካላቸዉ የጠየቁትን በተመለከተ ለማስረዳት ያቀረቧቸዉ ማስረጃዎች አጠራጣሪ በመሆናቸዉ የማስረዳት ብቃታቸዉ ዝቅተኛ እንደሆነ፣በአንጻሩ 2ኛ ተከሳሽ ያቀረቡት ምስክሮች አመልካች ቤቱን ከገዙ በኋላ የተደረገ ተጨማሪ ግንባታ የለም በማለት የገለጹት የተሻለና አሳማኝ ነዉ፡፡ስለሆነም አመልካች ተጨማሪ ግንባታ ያደረጉ ስለመሆኑ ያላስረዱ በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ የጠየቁትን ክፍያ ተጠሪዎች የሚከፍሉበት የሕግም ሆነ የዉል ምክንያት የለም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

አመልካች በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዉ ችሎቱ በመ/ቁጥር 189243 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 26/08/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በማስረጃነት ያቀረቧቸዉን ደረሰኞች ሲመረምርና ሲመዝን 2 ሰነዶች እዉነተኛ መሆናቸዉ አጠራጣሪ ነዉ ያለ ቢሆንም ቀሪዎቹን 14 ገጽ ደረሰኞች በተመለከተ ግን ለይቶ የገለጸዉ ነገር የለም፡፡14

ሰነዶች ሀሰተኛ ናቸዉ ብሎ አልወሰነም፡፡ሁሉቱ ደረሰኞች ሀሰተኛ ናቸዉ መባሉ ሁሉም ደረሰኞች ሀሰተኛ ናቸዉ ወይም ምንም የእድሳትና ጥገና ሥራ አለተከናወነም አያስብልም፡፡አመልካች ያቀረቧቸዉ ምስክሮች በአመልካች የተከናወኑ ግንባታዎችን በዝርዝር ገልጸዋል፡፡ የተጠሪዎች ምስክሮች የመሰከሩት ቤቱ በአመልካች እጅ ከመግባቱ በፊት የነበረበትን ሁኔታ መሰረት አድርገዉ ከመመስከራቸዉ ዉጭ ቤቱ አመልካች እጅ ከገባ በኋላ የተደረገዉን ተጨማሪ ግንባታ ቤት ዉስጥ ገብተዉ ያዩ ስለመሆኑ የሰጡት ምስክርነት ቃል አያሳይም፡፡ምንም እንኳን የቤት እድሳት ለማድረግ የእድሳት ፈቃድ የሚያስፈልግ በመሆኑ አመልካች የእድሳት ፈቃድ በማስረጃነት ባያቀርቡም አመልካች በቤቱ ላይ አከናወንኩኝ እያሉ ያሉት የመኝታ ቤት የልብስ ቁምሳጥን፣ኪችን ካቢኔት፣ የመታጠቢያ፣የመጸዳጃ እና የማብሰያ ክፍሎች ዉስጥ ያሉ ሲንኮች የሚገኙበት ስለመሆኑ የክሳቸዉ ይዘት ስለሚያሳይና እነዚህ የእድሳት ፈቃድ የማፈልጉ ሆነዉ እያለ ምንም አይነት የእዳስትም ሆነ ተጨማሪ ሥራ አመልካች አላከናወኑም ከሚል ድምዳሜ ላይ የስር ፍርድ ቤት መድረሱ ስህተት ነዉ፡፡ በመሆኑም አመልካች በቤቱ ላይ ተጨማሪ ግንባታ እና ሥራ ማከናወናቸዉ ስለተረጋገጠ አመልካች ለቤቱ ባወጡት ወጪ ተጠሪዎች አለአግባብ ሊበለጽጉ ስለማይገባ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2102 ድንጋጌ መሰረት ተገቢዉን ኪሳራ በርትዕ መወሰኑ ተገቢ ይሆናል በማለት ብር 300,000.00 ከሱ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 05/11/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉም ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ቤቱን ለማደስ የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳቁሶችን የገዛሁበትን ዋጋ የሚየሳዩ 16 ገጽ ሰነዶችን በማስረጃነት አቅርቤያለሁ፡፡የስር ፍርድ ቤት 14 ሰነዶችን ያልተቀበለባቸዉን ምክንያቶች በግልጽ በማሳየት ዉድቅ አላደረገም፡፡አንድ ጉዳይ በርትዕ የሚወሰነዉ የደረሰዉ ጉዳት ወይም የታጣን ጉዳት ልክ ለመገመት ባስቸገረ ጊዜ ወይም ለመገመት በማይቻል ጊዜ ብቻ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2102 ስር ተደንግጓል፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁጥር 152417፣35034 እና በሌሎችም መዛግብት ላይ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች ያወጣሁትን ወጪ የሚያስረዱ ደረሰኞችን በማስረጃነት ዘርዝረ አቅርቤ እያለሁ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በርትዕ ሊወሰን ይገባል በማለት የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ካቀረብኳቸዉ ደረሰኞች በሁሉቱ ላይ የተጻፉ የስልክ ቁጥሮች ቤቴሌ ቋት አይገኙም የሚል ማስረጃ መቅረቡ ደረሰኞቹ እምነት እንዳይጣልባቸዉ አያደርግም፡፡ወለዱ መታሰብ የሚገባዉ አመልካች ለቤቱ እድሳት እቃዎቹን ከገዛሁበት ከ2000ዓ/ም ጀምሮ መሆን ሲገባዉ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ሕጋዊ ወለድ እንዲከፈለኝ የተሰጠዉም ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ለክርክር ምክንያት ካደረጉዋቸዉ የወጪ ደረሰኞች መካከል 14 ደረሰኞችን ባለመቀበል የወሰነበትን አግባብነት እና ወለድን አስመልክቶ የሰጠዉ ዉሳኔ ከመሰረታዊ ማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር አንጻር ተጠሪዎች ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ 4ኛ ተጠሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ በወጣ መጥሪያ ጥሪ ተደርጎላቸዉ ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸዉ

ታልፏል፡፡1ኛ ተጠሪ በቀን 02/03/2014ዓ/ም በተጻፈ መልሳቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቧቸዉ ደረሰኞች በሙሉ በተቀነባበረ መንገድ ያቀረቧቸዉ ሀሰተኛ ሰነዶች በመሆናቸዉ ዉድቅ በማድረግ መወሰናቸዉ ተገቢ ነዉ፡፡በደረሰኞቹ የተጠቀሱት የንግድ መደብሮች ዉስጥ አንድ እንኳ እዉነተኛ ነጋዴ ሊገኝ እንዳልቻለ በማስረጃ የተረጋገጠ ከመሆኑም በተጨማሪ ሥልጣን ካለዉ የመንግስት አካል እንዲጣሩልን በመግለጽ ተከራክረናል፡፡በደረሰኞቹ ላይ ቲን ቁጥርና አድራሻ አለመጠቀሱና በፍጹም የማይታወቁ ነጋዴዎች በደረሰኞቹ ላይ መጠቀሳቸዉ እንዲሁም በአገራችን ለተርን ኦቨር ታክስ የሚከፈለዉ 10% ሆኖ እያለ ደረሰኞቹ ላይ 2% እንደተከፈለ መገለጹ ደረሰኞቹ ሀሰተኛ መሆናቸዉን የሚያሳዩ ናቸዉ፡፡በደረሰኞቹ ላይ የተጠቀሱ ቁሳቁሶች ለየትኛዉ ቤት እንደተገዙ ቁሳቁሶቹ ምን ያህል እንደሆኑ አለመገለጹ ደረሰኞቹ ተቀባይነት እንዳይኖራቸዉ የሚያደርጉ ናቸዉ፡፡በመሆኑ እነዚህን ምክንያቶች መሰረት በማድረግ ደረሰኞቹን ዉድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ በመስጠታቸዉ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በተናጠል በቀን 27/11/2013ዓ/ም በተጻፈ መልሳቸዉ አመልካች በክሱ በተመለከተዉ መሰረት ለቤቱ እድሳት ወጪ ማዉጣታቸዉን የሚያሳዩ ትክክለኛ ማስረጃዎችን አቅርበዉ ማስረዳት አልቻሉም፡፡የግንባታ ፈቃድም በማስረጃነት አላቀረቡም፡፡ቤቱን ከ15ዓመታት በላይ እየተገለገሉ ስለቆዩ ወለድ ሊከፈላቸዉ አይገባም፡፡ወለድ ሊከፈላቸዉ ይገባል የሚባል ከሆነም ቤቱን ከሚያስረክቡበት ቀን ጀምሮ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም ሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ጭብጥ ከግምት በማስገባት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት አመልካች ለቤቱ ጥገና እና ግንባታ አወጣሁኝ ያሉትን ወጪዎች ተጠሪዎች እንዲተኩላቸዉ በርትዕ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም አመልካች በተጠሪዎች ላይ በመሰረቱት ክስ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ገዝተዉ የቤት ሽያጭ ዉሉ በፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲፈርስ እስከተወሰነበት ጊዜ ድረስ ቤቱ በእጃቸዉ ስለቆየ ለቤቱ ጥገና እና ግንባታ ብር 1,398,000.00 ወጪ ማድረጋቸዉን ገልጸዉ ይህንን ገንዘብ እና ለቤቱ ግዥ የከፈሉትን ብር 500,000.00 ተጠሪዎችና የስር 1ኛ ተከሳሽ ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሏቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ይህንን ለማስረዳትም ለቤቱ ጥገና እና ግንባታ አወጣሁኝ ያሉትን ወጪዎች ያስረዱልኛል ያሉትን ሰነዶችንና ምስክሮችን ማቅረባቸዉን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የአሁን 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አመልካች በቤቱ ላይ ያደረጉት ጥገና እና ግንባታ የለም፤የግንባታ ፈቃድ አዉጥተዉ የሠሩ ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የለም፤ወጪ አዉጥቻለሁ ያሉትን ለማስረዳት አመልካች ያቀረቧቸዉ ደረሰኞች ሀሰተኞች ናቸዉ በማለት ሰነዶቹን ሀሰተኛ ያሉበትን ምክንያት በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡የስር ፍርድ ቤት በሁለት ደረሰኞች ላይ የተጠቀሱ የስልክ ቁጥሮች በኢትዮ-ቴሌኮም ሰርቨር ላይ የማይገኙ መሆኑን ከተቋሙ አረጋገጫለሁ በማለት ደረሰኞቹ እምነት የማይጣልባቸዉ ናቸዉ፣በዚህ መነሻም የአመልካች ምስክሮች

የሠጡት ምስክርነትም አሳማኝ አይደለም በማለት አመልካች ለጥገና አወጣሁኝ በማለት እንዲከፈዉ የጠየቀዉን ተጠሪዎች ሊከፍሉ አይገባም በማለት ወድቅ በማድረግ ወስኗል። ይግባኝ ሰሚዉ ደግሞ የስር ፍርድ ቤት ሁለቱ ደረሰኞች ትክክለኛ ስለመሆናቸዉ በመጠራጠሩ ብቻ ሌሎች 14 ደረሰኞችንና የአመልካች ምስክሮች የሰጡትን ምስክርነት ቃል ዉድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም በማለት ተጠሪዎች አመልካች ለቤቱ ጥገና እና እድሳት ባወጡት ወጪ አለአግባብ ልበለጽጉ አይገባም በማለት በርትዕ ብር 300,000.00 ክሱ ከቀረበበት ቀን ጀምሪ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፈላቸዉ ወስኗል።አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም መስረጃ አቅርቤ እያለሁ በርትዕ መወሰኑ እና ወለድ ወጪዉን ካወጣሁበት ዓመት ጀምሮ እንዲታሰብ አለመወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ በማለት ነዉ።

አመልካች አስጠገኛለሁ እንዲሁም ተጨማሪ ግንባታ አከናዉኛለሁ ያሉትን ቤት ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር በፈጸሙት ዉል በግዥ እንዳገኙ እና ይህ ዉል በፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲፈርስ መደረጉን የግራ ቀኙ ክርክርና የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ያሳያል። ዉሉ እንዲፈርስ በተሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች በቤቱ ላይ ያወጡት ወጪ ካለ ክስ በማቅረብ መጠየቅ እንዲችሉ መብት የተጠበቀላቸዉ መሆኑን ግራ ቀኙ አልተካካዱም። በመሆኑም በአመልካችና በአሁኖቹ ተጠሪዎች መካከል ያለዉ ግንኙነት ከዉል ዉጭ የሆነ ግንኙነት ሲሆን አመልካች ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ያደረጉት ዉል በፍርድ ስለፈረሰ እና አመልካች ክስ በማቅረብ መጠየቅ እንዲችሉ መብት የተጠበቀላቸዉ አመልካች በቤቱ ላይ ባደረጉት ማሻሻያ ተጠሪዎች አለአግባብ እንዳይበለጽጉ በሚል በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ መሰጠት ያለበት ከዉል ዉጭ የሆነ ኃላፊነትን እና ስለካሳ አወሳሰን በፍ/ብ/ሕግ የተደነገገዉን ጭምር መሰረት በማድረግ ሊሆን ይገባል።

አንድን ፍሬ ነገር ማስረጃ አቅርቦ የማስረዳት ሸክምን ከሚመለከተዉ መሠረታዊዉ መርህ (Basic Principle of Burden of Proof) መረዳት እንደሚቻለዉ አንድ አከራካሪ ፍሬ ነገር አለ ወይም የለም ብሎ የሚከራከር ተከራካሪ ወገን ፍሬ ነገሩ መኖሩን ወይም አለመኖሩን ተገቢዉንና ሕጉ በተለየ ሁኔታ የሚጠይቀዉ ማስረጃ ካለም በሕግ ተቀባይነት ያለዉ ነዉ የተባለዉን ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ሸክም(ግዴታ) አለበት (የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 258-260 እና የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2001 ይመለከታል)።

በያዝነዉ ጉዳይ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ማስጠገናቸዉንና ተጨማሪ ግንባታ ማድረጋቸዉን ለዚህም ብር 1,398,000.00 ወጪ ማድረጋቸዉን ፍርድ ቤትን ሊያሳምን የሚችል ተገቢዉን ማስረጃ ማስረዳት ይኖርባቸዋል።ከላይ እንደተመለከተዉ አመልካች ተጠሪዎች እንዲተኩላቸዉ እንዲወሰን ዳኝነት የጠየቁት ገንዘብ ለቤቱ ጥገና እና ለቤቱ ተጨማሪ ግንባታ አወጣሁኝ ያሉት ወጪ (ኪሳራ) መሆኑ ግልጽ ነዉ። እንደሚታወቀዉ የጉዳት ካሳ(ኪሳራ) የሚከፈልበት ዓላማ ጉዳት የደረሰበትን ተበዳይ (ነገር) ጉዳት ከመድረሱ በፊት ወደ ነበረበት ስፍራ ለመመለስ እንጂ ተጎጂዉ ከጉዳቱ እንዲያተርፍ ለማድረግ አይደለም። ወደዚህ አጠቃላይ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ተቀባይነት ያለዉ የካሳ አከፋፈል መሠረታዊ መርህ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2090/1 እና 2091 ላይ ተደንግጓል።የኾዉም በአንድ ጉዳት ምክንያት የሚከፈለዉ ካሳ ከደረሰዉ ጉዳት(በተያዘዉ ጉዳይ ከወጣዉ ወጪ) ጋር እኩል ሆኖ የሚመዛዘን መሆን እንዳለበት በሌላ

አነጋገር ተጠሪዎች እንዲከፍሉ መወሰን ያለበት አመልካች ለቤቱ ጥገና እና ተጨማሪ ግንባታ ካወጡት ወጪ ጋር እኩል ሆኖ መመዛዘን እንዳለበት የሚያስገድድ ነዉ፡፡ይህንን መርህ በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ የጉዳት ካሳ ጠያቂዉ ከጉዳቱ አትራፊ እንዳይሆን እና ከሚገባዉ ያነሰ እንዳይከፈለዉ ያደርጋል፡፡ ይህ መርህ በአግባቡ ገቢራዊ ይሆን ዘንድ በተቻለ መጠን የኪሳራዉን አይነት እና መጠን በማስረጃ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ጉዳት ስለመድረሱ ምክንያታዊ የሆነ እርግጠኝነት ሲኖር እና የካሳውን መጠን ለመወሰን አስቸጋሪ ሲሆን ዳኞች በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102/1 መሰረት የካሳውን መጠን ፍትህንና ርትዕን መሰረት በማድረግ መወሰን እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ባቀረቡት ክስ ዳኝነት የጠየቁት ለቤቱ ጥገና እና አከናዉኖለሁ ያሉትን ግንባታ ለመፈጸም አወጣሁኝ ያሉትን ወጪ ባቀረቡት የሰነድና የምስክሮች ቃል ተረጋግጦ እንዲወሰንላቸዉ ነዉ፡፡በእርግጥ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለአመልካች የጉዳት ካሳ አልወሰነም፡፡ለመጀመሪያ ጊዜ ካሳ የወሰነዉ የዚህ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንደመሆኑ ካሳ ሲወስን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2153 ላይ የተደነገጉትን ሁኔታዎች ከግምት አስገብቶ መወሰን ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም በመርህ ደረጃ ለቤቱ ጥገና እና አከናወንኩኝ ያሉትን ግንባታ ለመፈጸም ያወጡትን ወጪ በተመለከተ የተሠሩ ሥራዎች ምን እንደሆኑ፣ የተገዙ እቃዎች ምን እንደሆኑ፣በምን ያህል ገንዘብ እንደተገዙ እና የተገዙትም እቃዎች በእርግጥ ለዚህ ቤት የዋለ መሆን አለመሆኑ በማስረጃ በማስረዳት ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ጉዳቱ መድረሱ ተረጋግጦ የካሳዉን መጠን(የኪሳራዉን ልክ) በማስረጃ ለማረጋገጥ ባለመቻሉ በርትዕ ሲወሰን ወይም የጥገና እና የተጨማሪ ግንባታ ሥራ መሰራቱ ተረጋግጦ ለዚህ የወጣዉን ወጪ በትክክል በማስረጃ ማረጋገጥ ባለመቻሉ በርትዕ የሚወሰን ከሆነም አንዱ በሌላዉ ሀብት አለአግባብ እንዳይበለጽግ ወይም መካስ የለበት ከእነአካተዉ ሳይካስ እንዳይቀር ወይም መካስ ባለበት ልክ ሳይካስ እንዳይቀር የነገሮቹን ተራ ሁኔታዎችን በማመዛዘን ሊወሰን ይገባል እንጂ እንዲሁ በደፈናዉ በርትዕ በሚል ሊወሰን አይገባም፡፡

እንዲሁም ከላይ እንደተገለጸዉ አመልካች ማስረጃ አቅርበዉ በቤቱ ላይ ጥገና እና ተጨማሪ ግንባታ በማከናወን በክሱ የተገለጸዉን ወጪ ማዉጣታቸዉን እስከገለጹ ድረስ የማስረዳት ሸክማቸዉን መወጣት ያለባቸዉ ትክክለኛ ማስረጃ በማቅረብ ጭምር ነዉ፡፡ በመሆኑም አመልካች ለቤቱ ጥገና እና ግንባታ ማከናወናቸዉንና አወጣሁኝ ያሏቸዉን ወጪዎች በእርግጥም ያወጡ ስለመሆኑ እዉነተኛ ማስረጃዎችን በማቅረብ ማስረዳት ይኖርባቸዋል፡፡ፍርድ ቤቶችም አመልካች እነዚህን ፍሬ ነገሮች ለማስረዳት ያቀረቧቸዉን ማስረጃዎች ተጠሪዎችም በቤቱ ላይ የተደረገ ጥገናም ሆነ ተጨማሪ ግንባታ የለም ሰነዶቹም ሀሰተኛ ናቸዉ በማለት ያሰሙትን ክርክርና ክርክራቸዉን ለማስረዳት ያቀረቡትን እያንዳንዱን ማስረጃዎች በየፈርጃቸዉ መርምረዉ ትክክለኛነታቸዉን ማረጋገጥና ትክክለኛ አይደሉም(ሀሰተኛ ናቸዉ) የሚሉ ከሆነም ይህንን ያሉበትን ምክንያት በመግለጽ መወሰን ይኖርባቸዋል፡፡ከዚህ አኳያ የስር ፍርድ ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት አመልካች በማስረጃነት ካቀረቧቸዉ ደረሰኞች 14ቱን ደረሰኞች ተጠሪዎች ካቀረቡት ክርክር አንጻር በመመርመርና ከሚመለከታቸዉ የመንግስት አካላት እና ለአብነት በደረሰኞቹ ላይ የተጠቀሱ ሻጮች

በነጋዴነት የሚታወቁ መሆን አለመሆናቸውንና ደረሰኞቹም ከእነሱ የተሰጡ መሆን አለመሆኑን ከነጋዴዎቹ ተገቢውን ማጣራት አድርገዉ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት ቢኖርበትም ይህንን አላደረገም፡፡

በተጨማሪም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የተወሰኑ ሥራዎች ማለትም የመኝታ ቤት የልብስ ቁምሳጥን፣ ኪችን ካቢኔት፣የመታጠቢያ፣የመጸዳጃ እና የማብሰያ ክፍሎች ዉስጥ ሲንኮች የተሰሩ/ የተገጠሙ/ሥራዎች መኖራቸውን ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃዎች አረጋግጧል፡፡ ሆኖም የስር ፍርድ ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ከእነዚህ ሥራዎች ዉጭ በቤቱ ላይ የተደረገ ጥገና እና ተጨማሪ ግንባታ መኖሩ በማስረጃ የሚረጋገጥ ቢሆንና ለጥገናዉና ለግንባታዉ የወጣዉን ትክክለኛ ወጪ ለማረጋገጥ ካልተቻለ እንዲሁም በደረሰኞቹ ላይ በተመለከተዉ መሰረት ተገዙ የተባሉ እቃዎች በእርግጥም ለቤቱ ጥገና እና ተጨማሪ ግንባታ ጥቅም ላይ መዋል አለመዋላቸዉን የግራ ቀኙ ምስክሮች ከመሰከሩት ቃልና ከሰነድ ማስረጃዎች አንጸር መመርመርና አስፈላጊ ከሆነም ግምታዊ ወጪ ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል በባለሙያ እንዲረጋገጥ አድርገዉ መወሰን ሲገባቸዉ በዚህ አግባብ አጣርተዉ አለመወሰናቸዉ የክርክር አመራር ጉድለት እንዳለበት የሚያሳይ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል ከላይ ከተመለከተዉ አንጻር ሲታይ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለጥገና እና ለተጨማሪ ግንባታ አወጣሁኝ ያሉትን ወጪዎች ለማስረዳት ካቀረቡት ደረሰኞች ዉስጥ በሁለት ደረሰኞች ላይ የታየዉን ጉድለት ወይም እምነት እንዳይጣልባቸዉ የሚያደርግ ምክንያት በማግኘቱ ብቻ ቀሪዎቹም አመልካች በማስረጃነት ያቀረቧቸዉ 14 ደረሰኞች እና የአመልካች ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት ቃል ተመሳሳይ ጉድለት እንዳለባቸዉ ድምዳሜ ላይ በመድረስ አመልካች ከዚህ አንጻር የጠየቁትን ዳኝነት ዉድቅ ያደረገዉ በግምት ላይ በመመስረት በመሆኑ ተቀባይነት ያለዉን የማስረጃ አቀባበልና የማስረጃ ምዘና መርሆዎችን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ በተጨማሪም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የስር ፍርድ ቤት አመልካች በማስረጃነት ያቀረቡትን 14 ደረሰኞች ምክንያት ሳይሰጥ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የደረሰዉ ድምዳሜ እኛም የምንቀበለዉ ቢሆንም ራሱም ማስረጃዎቹ ተቀባይነት የሚያገኙበትንና የማያገኙበትን ምክንያት በግልጽ በዉሳኔዉ ላይ ሳያሰፍር በዝምታ ማለፉ የማስረጃ ምዘና መርህን የተከተለ አይደለም፡፡ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት አመልካች ያወጣሁትን ወጪ በማስረጃ አስረዳለሁ እያሉ በርትዕ ብር 300,000.00 ተጠሪዎች እንዲከፍሉ የወሰነበት አግባብ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2102/1 ስር በርትዕ ካሳ ለመወሰን ከግምት ሊገቡ የሚገባቸዉ ናቸዉ ተብለዉ የተደነገጉትን ሁኔታዎች ያላገናዘበ ከመሆኑም በላይ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2090 እና 2091 ስር ለተጎጂዉ የሚከፈለዉ ካሳ(ኪሳራ) ከደረሰዉ ጉዳት(አመልካች ካወጡት ወጪ) ጋር እኩል ሆኖ መመዛዘን አለበት የሚለዉን መሰረታዊ መርህ የሚጥስ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ አተገባበር ጉድለት ያለበት ነዉ፡፡በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 190914 ላይ በቀን 16/03/2012ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 189243 ላይ በቀን 26/08/2013ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሻሽለዋል፡፡

2. የስር ፍርድ ቤት የስር 1ኛ ተከሳሽ ላይ የሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡ሁለቱም ፍርድ ቤቶች አመልካች ለቤቱ ጥገና እና ተጨመሪ ግንባታ አወጣሁኝ በማለት እንዲከፈላቸዉ እንዲወሰንላቸዉ የጠየቁትን ዳኝነት በተመለከተ የሰጡት ዉሳኔ ክፍል ተሸሯል፡፡

3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርዱ ሐተታ ላይ በተመለከተዉ መሰረት አመልካች መስራታቸዉን ይግባኝ ሰሚ ችሎት ካረጋገጠዉ ዉጭ በክሱ የተጠቀሰዉን ቤት ያስጠገኑና ተጨማሪ ግንባታ ያከናወኑ መሆን አለመሆኑን፣ ጥገና እና ተጨማሪ ግንባታ ተከናዉኖ ከሆነ ለዚህ የተገዙ እቃዎች አይነት፣ ብዛትና የተገዙበትን ዋጋ እና ተያያዥ ወጭዎችን ለማስረዳት አመልካች ያቀረቡት ደረሰኞች ትክክለኛ መሆን አለመሆናቸዉን እንዲሁም እቃዎቹ ለቤቱ ጥገና እና ግንባታ መዋል አለመዋላቸዉን ከላይ በፍርድ ሀተታ ላይ በተመለከተዉ አግባብ አጣርቶ፣ በባለሙያ ምስክርነት ሊረጋገጥ የሚገባዉንም እንደዚሁ ትእዛዝ ሰጥቶ እንዲጣራ በማድረግ፣ እንዲሁም አስቀድሞ የሰማቸዉንና ያስቀረባቸዉን ማስረጃዎች ጭምር ከላይ በፍርድ ሀተታ ላይ ከተመለከተዉ አንጻር መርምሮና መዝኖ የሕግን መሠረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት መልሰንለታል፡፡

4. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የመ.ቁ.210520
ህዳር 27/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ አቶ ቃሲም እድሪስ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡ አቶ አብዱርሃማን ተማም- ጠበቃ አቶ ጌታቸው ማሞ-ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የከተማ ይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአሁን ተጠሪ በአመልካች እና በሌላ አንድ ግለሰብ ላይ በሲናና ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ጭብጥም ቦታና አዋሳኙ በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተገለፀውን 200 ካሬ ሜትር ይዞታ በ1998 ዓ.ም በህጋዊ መንገድ ተሰጥቷቸው በእጃቸው አድርገው የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወስደዉበት እና ግብር እየገበሩበት እያለ አመልካች እና ሌላኛው ግለሰብ ከይዞታው ላይ ምንም መብት ሳይነራቸው በላዩ ላይ የነበረውን አጥር በማፍረስ ቤት ሰርተዉበት የያዙባቸው መሆኑን በመግለፅ ድርጊቱ ህገ ወጥ ነው ተብሎ በይዞታው ላይ የሰሩትን ቤት አፍርሰው ይዞታውን እንዲለቁላቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት የአሁን አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና አማራጭ የስረ ነገር ክርክር አቅርበው መቃወሚያው በብይን ውድቅ ተደርጓል፡፡ የአማራጭ የስረ ነገር ክርክሩ ይዘትም ለክሱ መሰረት የሆነው ይዞታ ከመንግስት አካል በህጋዊ መንገድ በሰነድ ተረጋግጦ የተሰጠኝ ይዞታዬ በመሆኑ ተጠሪ ከይዞታው ላይ መብት የላቸውም የሚል ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን በመስማት እንዲሁም ስለይዞታው ከክፍለ ይዞታ አስተዳደር ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ክስ የቀረበበትን ይዞታ የአሁን ተጠሪ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ የለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የአሁን ተጠሪን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህግ ቁጥር 337 መሰረት ዘግቷል፡፡ ተጠሪ ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለሁለተኛ ጊዜ የይግባኝ አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኝን የይግባኝ ክርክር ከሰማ እና ስለ ይዞታው በድጋሚ ከዞን እና ከወረዳው መሬት አስተዳደር በተወጣጡ ባለሙዎች በጋራ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ክሰ የቀረበበት ይዞታ በ1998 ዓ.ም ለአሁን ተጠሪ በህጋዊ መንገድ ተሰጥቷቸው በዚሁ ይዞታ ላይ በ2002 ዓ.ም የይዞታ ማረጋጋጫ ምስክር ወረቀት የተሰጣቸው መሆኑን፤ ተጠሪ በዚሁ ይዞታ ላይ ከ1999 እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ በስማቸው ግብር ሲገብሩበት የነበረ ስለመሆኑ በወረዳው ፍርድ ቤትም ሆነ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የቀረበው የክፍለ መሬት አስተዳደር መግላጫ የሚያረጋግጥ መሆኑን፤ በስር ፍርድ ቤት ቀርበው የተሰሙት የተጠሪ የሰው ምክስሮችም ይህንኑ ፍሬ ነገር ያረጋገጡ መሆኑን፤ ከዚህ አንጸፃር በይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃው ላይ የየዞታው አዋሳኝ አለመጠቀሱ የሰነዱን ህጋዊነት የሚያሳጣ አለመሆኑን፤ በሌላ በኩል ይኸው ይዞታ በ2007 ዓ.ም ለአሁን አመልካች ቀድሞ በነበራቸው 200 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ ተጨምሮ በአጠቃላይ በ400 ካሬ ሜትር ይዞታ በሊዝ ውል የተሰጣቸው ስለመሆኑ ከክፍለ መሬት አስተዳደር የተሰጡት ልዩ ልዩ ማስረጃዎች የሚያሳዩ መሆኑን፤ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያሰሟቸው የሰው ምስክሮች ይዞታው በሊዝ ውል የተሰጣቸው ስለሆኑ ያረጋገጡ መሆኑን፤ ከቀረበው ክርክር እና ማስረጃ አኳያ የግራ ቀኙ መብት የሚለየው በማስረጃ ምዘና መሆኑን፤ በዚሁ አግባብ የቀረቡትን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች በተናጠል መዝኖ የተቀበለበትን እና ያልተቀበለበትን ምክንያት ካሰፈረ በኋላ የአሁን ተጠሪ ክስ በቀረበበት ይዞታ ላይ በህግ አግባብ የተሰጣቸው የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እያለ ይዞታው ለአሁን አመልካች የተሰጠበት መንገድ ህግና ስርዓትን ባልጠበቀ መንገድ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር አመልካች በይዞታው ላይ የሰሩትን ቤት በራሳቸው ወጪ አፍርሰው ይዞታውን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

አመልካች በተራቸው ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩ የማስረጃ ምዘናን የሚመለከት ነው በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የይግባኝ ሰሚ ችሎቱን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሐምሌ 05/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነውን ይዞታ አመልካች ከሚመለከተው አካል ጋር በተደረገ የሊዝ ውል የተረከቡ መሆኑ፣ የግንባታ ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑ እንዲሁም ለተጠሪ የተሰጣቸው ማስረጃ የመሬቱን ልዩ ቦታ ስም የማያሳይ ስለመሆኑ የመንግስት አካል በማጣራት ያሳለፈውን ውሳኔ ስር ፍ/ቤት የሻረበትን አግባብነት ከመሰረታዊ የክርክር አመራር እና ከማስረጃ ምዘና መርህ አኳያ ለማጣራት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ማስቀረቢያ ነጥብ አኳያ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በመሰረቱ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የፌዴራልም ሆነ የክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን የሚመነጨው ከፌደራሉ ህገ መንግስት ስለመሆኑ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 78 ይደነግጋል፡፡ በህገ መንግስት አንቀፅ 80(3) መሰረት በፌደራልም ሆነ በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስር ለሚቋቋም የሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ውስጥ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞ ሲገኝ በሰበር አይቶ የማረም ስልጣን ነው፡፡ ህገ መንግስቱን መሰረት አድርገው በፌደራልም ሆነ በየክልሉ የታወጁት የፍርድ ቤት ማቋቋሚያ አዋጆችም በህግ መንግስቱ በተገለፀው አግባብ ተመሳሳይ የዳኝነት ስልጣን ለሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡ ለመሆኑ ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10 ድንጋጌ እንዲሁም አሁን ለቀረበው ጉዳይ አግባብነት ካለው ከተሻሻለው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ 216/2011 አንቀጽ 26(1) ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በፌዴራልም ሆነ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስር የተቋቋመው የሰበር ሰሚ ችሎት በህግ መንግስቱ እና ህገ መንግስቱን ተከትለው በወጡ አዋጆች የተሰጣቸው የሰበር ሰሚነት ስልጣን ተግባራዊ ሲያደርጉ ፍሬ ነገርን በተመለከተ በዋናነት መነሻ የሚያደርጉት ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ነው፡፡ እናም የሰበር ችሎት ቀዳሚ ተግባር የሚሆነው የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ በማስረጃ የተረጋገጠውን መሰረት በማድረግ በሰጡት የህግ ትርጉም ውስጥ የፈፀሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት ካለ ለይቶ በህግ አግባብ ማረም ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍርድ ቤት ተመዝኖ አቋም የተያዘበትን ጉዳይ በተመለከተ በራሱ ማስረጃውን መዝኖ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችለው የህግ አግባብ የለም፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ የሻረው በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጡትን እንዲሁም በራሱ ማጣሪያ ትዕዛዝ ያረጋገጣቸውን ፍሬ ነገሮች መሰረት በማድረግ ባከናወነው የማስረጃ ምዘና ስለመሆኑ በፍርድ ሀተታው ላይ በግልፅ አስፍሯል፡፡ ይህ ፍርድ ቤቱ የደረሰበት ድምዳሜ በዚህ ችሎት ሊለወጥ የሚችለው ፍርድ ቤቱ በማስረጃ ምዘና ረገድ የፈፀመው ስህተት ከተገኘ ብቻ ስለመሆኑ ከላይ ስለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የዳኝነት ስልጣን ከሚዘረዝሩት ህግጋት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከማስረጃ ምዘና አንፃር የስር ፍርድ ቤት የፈፀመው የምዘና መርህ ጥሰት ስለመኖሩ የቀረበው የአመልካች የሰበር አቤቱታ የሚገልፀው ነገር የለም፡፡ ይህ ችሎትም ባደረገው ምርመራ በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት የማይቻል በመሆኑ የአመልካች መከራከሪያ ውድቅ ተደርጎ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/375991 ላይ ሰኔ 29/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ፅ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡210525

ቀን፡-30/03/2014ዓ/ም

ዳኞች፡-ሰለሞን አረዳ

እትመት አሰፋ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ዶ/ር ሙሉጌታ በካሎ

ተጠሪዎች፡-1ኛ. አቶ አማኑኤል ዮካሞ

2ኛ. ወ/ሮ ወሰን ጋዲዮ

3ኛ. ወ/ሮ መሰለች ዳንባራ

4ኛ.አቶ አየለ ጋዲዮ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሀምሌ 05 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የግራ ቀኙን የአፈጻጸም ክርክር አስመልክቶ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት መሆኑን ገልፀው በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ባቀረቡት ማመልከቻ መነሻነት ሲሆን አመልካች በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአፈፃፀም ከሳሽ የነበሩ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ የአፈፃፀም ተከሳሽ፣ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በመቃወም አመልካቾች ነበሩ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የጉዳዩ አመጣጥ እንዲህ ነው፡-አመልካችና 1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት እያደረጉ ያሉትን የአፈፃፀም ክርክር አስመልክቶ አመልካች ለፍርዱ ማስፈፀሚያ እንዲሆን የ1ኛ ተጠሪ ንብረት እንደሆነ በመግለፅ ያቀረቡትን በአለታ ጩኮ ወረዳ 01 ቀበሌ የሚገኘውን በ1ኛ ተጠሪ ስም የሚታወቀውን ቤት ማዘጋጃ ቤቱ የቤቱን ግምት አውጥቶ እንዲልክ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቶ ግምቱን ልኮ ግራ ቀኙ አስተያየታቸውን የሰጡ ሲሆን በዚህ እለትም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.418 አቤቱታ 3ኛ ተጠሪ የሚች ጋዲሶ ቃቂዮ ሚስት 4ኛ ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸውን እንዳረጋገጡ ገልፀው አከራካሪውን ቤት ግንቦት 07 ቀን 1985 ዓም በተደረገ ውል ከአቶ አማሎ ሂክሶ እና ወ/ሮ አስቴር አረፋይኔ ገዝተው ቤቱን እየኖሩ እንዲጠብቁ ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ሰጥተዋቸው እያለ በድብቅ ስም ለማዞር ሙከራ እያደረጉ መሆኑንና በስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለአፈጻጸም ሂደቱ መገመቱን እንደሰሙ ማዘጋጃ ቤቱን ጨምሮ በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ ክስ አቅርበው በክርክር ላይ መሆናቸውን ገልፀው በቤቱ ላይ የወጣው የሃራጅ ሽያጭ ሂደት እንዲታገድ ብፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.418(4) እንዲሁም በቤቱ ላይ የተሰጠው የመያዣ ትዕዛዝ እንዲነሳ ጠይቀዋል፡፡

አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ለዚህ አቤቱታ ምላሻቸውን ያቀረቡ ሲሆን ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ በቤቱ ላይ የነበረው የይግባኝል ክርክር ውሳኔ ማግኘቱን ገልፀው 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ስላመለከቱ ውሳኔው ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ በማድረግ ፍርድ ቤቱ የቀረበውን ውሳኔ ከግራ ቀኙ ክርክር ጋር በመመርመር በሰጠው ብይንም 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችን ጨምሮ በሶስት ተከሳሾች ላይ በአለታ ጩኮ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00942 ያቀረቡት ክስ ተመርምሮ ህዳር 04 ቀን 2013 ዓም በተሰጠው ውሳኔ አከራካሪው ቤት የ1ኛ ተጠሪ ሳይሆን የ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን ይህ ውሳኔ ተጠሪዎች በመመሳጠር ያሰጡት ነው በማለት አመልካች የተከራከሩ ቢሆንም ውሳኔውን በይግባኝ ያላሻሩት ፀንቶ ያለ ውሳኔ መሆኑን በመጥቀስ በቤቱ ላይ ተላልፎ የነበረው እግድ እንዲነሳ ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ብይን ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለሲዳማ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው የነበረ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠው ውሳኔም የስር ፍርድ ቤትን ብይን ያፀና ሲሆን የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም አመልካች የውጪ ሀገር ዜጋ በመሆናቸው አከራካሪውን የአፈፃፀም ክርክር ከፍተኛ ፍርድ ቤቱና ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ያዩት ባላቸው የውክልና ስልጣን መሆኑን በመጥቀስ በፌደራል ጉዳይ ላይ ጉዳዩን በሰበር የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም በዋናው ክርክር ወቅት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት ለማሸሽ እና ስም ለማዛወር ሲንቀሳቀሱ አመልክቼ የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቤቱ በ1ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበና የሚገበርበት መሆኑን አረጋግጦ አግዶ ካቆየ በኋላ ተጠሪዎች ያላቸውን ዝምድና በመጠቀም ንብረት ለማሸሽ ሀሰተኛ የመንደር ውል በማቅረብ ያቀረቡትን

ክስ ተቀብሎ የተሰጠውን ኢ-ፍትሀዊ ውሳኔ በመቀበል ቤቱ የ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ለመሆኑ አንዳችም ማስረጃ ሳይቀርብለት ፣የግዢ ውል ነው የተባለው የመንደር ውል በፍ/ብ/ህ/ቁ.1723 ያልፀደቀ ሆኖ እያለ የመንደር ውልን በመቀበል የተሰጡትን ውሳኔዎች በመቀበል የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት መደምደሚያ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተሽሮ ቤቱ ተሽጦ ለፍርድ ማስፈፀሚያ እንዲውል ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ፍርድ ባረፈበት ቤት ላይ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎችን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.418 አስገብቶ ለተጠሪዎች የወሰነበትን አግባብ ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪዎች በህጉ አግባብ ተጠርተው ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በሰጡት መልስም 2ኛ ተጠሪ በዋናው ክርክርም ሆነ በአፈፃፀም ክርክሩ ሳልካተት በሰበር ክርክሩ በ2ኛ ተጠሪነት ተካትቼ መቅረቤ አግባብ ባለመሆኑ ከሰበር ክርክሩ ውጪ እንድሆን ይወሰንልኝ፣አከራካሪው ቤት ቤተሰቦቻችን በአደራ እንድንጠብቅላቸው የሰጡን የቤተሰቦቻችን ቤት በመሆኑ፣በቤቱ ውስጥ በጠባቂነት መኖራችን ብቻ ባለቤት የሚያደርገን ባለመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በሰጡት መልስም የሰበር አቤቱታው የቀረበው በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁ.76684 ታህሳስ 16 ቀን 2013 ዓም ከተሰጠ ከ6 ወር ከ20 ቀን በኋላ ሀምሌ 05 ቀን 2013 ዓም በመሆኑ በህጉ የተመለከተው የ90 ቀናት የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ከሰበር አቤቱታው አቀራረብ ጋር በተያያዘ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጡት መልስም አከራካሪው ቤት ላይ ፍርድ እንዳረፈበት ተደርጎ የማስቀረቢያ ጭብጥ መያዙ አግባብ አይደለም፣3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በመ/ቁ.00942 በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እና በማዘጋጃ ቤቱ ላይ ባቀረብነው ክስ አከራካሪው ቤት ላይ በአሻጥር የሚያደርጉት ክርክር እንዲቆምና ቤቱ በ3ኛ ተጠሪ ስም እንዲዞርና 4ኛ ተጠሪ የወራሽነት ድርሻቸውን እንዲያገኙ የተወሰነ በመሆኑ እና ውሳኔው ጸንቶ ያለ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ይህንን ውሳኔ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሰጡት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አከራካሪው ቤት ለ1ኛ ተጠሪ የፍርድ እዳ ሊውል የሚችል የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ንብረት ነው? ወይስ የ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ንብረት? ውጤቱስ ምን ሊሆን ይገባል? የሚሉትን ጭብጦች በመመስረት የግራ ቀኙን የሰበር ክርክር ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክር አንፃር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡በኢፌዲሪ ህግ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ) እና በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10(1) እንደተመለከተው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ውስጥ

መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞ ሲገኝ በሰበር አይቶ የማረም ነው፡፡በዚህ አግባብም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ሰሚነት ስልጣኑን ተግባራዊ ሲያደርግ ፍሬ ነገርን በተመለከተ በዋነኝነት መነሻ የሚያደርገው ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን በአከራካሪው ቤት ላይ አፈፃፀሙ ይቀጥልልኝ ክርክር ውድቅ በማድረግ በአከራካሪው ቤት ላይ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ ብይን የሠጠውና ይህ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የሲዳማ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፀናው ማስረጃን የመስማት የመመርመርና የመመዘን ስልጣናቸውን ተጠቅመው የቀረቡትን ማስረጃዎች በመመርመርና በመመዘን በዋነኝነትም በአለታ ጩኮ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.00942 ህዳር 04 ቀን 2013 ዓም በተሰጠው ውሳኔ በአለታ ጩኮ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኘውን አከራካሪውን ቤት አቶ ጋዲዮ ቃቂሶ በውል ገዝተው ያገኙት ሆኖ እያለ በስር ፍርድ ቤት የፍርድ ባለዕዳ የነበሩት 1ኛ ተጠሪና በመ/ቁ.00942 2ኛ ተከሳሽ የነበሩት 2ኛ ተጠሪ አላግባብ ስሙን ማዛወራቸውን በማረጋገጥ አከራካሪውን ቤት ለ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች እንዲመልሱላቸው መወሰኑንና ይህ ውሳኔ ፀንቶ የሚገኝ መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡ይህ በ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች አመልካችነት ክርክር ተደርጎበት የተሰጠው ውሳኔ አመልካች አፈፃፀሙ ሊቀጥልበት ይገባል በማለት የሚጠቀሱት ቤት የ1ኛ ተጠሪ አለመሆኑ በፍርድ የተረጋገጠ መሆኑን ያሳያል፡፡

ይህ የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን የመስማት፤የመመርመርና የመመዘን ስልጣናቸውን ተጠቅመው የደረሱበት ድምዳሜ በዚህ ችሎት ሊለወጥ የሚችለው የስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ምዘና ረገድ የፈፀሙት ስህተት ከተገኘ ብቻ ሲሆን ይህ ችሎት ባደረገው ምርመራ በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት አልተገኘም ፤ በዚህ አግባብም በስር የሀዋሳ ከተማ ከ/ፍ/ቤት እና የሲዳማ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በሰጡት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት የማይቻል በመሆኑ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 26825 በቀን 20/05/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይንና እና ይህንን ብይን በማፅናት የሲዳማ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 76684 ታህሳስ 16 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ሀምሌ 06 ቀን 2013 ዓም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሂ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 210711
ሕዳር 30 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ተስፋዬ አዱኛ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አየሉ ታደሰ

2. ታሪኩ ታደሰ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 23/10/ 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 80590 በቀን 16/03/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 258188 ሚያዝያ 06 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የከተማን ይዞታ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ቁጥሩ 123(ሐ) የሆነው ቤት ባለይዞታ መሆናቸውን፤ 2ኛው ተጠሪ ይህንኑ ቤት አስመልክቶ በመ.ቁ 71430 አቅርበውት የነበረው ክስ ውድቅ ሆኖባቸው ሳለ በሌላ መዝገብ ባስወሰኑት ውሳኔ መነሻነት አፈጻጸም ከፍተው የሚመለከታቸውን አካለት በማሳሳት ቤቱን በአፈጻጸም የተረከቡት መሆኑን በመግለጽ ክስ የቀረበበትን ቤት መልሰው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እንዲያስረክቡአቸው እና ለ10 ወራት ቤቱን አከራይተው ያገኙትን ብር 17,500 / አስራ ሰባት ሺህ አምስት መቶ / እንዲከፍሏቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን ነው።

የአሁን ተጠሪዎች በሰጡት መልስ ክሱ በድጋሚ የቀረበ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ በሰጡት መልስ ደግሞ አመልካች ከአውራሻችን አንድ ክፍል ቤት ተከራይተው ኪራይ ሲከፍሉ ቆይተው አውራሻችን በሞት ሲለዩ በወቅቱ የመብራት ለመክፈል ከአቅም በላይ ሆኖብን ሲቆረጥ በስማቸው መብራት አስገብተዋል፤ አከራካሪው ቤት የአባታችን የውርስ ሀብት ነው፤ አመልካች ቤቱ ይገባኛል ከማለት በቀር በምን አግባብ ቤቱን እንዳገኙት ለማሳየት ያቀረቡት ማስረጃ የለም፤ አመልካች በአፈጻጸም መዝገብ አቤቱታ አቅርበው ውደቅ ተደርጎባቸዋል፤ ተጠሪዎች ቤቱን የተረከብነው አስፈጻሚ አካላትን አታለን ሳይሆን በውሳኔው መሠረት እንዲፈጸም በመ.ቁ 123407 በተሰጠ ትዕዛዝ መሠረት ነው፤ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል በሰጠው ምላሽ በግቢው ውስጥ የመንግስት ቤት እንደሌለ እና በአጎራባች ቁጥር ውስጥ አመልካች የጠቀሱት የቤት ቁጥር እንደሌለ ተረጋግጧል፤ ተጠሪዎች የአመልካችን ቤት አላከራየንም፤ ስለሆነም ክሱ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን በብይን ውድቅ አድርጓል፤ በፍሬነገሩ ላይ ደግሞ ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ስለጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ እና የመ.ቁ 123407 የሆነው መዝገብ በትዕዛዝ አስቀርቦ ከተመለከተ በኋላ የቦሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 05 አስተዳደር ጽ/ቤት በቀን 06/02/2011 ዓ.ም ለቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ በተጠሪዎች አባት ይዞታ ውስጥ የምናስተዳድረው የቀበሌ ቤት ውስጥ የለም በማለት ገልጾአል፤ ተጠሪዎች በመ.ቁ 101280 በቀን 11/4/2009 ዓ.ም በተሰጠ ፍርድ በቦሌ ክፍለከተማ ወረዳ 05 የቤት ቁጥር 123 የሆነው ቤት የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ስለሆነ እኩል እንዲካፈሉ በማለት ተወስኗል፤ አመልካች የመ.ቁ 123407 በሆነው የአፈጻጸም መዝገብ አቤቱታ አቅርበው አመልካች የቤቱ ባለቤት መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረቡ እና ፍርዱ ተፈጽሞ የተጠናቀቀ በመሆኑ በቤቱ ላይ መብት አለኝ የሚሉ ከሆነ ክስ አቅርበው ከሚጠይቁ በቀር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ ተደርጎባቸዋል፤ በመ.ቁ 71430 ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በማስረጃ አልተደገፈም ተብሎ ውድቅ ከመደረጉ በቀር ለአመልካች መብት አልፈጠረም፤ ተጠቃሹ ቤት የመንግስት ቤት ካልሆነ አመልካች የግላቸው ስለመሆኑ ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፤ አመልካች ቤቱ የግላቸው ስለመሆኑ ያላስረዱ በመሆኑ ቤቱ ይመለስልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል። አመልካች ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት የይግባኝ አቤቱታውን ሰርዞታል።

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም በቀን 23/10/2013 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- 2ኛ ተጠሪ በመ.ቁ 71430 አስቀድመው አቅርበውት የነበረው ክስ ውድቅ ተደርጎባቸዋል፤ በመጀመሪያው ክስ በወረዳው ውስጥ ኗሪ መሆኔ እና ካርታ ለማውጣት በዝግጅት ላይ የነበርኩ መሆኔ

በተገለጸበት ሁኔታ ተጠሪዎች ለቤት ቁጥር 123 በከፊቱት የአፈጻጸም መዝገብ አሳስተው የተረከቡትን ቤት ለመረከብ ያቀረብኩትን ክስ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የአሁን 2ኛ ተጠሪ በመ.ቁ 71430 አመልካችን ተክሳሽ በማድረግ በመሰረተው ክስ አስተዳደሩ አመልካች በራሱ ይዞታ ውስጥ እንደሚገኝ ገልጾ 2ኛ ተጠሪ ያቀረበው ክስ በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት ተወስኖ ሳለ 2ኛ ተጠሪ ይህን ውሳኔ ሳያሻር በአፈጻጸም የቤቱ ባለመብት የሆነበት አግባብ ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል።

ተጠሪዎች ጥቅምት 22 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- 2ኛ ተጠሪ ቤቱን የተረከብኩት በመ.ቁ 84805 የ1ኛ ተጠሪ ወላጅ እናት የሆኑት የሟች ወ/ሮ አቻሜ ጨንገሬ የውርስ ሐብት ተጣርቶ ክርክር የተነሳበት ቤት እና ይዞታ የ2ኛ ተጠሪ ወላጅ አባት እና ባለቤታቸው የነበሩት ወ/ሮ አቻሜ ጨንገሬ መሆኑ ተረጋግጧል፤ በዚሁ መሠረት ክፍፍል እንዲደረግ በመ.ቁ 101280 ክስ ቀርቦ ተጠሪዎች ቤቱን እንድንካፈል ተወስኗል፤ ይህን ተከትሎም የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተሰጥቶ ቤቱ እኩል ታከፍሎ ተረክቤአለሁ፤ የቤት ቁጥር 123/ሐ በሚል የተደለደለ ቤት የለም፤ አመልካች ቤት ቁጥር 123/ሐ ማለት የጀመሩት ከጊዜ በኋላ ነው፤ ስለሆነም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው። አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

በመሠረቱ ከሣሽ የሆነው ተከራካሪ ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 222 መሠረት አዘጋጅቶ ከሚያቀረበው የክስ ማመልከቻ ጋር ለጉዳዩ ማስረጃ ይሆኑኛል የሚላቸውን የሠውም ሆነ የጽሁፍ ማስረጃዎችን ዝርዝርና ዋናውን ወይም ትክክለኛ ግልባጮቻቸውን ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223 እና 234 ድንጋጌዎች ስር የተደነገገ ሲሆን የግራ ቀኙ ክርክር በቃል ተሰምቶና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 246፣ 247፣ 248 እና 249 ድንጋጌዎች አግባብ ተገቢው ጭብጥ ተይዞ ለጉዳዩ በሕጉ አግባብ የቀረቡት የተከራካሪ ወገኖች ማስረጃዎች ተሰምተውና አስፈላጊ ሲሆንም በሕጉ አግባብ ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ማስረጃዎችን እንዲቀርቡ በማድረግ ጉዳዩ በሚገባ ተጣርቶ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 138፣ 257፣ 258 እና 259፤ 181 እና 182 ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝቡናል።

በያዝነው ጉዳይ አመልካች የአከራካሪው ቤት ባለይዞታ ነኝ፤ ተጠሪዎች መብት እና ጥቅም ሳይኖራቸው ቤቱን ይዘውብኛል በማለት ከመከራከር በቀር በእርግጥም ይህን ክርክራቸውን የሚደግፍላቸውን ማስረጃ

ያቀረቡ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አያመለክትም፤ ይልቁንም ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ተጣርቶ እንዲቀርብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ከቀረበው ምላሽ እና በተለያዩ መዝገቦች ከተሰጠው ውሳኔ ይዘት የተረጋገጠው ፍሬነገር አከራካሪ የሆነው ቤት በሚገኝበት ይዞታ ውስጥ ቀበሌው የሚያስተዳደረው ቤት የሌለ መሆኑን፤ ተጠሪዎች ቤቱን የተረከቡት የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ስለሆነ እኩል እንዲካፈሉ በማለት የተሰጠውን ውሳኔ ለማስፈጸም በተከፈተ የአፈጻጸም መዝገብ በተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሠረት መሆኑን፤ ተጠሪዎች አስቀድሞ በመ.ቁ 71430 አቅርበውት የነበረው ክስ በማስረጃ አልተደገፈም ተብሎ ውድቅ ከመደረጉ በቀር ለአመልካች የፈጠረው መብት የሌለ መሆኑን እና አመልካች የቤቱ ባለቤት መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ይህንኑ የተረጋገጠ ፍሬረገር መሠረት በማድረግ አመልካች የቤቱ ባለቤት መሆናቸውን ስላላስረዱ ቤቱን ለመረከብ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጡት ውሳኔ በሕግ አግባብ የተሰጠ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 80590 በቀን 16/03/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 258188 ሚያዝያ 06 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. ነሐሴ 28 ቀን 2014 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

ማ/አ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ.210727

ቀን፡-28/03/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ገቢዎች ቢሮ - ዐቃቤ ሕግ ማዘንጊያ ደምሴ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ አዕምሮ ዘሪሁን

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው ተጠሪ በባሕር ዳር ከተማ ገቢዎች መምሪያ የታክስ ኦዲትና የሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት አስተባባሪነት ከነበሩበት ኃላፊነት ተነስተው ከደረጃ 9 ወደ ደረጀ 8 ዝቅ ብለው በሽያጭ መመዝገቢያ ኤክስፐርት ሆነው እንዲሰሩ በመመደባቸው ቅሬታ አቅርበው ተቀባይት በማጣቱ ለአማራ ክልል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የአስተዳደር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ጥፋት ሳይኖረብኝና የዲሲፕሊን ክስ ሳይቀርበብኝ ከሥራ መደቡ መነሳቴ ሆነ ከደረጃና ደመወዝ ዝቅ መደረጌ አግባብ አይደለም የሚል ሲሆን አመልካች ባቀረበው መልስ በደንብ ቁጥር 79/2003 አንቀጽ 9(4) መሠረት ማንኛውም የሥራ ሂደት አስተባባሪ በአሳማኝ ምክንያት ከኃላፊነት ሲነሳ ከያዘው መደብ ዝቅ ብሎ እንደሚመደብ ስለሚገልጽ በዚህ አግባብ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የተከናወነ ነው ብሏል። አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን አከራክሮ ተጠሪ ከደረጃ 9 ወደ ደረጃ 8 ዝቅ ብለው እንዲሰሩና ደመወዛቸው እንዲቀነስ የተደረገው ጥፋት ያለባቸው ስለመሆኑ ወይም የሥነ-ምግባር ጥሰት መፈጸማቸው የዲሲፕሊን ክስ ቀርቦ ሳይረጋገጥ በጥርጣሬ ብቻ መሆኑ ፍትሕ የማግኘት መብታቸውን የሚጥስ ነው በማለት የተጠሪ መሥሪያ ቤት ውሳኔን ሽሯል። የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝና ሰበር ሰሚ ችሎቶች የአመልካችን የይግባኝና የሠበር አቤቱታ ባለመቀበል ሠርዘዋል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ተጠሪ የዕውቀትና ክህሎት ክፍተት ያለባቸው እና የሥነ-ምግባር ጥሰት የፈጸሙ በመሆኑ ከሥራ መደባቸው መነሳታቸው ተገቢ ነው። በደንብ ቁጥር 79/2003 አንቀጽ 9(4) መሠረት የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊ የሥራ ሂደት ባለቤቶችን ያለዲሲፕሊን ክስ ሂደት ምደባ ማስተካከል ይችላል። ቅሬታ ቀርቦ አመልካች በሚሰጠው ውሳኔ ላይ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የማየት ሥልጣን የለውም የሚል ነው። የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ፍሬ ነገሩን አከራክሮ የመወሰን ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቷል። ተጠሪ የሠጡት መልስ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት በሕግ ሥልጣን ያለው አካል ነው። አመልካች ያለዲሲፕሊን ክስ ከሥራ መደብና ከደረጃ የማንሳት ሥልጣን በሕግ አልተሰጠውም፤ ውሳኔው ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል ብለዋል። አመልካች የመልስ መልስ በማቀረብ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ግራቀኙን ክርክር፣ የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘውን ጭብጥ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል።

እንደመረመርነው ተጠሪ በባሕር ዳር ከተማ ገቢዎች መምሪያ የታክስ ኦዲትና የሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት አስተባባሪነት ከነበሩበት ኃላፊነት ተነስተው ከደረጃ 9 ወደ ደረጀ 8 ዝቅ ብለው በሽያጭ መመዝገቢያ ኤክስፐርት ሆነው እንዲሰሩ በመመደባቸው ጥፋት ሳይኖረብኝና የዲሲፕሊን ክስ ሳይቀርበብኝ ከሥራ መደቡ መነሳቴ ሆነ ከደረጃና ደመወዝ ዝቅ መደረጌ አግባብ አይደለም የሚል ክርክር አቅርበው በየደረጃው የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ከደረጃ 9 ወደ ደረጃ 8 ዝቅ ብለው እንዲሰሩና ደመወዛቸው እንዲቀነስ የተደረገው ጥፋት ያለባቸው ስለመሆኑ ወይም የሥነ-ምግባር ጥሰት መፈጸማቸው የዲሲፕሊን ክስ ቀርቦ ሳይረጋገጥ በጥርጣሬ ብቻ መሆኑ ፍትሕ የማግኘት መብታቸውን የሚጥስ ነው በማለት የተጠሪ መሥሪያ ቤት ውሳኔን በመሻራቸው የቀረበ የሠበር አቤቱታ ነው።

የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም በሚል ጭብጥ በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘ ሲሆን በአማራ ክልል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 253/2010 አንቀጽ 4 ላይ እንደተመለከተው የሕጉ የተፈጻሚነት ወሰን በመንግስት መሥሪያ ቤትና በመንግስት ሠራተኞች ላይ ነው። የአስተዳደር ፍርድ ቤቱም ከሥራና ከሠራተኞች ጋር በሚሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ ጉዳዩን የመመልከት ሥልጣን በአዋጁ ተሰጥቶታል። በመርሕ ደረጃ ማንኛውም የክልሉ የመንግስተ ሠራተኛ የሚተዳደረው በዚሁ ሕግ መሠረት ይሆናል። በሌላ በኩል ሕግ አውጪው ሲፈቅድና በተለየ ሕግ ሲደነግግ

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞቻቸውን በተለየ ሕግ ሊያስተዳድሩ ይችላሉ፡፡ የአማራ ክልል የገቢዎች ባለስልጣን ተግባራትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 14 እና 8(1) መሠረት መሥሪያ ቤቱ ሠራተኞቹን በአዋጁና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሠረት እንደሚያስተዳድር ተመልክቷል፡፡ ይህን ተከትሎም ደንብ ቁጥር 79/2003 የተደነገገ ሲሆን ሠራተኞቹን የሚተዳደሩበትን ዝርዝር ድንጋጌዎች ይዟል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ መሥሪያ ቤት ሠራተኞችን የሚያስተዳድረው በተለየ ሕግ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ በደንቡ አንቀጽ 44(1) ላይ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ተፈጻሚነቱ በደንቡ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ በደንብ ቁጥር 79/2003 ላይ የገቢዎች ባለስልጣን ሠራተኞች የሥራ ክርክርን የሚመለከት የዳኝነት ሥልጣን ያለው አካል አልተመለከተም፡፡ ስለሆነም በደንቡ የሥራ ክርክርን የሚመለከት አካል ማን እንደሆነ ያልተሸፈነ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 253/2010 መሠረት የተቋቋመው የአስተዳደር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 253/2010 አንቀጽ 80 ከተሰጠው ሥልጣን መካከል የደመወዝ መቀነስ አንዱ በመሆኑ ተጠሪ ከሥራ ደረጃና መደብ ዝቅ ተደርገው የተቀነሰው ደመወዛቸው ላይ ይግባኝ ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ አቅርበው መታየቱ ተገቢ በመሆኑ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን ያለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በሰበር አቤቱታው ተጠሪ የዕውቀትና ክህሎት ክፍተት ያለባቸው እና የሥነ-ምግባር ጥሰት የፈጸሙ በመሆኑ ከሥራ መደባቸው መነሳታቸው ተገቢ ነው፡፡ በደንብ ቁጥር 79/2003 አንቀጽ 9(4) መሠረት የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊ የሥራ ሂደት ባለቤቶችን ያለዲሲፕሊን ክስ ሂደት ምደባ ማስተካከል ይችላል በሚል ያቀረበው ክርክር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)(ሀ) እና (ሸ) እንዲሁም አንቀጽ 10(1)(ሐ) እና (መ) መሠረት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ሕገ-መንገስቱን የሚቃረን ባለመሆኑ፣ ግልጽ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔንና የሕግ ትርጉምን ያልተቃረነ ስለሆነና ጉዳዩም ከተከራካሪዎች ባለፈ ሀገራዊ ፋይዳ ያለው ባለመሆኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ቀርቦ የሚመረመር ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ውሳኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 105612 ሰኔ 24 ቀን 2013 ዓ/ም፣ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 55215 ግንቦት 12 ቀን 2015 ዓ/ም እና የአማራ ክልል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የአስተዳደር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 10251/2013 ሚያዚያ 18 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- አፈጻጸሙ ላይ የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

❖ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሜ/መ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ. 210876

ሕዳር 30 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

እትመት አሠፋ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ቻላቸው ክንዴ- ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ነኢማ ከማል

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 03 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 01006/2013 ሠኔ 09 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የቤት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፤ የአሁን አመልካች 1ኛ ተከሳሽ፤ በዚህ የሰበር ክርክር የሌሉ አቶ ደረጀ ተፈራ የተባሉ ግለሰብ ደግሞ 2ኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ከስር 2ኛ ተከሳሽ ባል እና ሚስት መሆናቸውን እና በጋምቤላ ከተማ 03 ቀበሌ ውስጥ በአመልካች ስም ተመዝግቦ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በሚገኘው 208 ካ.ሜ ላይ ያረፈውን ቤት በጋራ ያፈሩ መሆኑን፤ በሕመም ምክንያት ወደ ጅማ በሄዱበት ወቅት አመልካች ከእውቅናቸው ውጪ በቤቱ ውስጥ የገባ መሆኑን በመግለጽ በቤቱ ውስጥ በምን ምክንያት እንደገባ ተጠይቆ ቤቱን ለቆ እንዲያስረክባቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በሰጡት መልስ የተጠሪ ጥያቄ ግዙፍ የሆነውን የባለቤትነት መብት የሚመለከት በመሆኑ የንብረቱ ባለቤት መሆንዋን የሚያሳይ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ልታቀርብ ይገባል፤ ተጠሪ ይህን ማስረጃ ያላቀረበች በመሆኑ ክሱን ለማቅረብ የሚያስችል መብት እና ጥቅም የላትም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርባል፡፡ በሌላ በኩል የስር 2ኛ ተከሳሽ መልስ የመስጠት መብቱ የታለፈ መሆኑን ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የቀረበልን የውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ መብት እና ጥቅም ያላቸው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 አግባብ የቤት ባለቤትነት ካርታ ወይም የአፈር ግብር በሰነድ ማስረጃነት ያላቀረቡ በመሆኑ አመልካች ያቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተገቢ ነው በማለት ክሱን በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡

ተጠሪ ይህን ብይን በመቃወም ለጋምቤላ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን አጽንቷል፡፡

ተጠሪ በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የተጠሪ እና ባለቤታቸው የሆኑት የስር 2ኛ ተከሳሽ የጋራ ንብረት በመሆኑ ቢሸጥም ባልና ሚስቱ እኩል የመካፈል መብት ያላቸው በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ መብት እንደሌላት የሰጡት ውሳኔ አግባብ አይደለም በማለት ሽሮ የመኖሪያ ቤቱ የሽያጭ ውል ፈራሽ ነው ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳን አዲስ ጭብጥ በመያዝ ውሳኔ ሰጥቷል፤ የሽያጭ ውሉ በማስረጃነት ባልቀረበበት ሁኔታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት መመለስ ሲገባው የሽያጭ ውል ሊፈርስ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበችው አቤቱታ የተያዘብኝ ቤት ይለቀቅልኝ የሚል ሆኖ ሳለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ የመወሰኑን አግባብነት ከመሠረታዊ የክርክር አመራር ስነ ስርዓት ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ማጣራት ሳያደርግ በብይን መዝጋቱ ተገቢነት የለውም፤ የስር 2ኛ ተከሳሽ የራሱን ድርሻ ከመሸጥ ውጪ የተጠሪን ድርሻ ከእኔ እውቅና ውጪ መሸጥ አይችልም፤ ስለሆነም ይህንኑ መሠረት በማድረግ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔው ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው የአሁን ተጠሪ አላግባብ የተያዘባቸው ቤት እንዲለቀቅላቸው ሲጠይቁ የአሁን አመልካች በሰጡት መልስ ተጠሪ የባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ክሱን ለማቅረብ የሚያስችል መብት እና ጥቅም የላትም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ መሆኑን፤ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ይህንኑ መቃወሚያ መሰረት በማድረግ ወደ ፍሬነገሩ ሳይገባ የተጠሪን ክስ በብይን ውድቅ ያደረገው መሆኑን፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ የስር ፍርድ ቤት በመቃወሚያው ላይ የሰጠውን ብይን ምንም ሳይል አልፎ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የተጠሪ እና ባለቤታቸው የሆኑት የስር 2ኛ ተከሳሽ የጋራ ንብረት በመሆኑ የመኖሪያ ቤቱ የሽያጭ ውል ፈራሽ ነው በማለት የወሰነ መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ፍርድ ቤት ተከራካሪ ወገኖች በተለያዩበት የፍሬነገር ጉዳይ ላይ ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ መስጠት የሚችለው በቅድሚያ በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ተገቢውን ብይን ከሰጠ በኋላ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 246 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሐገራችን የሰበር ክርክሮች የሚመሩበት የተለየ ስርዓት የሌለ በመሆኑም አንድን የፍትሐብሔር ጉዳይ በሰበር የሚያይ ፍርድ ቤትም በተመሳሳይ የፍትሐብሔር ክርክሮች የሚመሩበትን የሥነ ሥርዓት ሕግ ሊከተል ግድ ይለዋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የጋምቤላ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪን ክስ ውድቅ ያደረገው አመልካች ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሠረት በማድረግ በብይን ነው፤ ከዚህ ውጪ ግራቀኙ በተከራከሩበት የፍሬነገር ክርክር ላይ ተገቢውን ጭብጥ በመያዝ አጣርቶ የሰጠው ውሳኔ የለም፤ ይህ ብይን ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የጋምቤላ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እስካልተቀየረ ድረስ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፍሬ ጉዳዩን ከመመርመሩ በፊት በቅድሚያ የስር ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሠረት በማድረግ የሰጡት ብይን ተገቢ መሆን አለመሆኑን መርምሮ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ስነ ስርዓታዊ የክርክር አመራር ሒደት ሳይከተል በፍሬነገሩ ላይ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. በጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 01006/2013 ሠኔ 09 ቀን 2013 ዓ.ም በስሩ ያሉት ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ትዕዛዝ በመሻር የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአመልካች በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሠረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን ተገቢ መሆነ አለመሆኑን በቅድሚያ መርምሮ ውሳኔ መስጠት ሲገባው ይህን ሳያደርግ በፍሬነገሩ ላይ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ስሕተት የተፈጸመበት ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. በጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው መሠረት በስሩ ያሉት ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሠረት በማድረግ የሰጡት ብይን ተገቢ መሆን አለመሆኑን መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት፤ በሚሰጠው ውሳኔ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሚለወጥ ከሆነ በፍሬ ጉዳዩ ላይ አከራክረው እንዲወስኑ ለስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን እንዲመልስላቸው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-210953

29/03/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1ኛ. አቶ አርአያ ዮሴፍ -ቀረቡ

2ኛ. አቶ ፈቀደ ዮሴፍ - -አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ አስናቀች መንግስቱ - አልቀረቡም

2ኛ. ወ/ሮ ብዙ ደበሌ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች በቀን 09/11/2013 ዓ.ም በተሻፈ ማመልከቻ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.376953 በቀን 8/11/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ሰሚው ችሎት እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ሲሆን አመልካቾች በአለልቱ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሳሾች የነበሩ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ አሻሽለው ባቀረቡት ክስ አመልካቾች በጋራ በመሆን በ2009 ዓ.ም ምንም መብት ሳይኖርቸው ከሚበቃ ከተማ ቀበሌ 01 ፍትሕ ጽ/ቤት አካባቢ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተብሎ በሚጠራው ቦታ የሚገኘውን 600 ካ.ሜ የሆነ 39 ቅጠል ቆርቆሮ በላዩ ላይ ያለውን ግምቱ ብር 200,000.00/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ሊያወጣ የሚችል እና አወሳኙ በክስ ዝርዝር የተገለፀው በ1984 ዓ.ም እናቴ ወ/ሮ መንግስቴ ደስታ የምትባል የተናዘዘችልኝ ይዞታ በዚሁ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.12873 በቀን 06/05/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት በዚህ ይዞታ ላይ ወራሽነትን አረጋግጬ ወንድሞቼ የሆኑትን ጣልቃ ገቦችን ውስጥ ትቼ በስራ ምክንያት ወደ አዲስ አበባ ከተማ ከሄድኩ በኋላ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ በስራ ምክንያት ወደ አረብ ሀገር በመሄዴ ምክንያት በሕገ ወጥ መንገድ ይዘውብኝ ቤት ሰርተውበት እየነገዱበት ስለሆነ በራሳቸው ወጪ የሰሩትን ቤት አፍርሰው ይዞታውን እንዲለቁልኝ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአሁን አመልካቾች በሰጡት መልስም የአሁን 1ኛ ተጠሪ ተደረገልኝ የምትለው ኑዛዜ ላይ የቤት ቁጥር የቤት ቁጥር የለውም፣ ካሬ ሜትርም የለውም፣ አዋሳኝም የለውም፣ ቤቱ ስንት ቅጠል ቆርቆሮ እንደሆነም አይገልጽም፣ ስለሆነም የአሁን 1ኛ ተጠሪ ጠቅሳ ያቀረበችው ቤት የቀበሌ ሆኖ ለጊዜው እንዲያርፉበት የተደረገ ነው ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ በዚህ ይዞታ ላይ የባለይዞታነት ማስረጃ ስለሌላት ልትጠይቀን አትችልም፡፡እኛ በማይክሮ እና በጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ ተደራጅተን መኖሪያ ቤታችንን ብር 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ የሚያወጣ የሰራንበት እና በብሎኬት ምርት እና ስራ ደብሊዩ/ኬ/ቲ/አይ/ቲ በቀን 23/04/2007 ማስረጃ አውጥተንበት እየሰራንበት ስለሆነ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ክስ ውድቅ እንዲሆንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአለልቱ ወረዳ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶና ተገቢውን ማጣራት አድርጎ በሰጠው ውሳኔም ተጠሪዎች ለይዞታው ማስረጃ የሌላቸው መሆኑንና ግብርም ያልገበሩበት በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎት ይህ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፀና ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር የቤት ቁጥር 39 የሆነው ቤት በማን ስም እንዳለ በማጣራት ከሰው ምስክሮቹ ቃልና ከኮሚቴ ሪፖርቱ ጋር በመመዘን ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን መልሶታል፡፡

በዚህ አግባብም የአለልቱ ወረዳ ፍርድ ቤት ባደረገው ማጣራት የሚቃዋ ፊቼ ገሊላ ከተማ አስተዳደር ቤቱ በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ማስረጃ የሌለው መሆኑን መግለፁን፤ከዚህ ባለፊ የሽማግሌዎችን ቃል በመቀበል ያቀረበው ሪፖርት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፤የግራ ቀኙ ምስክሮች የሰጡት ቃል ተመጣጣኝ መሆኑን፤የወራሽነት ማስረጃን በተመለከተ 1ኛ ተጠሪ መብት ከሌላቸው ውድቅ ሊደረግና ዋጋ ሊያጣ የሚችል መሆኑን፤ኑዛዜው ስለይዞታው ምንም የማይል ቤቱ የት እንደሚገኝና አዋሳኙ እነማን እንደሆኑ የማያመለክት መሆኑን፤አመልካቾች ያቀረቡት ህዳር 19 ቀን 1983 ዓም የተፃፈው ውል አዋሳኙ ሙሉ ለሙሉ ባይመሳሰልም ግንኙነት ያለው መሆኑን፤በይዞታው ላይ ማንም ግብር የማይከፍልበት መሆኑን፤ተጠሪዎች ያቀረቧቸው ምስክሮች የባለይዞታ የምስክር ወረቀትን ለመደገፍ

የሚረዱ እንጂ በራሳቸው ባለቤትነትን ለማሳየት በቂ አለመሆኑን በመጥቀስ የቀረበው ክስ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 33(2) እና (3) መሰረት ውድቅ ነው በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች የአለልቱ ወረዳ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታ ለሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔም የተጠሪዎች ምስክሮች በአከራካሪው ቦታ ላይ ያለው አሮጌ ቤት የ1ኛ ተጠሪ እናት መሆኑን፤ይህንን ቤትም 1ኛ ተጠሪ በውርስ ያገኙ መሆኑን በቦታው ላይ አሁን የተሰራው ቤት ሁለት አመት የማይሞላው መሆኑን ያስረዱ መሆኑን፤የተለያዩ አካላት የአካባቢውን ሽማግሌዎች በመያዝ ባደረጉት ማጣራት ይዞታው የወ/ሮ መንግስቴ ደስታ መሆኑን ፤አመልካቾች በሽያጭ አስተላልፎልናል የሚሉት ሀምሳ አለቃ ገ/ማሪያም ጉደታ በይዞታው ላይ መብት የሌለው መሆኑን ማረጋገጣቸውን በመጥቀስ በማስረጃ ምዘና ረገድ ተጠሪዎች በይዞታው ላይ የተሻለ መብት ያላቸው መሆኑን ማስረዳታቸውን በመጥቀስ አመልካቾች መብት በሌላቸው መሬት ላይ ያከናወኑት ግንባታ በራሳቸው ወጪ በማፍረስ ይዞታውን ለአሁን ተጠሪዎች እንዲለቁ በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ሽሯል፡፡

የአሁን አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙን በፍ/ስ/ስ/ ሕግ ቁጥር.337 መሰረት የሰረዘው ሲሆን ሰበር ሰሚ ችሎቱም በስር ፍርድ ቤቶች የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት አመልካቾች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም በአጭሩ የአለልቱ ወረዳ ፍርድ ቤት ከዚህ በፊት ለክርክር መነሻ የሆነውን ቤት የማን እንደሆነ፤ በማን ስም ተመዝግቦ እንዳለ እንዲሁም ማን ግብር እንደሚገብርበት ተጣርቶ እንዲቀርብ በታዘዘው መሰረት በዚህ አከራካሪ በሆነው እና ክርክር ባስነሳው ቦታ ላይ ማንም መብት እንደሌለው፤ እንዲሁም ማንም ግብር የገበረበት እንደሌለ፤ የሚቃዋ ፍቼ ገሊላ ከተማ አስተዳደር በደብዳቤ ቁጥር G/9/B/M/M/F/G 1113/64 በቀን 03/10/2011 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ለወረዳው ፍርድ ቤት ገልጿል፡፡ይህም ተጠሪዎች ከመነሻውም አመልካቾች ላይ መብት በሌላቸው ጉዳይ ላይ ክስ ማቅረባቸውን ፤ክስ ባቀረቡበት ጉዳይም የመክሰስ መብት የሌላቸው መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ እያለ በዚህ አግባብም የወረዳው ፍርድ ቤት ሕጉን በተከተለ መልኩ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በይዞታው ላይ ምንም መብት የላትም ብሎ ክሱን ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ሆኖ እያለ በየደረጃው ያሉት የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የአሁን ተጠሪዎች ባለመብት ናቸው ብለው መወሰናቸው አግባብነት የለውም፡፡የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተፈፀመውን የሕግ ስሕተት ሊያርም ሲገባው የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ማጽናቱ አግባብነት የለውም፡፡ስለሆነም የስር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተሽሮልን ተገቢው ፍርድ እንዲሰጥልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታና ቤት የተጠሪዎች አውራሽ ይዞታ ስለመሆኑ የሰነድ ማስረጃ ባላቀረቡበት እና የሚመለከተው የአስተዳደር አካል ተጠይቆ ቤትና ይዞታው የተጠሪዎች አውራሽ አለመሆኑን ምላሽ በቀረበበት የስር ፍርድ ቤት አመልካቾች የሰሩትን ቤት አፍርሰው ይልቀቁ በማለት የወሰነበትን አግባብነት ከፍ/ስ/ስ/ ሕግ ቁጥር 33(2)(3) አኳያ ለመመርመር የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት መልስም የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.81912 ላይ ግንቦት 17 ቀን 2013 ዓ.ም ለወሰነው ውሳኔ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 344570 ላይ ሐምሌ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ለሰጠው ትዕዛዝ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.376953 ላይ ሐምሌ 08 ቀን 2013 ዓ.ም ለሰጠው ትዕዛዝ መሰረቱ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 321496 ላይ የካቲት 17 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ይዞታው የማነው የሚለውን በተመለከተ በግራ ቀኝ የቀረበ የሰነድ ማስረጃ ያልቀረበ ስለሆነ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የማነው የሚለውን ጭብጥ የምስክሮችን ቃል እና ከከተማ አስተዳደሩ የቀረበውን ቃለ ጉባኤ በመመዘን ውሳኔ እንዲሰጥ ትዕዛዝ የሰጠው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፡፡የሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረት በማድረግ ማስረጃን ለመመዘን ባለው ስልጣን የምስክሮችን ቃል እና የቃለ ጉባኤውን ይዘት በመመዘን ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ የአሁን ተጠሪዎች አውራሽ የሆኑት የሚች ወ/ሮ መንግስቴ ደስታ መሆኑን አረጋግጦ መወሰኑ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት መወሰናቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የለውም፡፡

አመልካቾች በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 321496 ላይ የካቲት 17 ቀን 2012 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ አግባብ አልነበረም የሚሉ ከሆነ በወቅቱ ስልጣን ላለው የበላይ ፍርድ ቤት ተፈጥሯል የሚሉትን መሰረታዊ የሕግ ስሕተት በመጥቀስ አቤቱታ ማቅረብ ነበረባቸው እንጂ አሁን በዚህ ደረጃ በስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሰረት ተወስኖ እያለ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል ማለታቸው ራሱ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ነው፡፡ስለሆነም የተፈጠረ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የሌለ በመሆኑ የስር ከፍተኛ፣ ጠቅላይ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የለውም ተብሎ እንዲወሰንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾችም የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡በኢፌዲሪ ህግ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ) እና በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10(1) እንደተመለከተው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ውስጥ

መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞ ሲገኝ በሰበር አይቶ የማረም ነው፡፡በዚህ አግባብም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ሰሚነት ስልጣኑን ተግባራዊ ሲያደርግ ፍሬ ነገርን በተመለከተ በዋነኝነት መነሻ የሚያደርገው ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአለልቱ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የሻረው አመልካቾች በ1993 ዓም በተደረገ የሽያጭ ውል አከራካሪውን ቤት በመግዛት ቀድሞ የነበረውን ቤት በማፍረስ አዲስ ቤት መስራታቸውን ካስረዱት የአመልካቾች ምስክሮች ቃል ይልቅ በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ የተደረገው ማጣራት ስለጉዳዩ በጥልቀት የሚያውቁትን የአካባቢውን ሽማግሌዎች በመያዝ የተደረገ ሆኖ ይዞታው የወ/ሮ መንግስቴ ደስታ መሆኑን ፣አመልካቾች በሽያጭ አስተላልፎልናል የሚሉት ሀምሳ አለቃ ገ/ማሪያም ጉደታ በይዞታው ላይ መብት የሌለው መሆኑን ማረጋገጣቸውን፣የተጠሪዎች ምስክሮች በአከራካሪው ቦታ ላይ ያለው አሮጌ ቤት የ1ኛ ተጠሪ እናት መሆኑን፣ይህንን ቤትም 1ኛ ተጠሪ በውርስ ያገኙ መሆኑን በቦታው ላይ አሁን የተሰራው ቤት ሁለት አመት የማይሞላው መሆኑን ያስረዱ መሆኑን፣በዚህም ከማስረጃ ምዘና አንፃር ተጠሪዎች በይዞታው ላይ የተሻለ መብት ያላቸው መሆኑን ማስረዳታቸውን በመጥቀስ ነው፡፡ይህ የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ በዚህ ችሎት ሊለወጥ የሚችለው የስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ምዘና ረገድ የፈፀሙት ስህተት ከተገኘ ብቻ ሲሆን ይህ ችሎት ባደረገው ምርመራ በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት ያልተገኘ በመሆኑ የአመልካቾችን መከራከሪያ ውድቅ በማድረግ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 81912 ግንቦት 17 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና ይህንን ፍርድ በማፅናት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 344570 ሐምሌ 1 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.376953 ሐምሌ 8 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር.348(1) መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. በሰበር ሰሚው ችሎት ተለዋጭ ትዕዛዝ እስኪደርሰው ድረስ በአለልቱ ወረዳ ፍርድ ቤት አፈፃፀም ምድብ ችሎት በመ/ቁ. 17076 የተጀመረው የአፈፃፀም መዝገብ ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ በቀን 15/11/2013 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 211260

ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ-ክርስቲያን ኮሚሽን

ተጠሪ- አቶ መስፍን አዱኛ- ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የግል የስራ ቅጥር ዉልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በጀመረበት በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ በቀን 30/06/2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ክስ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በፕሮጀክት ኦፊሰርነት በወር ብር 10,095.00 እየተከፈለኝ ሳገለግል የቆየሁ ቢሆንም አመልካች ምንም አይነት ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠኝ፣ በማላውቀው እና በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅምት 20 ቀን 2013 ዓ.ም የስራ ውሌን ያቋረጠው በመሆኑ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ተብሎ ወደ ስራዬ እንድመለስ፤ ወደ ስራ የማልመለስ ከሆነ ደግሞ ያልተጠቀምኩበት የ58 ቀን የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ፣ ካሳ፣ የሶስት ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ ክፍያ ለዘገየበት የሶስት ወር ደመወዝ ቅጣት እንዲከፍል እና የስራ ልምድ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቀዉን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

አመልካች በበኩሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን በማስቀደም ፍሬ ነገሩን አስመልክቶ ባቀረበው መልስ ተጠሪ የተቀጠረው በአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ-ክርስቲያን የእርዳታ እና ልማት ዘርፍ ውስጥ ኦ ቪ ሲ በሚባል ፕሮጀክት ስራ ሲሆን ስራዉም ለተወሰነ ጊዜ የሚሰራ መሆኑን፤ ከዚህ ባለፈ ግራስ ኢምፓወርመንት በሚባል ሌላ ፕሮጀክት ላይ እንዲሳተፍ ተደርጎ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ እንዲሰናበት የተደረገ በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው። የዓመት እረፍት ክፍያን በሚመለከት ተጠሪ የነበረው የእረፍት ጊዜ 25 ቀናት ሲሆን ከዚህ ውስጥም 8 ቀናት ተጠቅሟል፤ ለቀረው የ17 ቀን እረፍት የስራ ውሉ እንደተቋረጠ ወደ ገንዘብ ተለውጦ የተከፈለው በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል።

ጉዳዩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች ድርጅት የሚሰራው ስራ የገንዘብ ችግር ያለባቸው እና የኤች አይ ቪ ታማሚዎችን በየጊዜው ድጋፍ እና ስልጠና በመስጠት ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግ ሲሆን ግለሰቦቹ ስልጠናውን አጠናቀው የጨረሱበትን ጊዜ እንደ አንድ የፕሮጀክቱ ፌዝ በመቁጠር ቀጣይ ተጠቃሚዎች ሲመጡ ደግሞ እንደ ሌላ ፌዝ በመቁጠር ቀጣይነት ባለው መልኩ ሰራተኞችን ሲያሰራ እንጂ እየበተነ ያልነበረ በመሆኑ ተጠሪ ለተወሰነ ጊዜ ስራ የተቀጠረ ነው ለማለት አይቻልም። ስለሆነም የተጠሪ ስንብተ ህገ-ወጥ ነው በማለት አመልካች ለተጠሪ የሶስት ወር ማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና ካሳ በጠቅላላው ብር 90,855.00 ይክፈለው በማለት ወስኗል። በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኘው አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ይግባኙ ተሠርዞበታል። ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህን በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

አመልካች በቀን 15/11/2013 ዓ.ም በተፃፈ 03 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያላቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙለት ጠይቀዋል። የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ የተጠሪ የስራ ውል ጥቅምት 20 ቀን 2013 ዓ.ም እንደሚቋረጥ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠ በኋላ የደመወዝ ጭማሪ መደረጉ ስራው የቀጠለ መሆኑን ያረጋግጣል በሚል ከተጠሪ በኩል የቀረበ ክርክር ሳይኖር ውሳኔ መሰጠቱ፤ ፕሮጀክቱ በገንዘብ እጥረት ምክንያት የተጠሪን የስራ መደብ መሠረዙ በማስረጃ ተረጋግጦ ሳለ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው መባሉ፤ ፕሮጀክቱ ሙሉ በሙሉ ባለመዘጋቱ ብቻ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው መባሉ፤ እንዲሁም አመልካች ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ እያለ የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንድንከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የህግና የማስረጃ ምዘና ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው።

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች ተጠሪን ለፕሮጀክት ስራ የቀጠረው እና ፕሮጀክቱ በበጀት እጥረት ምክንያት በመቋረጡ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ተጠሪን የተቀጠረበትን የስራ መደብ ከሠረዘ በኋላ በሌላ መደብ ላይ ደመወዝ በመክፈሉ ማስጠንቀቂያውን ትቷል እና ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ተብሎ የተወሰነበት አግባብነት ተጠሪ ባለበት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል። በዚሁም መሠረት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥት ተደርጎ በቀን 04/02/2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካች በቀን 10/06/2000 ዓ.ም እና በቀን 20/02/2013 ዓ.ም በተፃፉ ደብዳቤዎች ስራውን በቋሚነት ተቀጥሬ ላልተወሰነ ጊዜ እንድሰራ የሚገልጹ ሲሆኑ አመልካች ስራው ለተወሰነ ጊዜ የሚሰራ እንደሆነ በመግለጽ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ አመልካች በቀን 20/02/2013 ዓ.ም በሰጠኝ ደብዳቤ ደመወዝ የተጨመረው በአዲስ የስራ መደብ ላይ ሳይሆን ባለው ህግ እና ደንብ መሠረት ሀብት አግኝቶ በቀጣይ በመልካም አፈፃፀም እንድሰራ በማበረታታት በማሰብ ነው፤ ፕሮጀክቱ ተሠርዟል በሚል የቀረበውም ክርክርም

ሀሰተኛ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል። አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቶ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል።

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ከተያዘው ጭብጥ፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመረዉም ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሰረት ያደረገዉ አመልካች የስራ ዉሉን ከህግ ዉጪ ማቋረጡን ሲሆን፣ አመልካች በበኩሉ ዉሉ የተቋረጠዉ ተጠሪ የተቀጠረበት የፕሮጀክት ስራ በመጠናቀቁ ምክንያት መሆኑን ጠቅሶ ስንብቱ ህጋዊ ነዉ በማለት ተከራክሯል። ስለሆነም ለክርክሩ እልባት ለመስጠት በፍት/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 246(1) መሠረት መያዝ የሚገባዉ ትክክለኛ ጭብጥ የስራ ዉሉ የተቋረጠዉ ተጠሪ የተቀጠረበት የፕሮጀክት ስራ በመጠናቀቁ ነዉ ወይ? የሚል ነዉ። አመልካች የስራ ዉሉን ማቋረጡን ሳይክድ ያቋረጠዉ ተጠሪ የተቀጠረበት የፕሮጀክት ስራ በመጠናቀቁ ምክንያት ጠቅሶ የተከራከረ በመሆኑ ይህን በቅድሚያ የማስረዳቱ ሸክም የአመልካች ይሆናል። የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ይህንኑ በጭብጥነት በመያዝ የግራ ቀኝ ማስረጃዎችን ሰምቶ እና መርምሮ አመልካች ለተጠሪ በዓፈዉ ደብዳቤ የስራ ዉሉ ከጥቅምት 20 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ እንደሚቋረጥ ተጠሪን ካሳወቀዉ በኋላ ዉሉ ይቋረጣል የተባለበት ጊዜ ካበቃ በኋላ ተጠሪ ደመወዝ ተጨምሮለት በስራዉ እንዲቀጥል በሌላ ደብዳቤ የገለጸለት መሆኑንና ይህ ከሆነ በኋላ የተከሰተ የስራ ዉሉን ሊቋርጥ የሚችል ሌላ ምክንያት ስለመኖሩ የቀረበ ማስረጃ ያለመኖሩን፣ ምንም እንኳ አመልካች በሊጋሾች የሚደገፍ ቢሆንም ሰራተኞችን እየቀጠረ ሰፊ እና ቀጣይነት ያለዉ ነገር ግን በፌዝ በፌዝ እየተከፋፈለ ስራዉም እየተሰራ የሚገኝ እንጂ አለመሰረዙን ከድምዳሜ ላይ ደርሷል። በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 መሠረት የዚህ ችሎት ስልጣን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ በመሆኑ ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን የማረጋገጥ ስልጣን የለዉም። የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከላይ በተመለከተዉ መልኩ የደረሰበት የፍሬ ነገር ድምዳሜ በአዋጁ ስለ መሠረታዊ የህግ ስህተት ትርጓሜ በሚሰጠዉ የአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከተዉ አንፃር ሲታይ የተፈጸመ የህግ ስህተት የለም። ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ በማለት የደረሱበት ድምዳሜ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም። ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

ዉሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 171736 ሰኔ 18 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎትየሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 267883 ሐምሌ 12 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሰረት ጸንተዋል።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

2. የሰበር አጣሪ ችሎት ሐምሌ 23 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል።

3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሂ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ. 211408
ቀን ፡- ግንቦት 02 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ አማረ አምባዬ፡- ጠበቃ ትዕግስት ተስፋዬ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ ነጃት ሰይድ፡- አልቀረቡም

2. በአዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የግንባታ ፈቃድና

ቁጥጥር ጽ/ቤት፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪዎች ተከሳሾች ነበሩ፡፡ አመልካች ያቀረቡት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 438 የሆነ ቤትና ቦታ ያለኝ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ አጎራባች ይዞታ ያላቸው በመሆኑ ተገቢውን ርቅት ጠብቀው ሕንጻቸውን መገንባት ሲገባቸው ከግድግዳዬ ጋር አጣብቀው የሠሩ በመሆኑ ቤቱ በመፍረሱ ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ ውል የደረሰውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እተካለሁ በማለት ሥምምነት ያደረጉ ቢሆንም የበለጠ ጉዳት

አድርሰው ውሉ ከሚሸፍነው በላይ ተጨማሪ ጉዳት ደርሷል። 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ሰርተው እንዲያስረክቡ ብጠይቃቸውም ፈቃደኛ አይደሉም። ስለዚህ ለደረሰው ጉደት ብር 726,417.91 እና የማከራየው ቤት ገቢ ስለተቋረጠ በየወሩ ብር 1,100.00 ካሣው ተከፍሎ እስኪጠናቀቅ ድረስ እንዲከፍሉ፣ ርቀታቸውን ጠብቀው እንዲገነቡ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ 1ኛ ተጠሪ የገነቡትን ግንባታ አፍርሶ በሕግ የተቀመጠውን የቦታ ርቀት ያስጠብቅ ተብሎ ይወሰንልኝ የሚል ነው። 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ጉዳዩ በሥምምነት ያለቀ ነው፤ ከአመልካች ጋር በሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ የውል ሥምምነት ደረሰ የተባለው ጉዳት በሽማግሌዎች ተገምቶ ክፍያ እንዲከፈልና ግንባታው እንዲቀጥል ውል አድርገናል። ክሱ ውደቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል። የቃል ክርክር ሲደረግም አመልካች ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገው ውል ዕቃን እንጂ ቤትን የሚመለከት አይደለም፤ ውሉም ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ ሌላ ውል ተተክቷል። በውል ከተስማማነው በላይ ተጨማሪ ጉዳት ድርሷል ብለዋል።

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገው ሥምምነት ስለቤቱ ጉዳትም ሥምምነት አድርገዋል። አመልካችና 1ኛ ተጠሪ በእርቅ ወይም በሥምምነት የጨረሱትን ነገር ላይ ክስ መቅረቡ ተገቢነት የለውም፤ በሥምምነቱ መሠረት ካልተፈጸመ በሥምምነቱ መሠረት እንዲፈጸም ክስ ማቅረብ እንጂ ከዚህ ውጭ አዲስ ክስ መቅረቡ ተገቢነት የለውም በማለት የአመልችን ክስ ውደቅ አድርጓል። 2ኛ ተጠሪ ላይ የተጠየቀው ዳኝነት የማየት ሥልጣን ፍርድ ቤቱ የለውም በማለት ወስኗል። አመልካች ያቀረቡትን ይግባኝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ባለመቀበል ሠርዟል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም እርቁ ወይም ውሉ ተፈጸመ የሚባለው ክፍያ ሲፈጸም ወይም ንብረቱ ሲያድሱ ነው። ጉዳቱ አሁንም እየቀጠለ ባለበትና ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገው ውል ዕቃን ብቻ የሚመለከት ሆኖ እያለ ክሱ ውደቅ መደረጉ ተገቢነት የለውም። ፍርድ ቤቱ ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገውን ሥምምነት መሠረት አድርጎ ውሳኔ አልሰጠበትም። 1ኛ ተጠሪ ተጨማሪ ጉዳት በማድረሳቸውና ውሉ ከሚሸፍነው በላይ ጉዳት ስለደረሰ አጠቃልዬ ካሳ መጠየቄ ተገቢ ነው። በሥምምነቱ ባልተሸፈነው ጉዳት ላይ ውሳኔ ሳይሰጥበት ወይም ክስ የማቅረብ መብቱ አለመጠበቁ ስህተት ያለበት ነው። 2ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበውን ክስ ሳይሰማ ሥልጣን የለኝም ማለቱ ሕጋዊ አይደለም የሚል ነው። የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ በግራቀኙ መካከል ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገውን ሥምምነት ውሳኔ ሳይሰጥበት ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገው ሥምምነት መሠረት በማድረግ ብቻ ክሱን በብይን ውደቅ ያደረግበትን አግባብነት ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ አዟል። 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ይዘትም ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገው ውል አልተተካም። ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገ ሥምምነት ካለም ሥምምነቱን መሠረት በማድረግ መብታቸውን ይጠይቃሉ እንጂ በራሳቸው በባለሙያ አስገምተው ካሣ መጠየቃቸው ተገቢነት የለውም። ስለሆነም የሰበር አቤቱታው ተቀባይነት የለውም ብለዋል። 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ 1ኛ ተጠሪ የግንባታ ፈቃድ የወሰዱት ከ2ኛ ተጠሪ ጽ/ቤት ሳይሆን ከንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የግንባታና ፈቃድ ቁጥጥር ጽ/ቤት

በመሆኑና የአጎራባች ሥምምነት የሚፈጸመው በተጠሪ ጽ/ቤቱ በኩል ባለመሆኑ ክሱ አይመለከተኝም ብሏል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘው ጭብጥ፣ በሥር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ያቀረቡት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 438 የሆነ ቤትና ቦታ ያለኝ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ አጎራባች ይዞታ ያላቸው በመሆኑ ተገቢውን ርቅት ጠብቀው ሕንጻቸውን መገንባት ሲገባቸው ከግድግዳዬ ጋር አጣብቀው የሠሩ በመሆኑ ቤቱ በመፍረሱ ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ ውል የደረሰውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እተካለሁ በማለት ሥምምነት ያደረጉ ቢሆንም ውሉ ከሚሸፍነው በላይ ተጨማሪ ጉዳት ስለደረሰ ብር 726,417.91 እና የማከራየው ቤት ገቢ ስለተቋረጠ በየወሩ ብር 1,100.00 ካሣው ተከፍሎ እስኪጠናቀቅ ድረስ እንዲከፍሉ፣ ርቀታቸውን ጠብቀው እንዲገነቡ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ 1ኛ ተጠሪ የገነቡትን ግንባታ አፍርሶ በሕግ የተቀመጠውን የቦታ ርቀት ያስጠብቅ ተብሎ ይሰወንልኝ የሚል ነው፡፡

የአመልካች ቤት ላይ ጉዳት ሲደርስ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ከውል ውጭ ግንኙነት የነበራቸው ሲሆን ጉዳቱ መድረስ ከጀመረ በኋላ ግንኙነታቸው ውል መሠረት በማድረግ ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገው ሥምምነት ስለቤቱ ጉዳት ላይ መዋዋላቸውን የሥር ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ አመልካችም በክስ ማመልከቻው ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም ሥምምነት መደረጉንና ተጠሪ በውሉ መሠረት ካለመፈጸማቸውም በላይ ተጨማሪ ጉዳት ማድረሳቸውን ገልጸዋል፡፡ ይሕም ለክሱ መሠረት የሆነው አለመግባባት ግራቀኙ ካደረጉት ውልና ካለባቸው ግዴታ ጋር የሚያያዝ በመሆኑ የክሱ መሠረት የውል ግንኙነት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በአመልካች የክስ አቤቱታ ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ ውል የደረሰውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እተካለሁ በማለት 1ኛ ተጠሪ ሥምምነት ያደረጉ ቢሆንም የበለጠ ጉዳት አድርሰው ውሉ ከሚሸፍነው በላይ ተጨማሪ ጉዳት ደርሷል፣ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ሰርተው እንዲያስረክቡ ብጠይቃቸውም ፈቃደኛ አይደሉም በማለት ያካተቱት ፍሬ ነገር ክሱ በአንድ በኩል የውል አለመፈጸምንም መሠረት ያደረገ መሆኑን ሲያሳይ በሌላ በኩል ውሉ ከሚሸፍነው ጉዳት በላይ ስለደረሰ ጉዳቱን አጠቃልዬ ማቅረቤ ተገቢ ነው የሚለው የአመልካች መከራከሪያ ከውል ውጭ ግንኙነትንም መሠረት ያደረገ የክስ አቀራረብ የተከተሉ መሆኑን ያሳያል፡፡ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የውል ሥምምነት ካደረጉ በኋላ 1ኛ ተጠሪ የውል ሥምምነቱን በመፈጸም ሂደት ተጨማሪ ጉዳት ካደረሱ የውል ጉዳት ኪሣራ ማዕቀፍ ውስጥ የሚታይ እንጂ ግንኙነቱን ከውል ውጭ የሚያደርገው አይደለም፡፡ ይሕም ክስ አቀራረቡ የክሱን መሠረት ግልጽ ያላደረገ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በክስ በአቤቱታቸው ላይ የጠቀሱት ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገ ሥምምነት ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ደግሞ በመከላከያ ክርክራቸው ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገ ሥምምነት በመጥቀሳቸው የሥር ፍርድ ቤት በክሱ የተጠቀሰውን የግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም ሥምምነት በዝምታ በማለፍ ውሳኔውን ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገው ሥምምነት ላይ መስርቷል፡፡ በክሱ

የተጠቀሰውን የውል ሥምምነት መታለፉ የክርክር አመራር ግድፈት ያለበት መሆኑ እንደጠበቀ ሆኖ በሁለቱ የውል ሥምምነቶች መካከል ያለው ተዛምዶ ምን እንደሆነ በክሱ ተብራርቶ አለመቅረቡ የክርክር አመራር ግድፈት ለመፈጸሙ እንደመነሻ ሊወሰድ የሚችል ነው።

ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል። በፍብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 91/1/ እንደተመለከተው ክርክርን ለመለወጥ፣ አቤቱታውን ለማብራራት ሆነ ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ አቤቱታን ማሻሻል ይቻላል። ክስ የሚሻሻለው የቀረበውን አቤቱታ ለማብራራት ወይም ለፍትሕ መሰናክል የሆነ ነገር ካለ አስተካክሎ በመምራት ውጤት ጋር እንዲደርስ ለማስቻል ነው። ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት የሚቸገር ከሆነ እንደሁኔታው ክስ ወይም መልስ ተሻሽሎ እንዲቀርብ በማድረግ የክርክር ሂደቱንም ሆነ የውጤቱን ፍትሐዊነት የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርበታል። ስለሆነም አመልካች በክስ አቤቱታቸው የገለጹትን በማሻሻል ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያላቸውን ትክክለኛ የሆነው የውል ግንኙነት በሚያሳይ መልኩ እንዲያሻሽሉ ተደርጎ 1ኛ ተጠሪም በተሻሻለው ክስ መሠረት ክርክር እንዲያቀርቡ ተደርጎ ክርክሩ መመራት ሲገባው ይህ ሳይፈጸም ክርክሩ በቀረበው የክስ ጭብጥ መሠረት መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ግድፈት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል።

በሌላ በኩል አመልካች ከውል አንጻር 1ኛ ተጠሪ ላይ ክስ ሲያቀርቡ በ2ኛ ተጠሪ ላይ ከዋናው ዳኝነት ጋር የተገናኘ ግን ደግሞ ከውል ውጭ ባለ ኃላፊነት 1ኛ ተጠሪ የገነቡትን ግንባታ አፍርሶ በሕግ የተቀመጠውን የቦታ ርቀት ያስጠብቅ ተብሎ ይወሰንልኝ ሲሉ ክሱን አጣምረው አቅርበዋል። እንዲህ ዓይነት በአንድነት ተጣምረው መታየት የሚችሉ ጉዳዮች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ተነጥሎ ከታየ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ሊያሳካው የፈለገውን ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ ክርክርን የመምራት ዓላማ እንዳይሳካ ያደርጋል። በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 17(2) ላይ በአንድ ክስ ውስጥ የተለያዩ ዳኝነቶች ሲቀርቡ ዋናውን ወይም ከፍተኛውን ዳኝነት የሚመለከተው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን እንዳለው ተመልክቷል። አመልካች ያቀረቡት ዋናው የክስ መሠረት ንብረታቸው ላይ ጉዳት መድረስ ጋር ተያያዝ ዳኝነት በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ላይ የተጠየቀው ዳኝነትም ተከታይና ተጨማሪ ዳኝነት በመሆኑ ዋናውን ዳኝነት ለመወሰን ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት አብሮ መወሰን ይኖርበታል። በዚህ ረገድ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበውን ዳኝነት ለመመልከት ሥልጣን የለኝም ማለቱ መሠረታዊ የሆነ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል።

ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 205335 ሰኔ 16 ቀን 2013 ዓ/ም እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 236665 መጋቢት 16 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በፍርድ በተመለከተው አግባብ የክሱን መሠረት ለይተውና አብራርተው ክሱን አሻሽለው እንዲያቀርቡ በማድረግ፣ የተጠሪዎችን መልሰ በመቀበል ግራቀኙን አከራክሮ የመሠለውን እንዲወሰን ጉዳዩን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሠረት መልሠናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጸፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 211427

ግንቦት 26 ቀን 2014ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ዓለሙ ጋዲሞ

ተጠሪዎች፡-1) ወ/ሮ ትርንጎ ዳንሼ

2) ወ/ሮ ሽቶ ዳንሶ የቀረበ የለም

3) ወ/ሮ ብርቱካን ደንግሶ

4) አቶ ደስታ ደንግሶ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0030 ታሕሣስ 13 ቀን 2014ዓ/ም በዋለው ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ሲል አቤቱታውን መሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፀመበት ነው በሚል እንዲታረምለት አመልካች በመጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በሰዳማ ዞን ዳራ ኦትልቾ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳ ፍርድ ቤቱ በነበረው ክርክር አመልካች ከሣሽ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡ አመልካች ጥቅምት 16ቀን 2011ዓ/ም በተፃፈ ክሱ ከተጠሪዎች ጋር በገባው የመሬት መጠቀም ውል ሣይፈርስ ተጠሪዎች ባቀረቡት የሁከት ክስ መሬቱን እንዲለቅ በመሬቱ ላይ ላፈራው ንብረት ግምትን በሚመለከት በዳኝነት እንዲጠይቅ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መወሰኑ መነሻ በማድረግ በመሬቱ ላይ አፍርቻቸዋለሁ የሚላቸውን 23 ዓይነት አትክልችና ልዩ ልዩ ንብረቶች በመዘርዘር በባለሙያ ተገምተው እንዲከፈለው ጠይቋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው የተዘረዘሩ ንብቶች አመልካችን የሚመለከቱ አለመሆናቸውን፤ አመልካች ማስረጃ እንዲሆነው ያቀረበው ውልም ከእነሱ ጋር የተፈፀመ አለመሆኑን በመቃወሚያነት አቅርበው ውድቅ ሲደረግ በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ አንደኛ ከተጠሪ ጋር የገቡት ውል አለመኖሩን ከገለፁ በኋላ ሁሉም ተጠሪዎች በጋራ ሆነው ለክሱ ምክንያት የሆኑትን አትክልቶች የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች ደግሞ በሕይወት ሳሉ የተከሷቸው በመሆናቸው አመልካችን የማይመለከቱት ናቸው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት በአንደኛ ተጠሪ የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ ካደረገ በኋላ የግራ ቀኙን ምስክሮች የሰጡትን ምስክርነት መርምሮ ቀደም ሲል በነበረው ክርክር አመልካች በመሬቱ ላይ ላፈራው ንብረት ግምት እንዲጠይቅ የተፈቀደለት መሆኑን፤ በዚሁ መሰረት የግብርና ባለሙያ አመልካች በመሬቱ ላይ ያፈራው ንብረት በአንድ ዓመት ምን ያህል እንደሚያወጣ ገምቶ እንዲልክ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በዓመት 26,066.00 ብር እንደሚያወጣ መልስ ተሰጥቶታል፡፡ ፍርድ ቤቱም ይህን የባለሙያ ግምት በ10ዓመት በማባዛት ውጤቱን ለሁለት በማካፈል 130,330.00 ብር ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲከፍሉት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኙት ተጠሪዎች የይግባኝ አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የግብርና ባለሙያ ገምቶ የላከውን ግምት በ10 አባዝቶ ለሁለት አካፍሎ የተገኘውን ውጤት ተጠሪዎች እንዲከፍሉ የመወሰኑን ተገቢነት በጭብጥነት ይዞ ከመረመረ በኋላ ውሉ የፈረሰው ሕገወጥ ነው በሚል ስለሆነ የጊዜ ገደብ የሌለበትን ውል ወደፊት በ10 ዓመት የሚገኘውን ጥቅም ታሣቢ በማድረግ በ10 ማባዛቱ ተገቢነት የሌለው ነው ሲል ተጠሪዎች 26,066.00 ብር ብቻ ለአመልካች እንዲከፍሉት ሲል አሻሽሎ ወስኗል፡፡

አመልካች በበኩሉ የይግባኝ አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የስር ፍርድ ቤቱን ውሣኔ የማሻሻሉን ተገቢነት በጭብጥነት ይዞ ከመረመረ በኋላ ውሣኔውን አፅንቶታል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ሲል አቤቱታውን በመሰረዙ አመልካች ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አመልካች ሚያዚያ 12ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው የስር ፍርድ ቤቱ የንብረቱን ግምት በባለሙያ እንዲገመት ካደረገ በኋላ በግምቱ ላይ ግራ ቀኙ አስተያዬት እንዲሰጡበት ሣይደረግ፤ ግምቱ መገመት ያለበት የአንድ ዓመት ሣሆን ተቆርጦ ቢሸጥ የሚያወጣውን ዋጋ በመሆኑ እንደገና ተገምቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠት ሲገባ፤ በቀረበው ክስ በባለሙያ ተገምቶ እንዲከፈለው ጠየቀ እንጅ ለሁለት ተካፍሎ የአንድ ዓመት ግምት እንዲሰጠው ባልጠየቀበት ከላይ የተገለፀውን ውሣኔ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተው ተብሎ እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ቀደም ሲል በግራ ቀኙ በነበረው ክርክር አመልካች መሬቱን ለቆ እንዲወጣ ሲወሰንበት በመሬቱ ላይ ያለማውን የንብረት ግምት ይከፈለው ዘንድ ክስ ማቅረብ እንደሚችል ተወስኖለታል በሚል በጠቅላላው የንብረት ግምቱ በአስር ዓመት ተባዝቶ እንዲከፈል የተሰጠውን ውሣኔ ዳኝነት ያልተጠየቀበት ነው ተብሎ የበላይ ፍርድ ቤቶች የአንድ ዓመት ግምት ብቻ እንዲከፈል የወረዳው ፍርድ ቤትን

ውሳኔ በማሻሻል የመወሰናቸው አግባብነት እንዲጣራ ተብሎ ጉዳዩ ቀርቦልናል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው መጋቢት 1ቀን 2014ዓ/ም በተፃፈ የጋራ መልሳቸው ቀደም ሲል በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የነበረው ክርክር ከአባታቸው በውርስ ያገኙትን መሬት አመልካቹ ስለያዘባቸው እንዲለቅላቸው ክስ አቅርበውበት አመልካች መሬቱን ገዝቻለሁ የሚል ክርክር አቅርቦ ውሉ ሕገወጥ ነው ተብሎ በመሬቱ ለተከላቸው ተክሎች ግምት እንዲጠይቅ በተጠበቀለት መብት መሰረት ክስ ማቅረቡን፣ ንብረቶችም በባለሙያና በሽማግሌዎች ተቆጥረው በግራቀኞቸው ስምምነት ተደርጎ ተፈራርመውበት ባሙያው ግምቱን ሰርቶ መላኩን፣ በዚህ በባለሙያ ግምት መሰረት የወረዳ ፍርድ ቤቱ መወሰን ሲገባው በአስር ዓመት አባዝቶ እንዲከፈል መወሰኑ ተገቢ ባለመሆኑ በከፍተኛው ፍርድ ቤት መሻሻሉ ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሌለ የስር ፍርድ ቤቱ ውሣኔ እንዲፀናላቸው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቦ የግራ ቀኙ ክርክር ተጠናቋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥኛ የግራ ቀኙን ክርክር ሲሆን አጣሪ ችሎቱ ከያዘው ማስቀረቢያ ነጥብ አኳያ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ውሣኔና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጋዎች ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል፡፡

እንደተመረመረው ቀደም ሲል በነበራቸው ክርክር አመልካች መሬቱን እንዲለቅ የተወሰነው ውሉ ሕገወጥ ተብሎ መሆኑ፣ አመልካች ያቀረበው ክስ ቀደም ሲል በተሰጠው ውሳኔ የተጠበቀለትን መብት መነሻ በማድረግ በክሱ ላይ የተዘረዘሩት ንብረቶች ግምት በባለሙያ ተገምቶ እንዲከፈለው እንዲወስንለት መሆኑ፣ ባለሙያው በቦታው ተገኝቶ የገመተው 26,066.00 ብር መሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረ ነበር፡፡

የስር ወረዳ ፍርድ ቤቱ በባለሙያ ተገምቶ የቀረበለትን ግምት በ10ዓመት አባዝቶ እንደገና ለሁለት አካፍሎ የተገኘውን ድርሻ ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ ከመወሰኑ ውጪ ለምን እንደሆነ ምክንያቱን በግልፅ አላሰፈረም፡፡ ይግባኝ ሰሚ የሆነው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በማሻሻል የአንድ ዓመት ብቻ እንዲከፍል ሲወስን አመልካች የአስር ዓመት ግምት እንዲከፈለው አልጠየቀም በሚል ምክንያት ነው፡፡ በአመልካች በኩል የንብረቱ ግምት በባለሙያ ተገምቶ እንዲከፈለው ከመጠየቁ ውጪ የአስር ዓመት እንዲከፈለው መጠየቁን አይከራከርም፡፡

በመሰረቱ ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸውን ሙግት አጣርተው ውሣኔ ወይም ፍርድ ሲሰጡ በተከራካሪ ወገኖች በተጠየቁት ዳኝነት አይነትና ልክ ሊሆን እንደሚገባ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር182(2) የሚደነግግ ሲሆን ባልተጠየቀ ዳኝነት ፍርድ ወይም ውሣኔ መስጠት የማይቻልና ተገቢነት የሌለው መሆኑን ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 31547 መጋቢት 7ቀን 2000ዓ/ም እና በመዝገብ ቁጥር 33945 ጥቅምት 20ቀን 2001ዓ/ም የሰጠው

የሕግ ትርጉም ያስገነዝባል፡፡ ሲጠቃለል ከይግባኝ ሰሚ ጀምሮ በየደረጃው የሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ውሣኔ

1) የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0030 ታሕሣስ 13 ቀን 2014ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348(1) **ፀንቷል፡፡**

2) **ይህ የሰበር ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የዬራሳቸውን ይቻሉ፡፡**

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሠ/መ/ቁጥር 211615
ኅዳር 01 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች :-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች:- አቶ ሲሳይ ለገሰ ቡሩሳ -ጠበቃ ብርሃኔ ግርማ ቀረቡ

ተጠሪዎች:-ወ/ሮ እቴነሽ ተስፋዬ-ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ዉል ለማስፈረስ የተጠየቀ ዳኝነት ተከትሎ የተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ የቀረበ የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ተጠሪ በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ቤት በአሁን አመልካችና በስር 1ኛ ተከሳሽ ተሾመ ተስፋዬ ላይ በመሰረቱት ክስ አዋሳኞቹ በክሱ የተጠቀሰዉን በመከጡሪ ከተማ ዉስጥ ያላቸዉን ወላጅ አባታቸዉ አቶ ተስፋዬ ጨቡዶ እና እናታቸዉ ወ/ሮ አበራሽ ወርቁ በቀን 30/01/1992 ዓ/ም በተጻፈ ዉል አዋሳኙ በክሱ ላይ በተጠቀሰዉ ይዞታ ላይ የተሰራዉን መኖሪያ ቤት ለወንድማቸዉ ለስር 1ኛ ተከሳሽ ሲሰጡ 150 ካሬ ሜትር ቦታ ደግሞ ለእሳቸዉ ሰጥተዋቸዉ በቦታዉ ላይ 5 ክፍል ሰርቪስ ቤት መስራታቸዉን፤ ከዚህ በኋላ በ1998ዓ/ም ዉስጥ በግድያ ወንጀል ተከሰዉ ተፈርዶባቸዉ 9ዓመት ከ1 ወር ከታሰሩ በኋላ በዚሁ በሰሩት ክፍል ቤቶች ዉስጥ እየኖሩ እያሉ የስር 1ኛ ተከሳሽ የራሳቸዉን መኖሪያ ቤት ለአመልካች ሲሸጡ የተጠሪንም ሰርቪስ ቤቶች ቀላቅለዉ ሸጠዋል፡፡ስለሆነም በአመልካችና በስር 1ኛ

ተከሳሽ መካከል በቀን 06/07/2008ዓ/ም የተጠሪን ሰርቪስ ቤቶች ተጨምሮ የተደረገዉ የሽያጭ ዉል እንዲፈርስ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ከስር 1ኛ ተከሳሽ በሰጡት መልስ ተጠሪ በቀን 30/01/1992ዓ/ም ተድኅልኛል ያሉት የሥጦታ ዉል እንደ ሕጉ ተደረገ ዉል አይደለም፡፡የስር 1ኛ ተከሳሽ የሸጡት ቤት የራሳቸዉን የግል ቤት እንጂ ከሳሽ መብት ያላቸዉን ቤት አይደለም፡፡በአመልካችና በስር 1ኛ ተከሳሽ መካከል በተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል ላይ ተጠሪ ምስክር ሆነዉ ስለፈረሙ ዉል ይፍረስልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 17034 ላይ አስቀድሞ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 318320 ላይ ጉዳዩን መርምሮ በቀን 07/04/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የያዛቸዉን ጭብጦች መሰረት አድርጎ የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች ሰምቶና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 26/01/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የስር 1ኛ ተከሳሽ የራሳቸዉን አንድ ትልቅ ቤት እና የተጠሪን አምስት ሰርቪስ ቤቶች ቀላቅለዉ በቀን 06/07/2008ዓ/ም በተጻፈ ዉል ለአመልካች መሸጣቸዉ ተረጋግጧል፡፡በሌላ በኩል ይህ ቤት ሲሸጥ ተተሪ በቦታዉ ላይ ተገኝተዉ ምስክር በመሆን በሽያጭ ዉል ላይ የፈረሙና ቤቱን እንዲለቁ ሲጠየቁ እሺ እለቃለሁ በማለት ጊዜ ይሰጠኝ በማለት ሲለምኑ እንደቆዩ በዉሉ ላይ ምስክር የሆኑ ምስክሮች ከሰጡት ምስክርነት ቃል ተረጋግጧል፡፡ይህም የሚያሳየዉ ተጠሪ ቤቱ ሲሸጥ ተሳትፎ እንደነበራቸዉ የሚያሳይ ነዉ፡፡ስለሆነም የዉሉ አፈጻጸም ተጠሪን ያስገድዳቸዋል፡፡አመልካችም ቤቱን የገዙት ተጠሪ የስር 1ኛ ተከሳሽ እህት መሆናቸዉንና በአንድ ላይ ሲኖሩ እንደነበር በማየት ቤቱን በቅን ልቦና ስለገዙ ዉሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 324590 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 25/06/2013 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የስር 1ኛ ተከሳሽ ለአመልካች ከሸጡት ትልቅ መኖሪያ ቤታቸዉ ጋር የተጠሪን 5 ክፍል ሰርቪስ ቤት ቀላቅለዉ መሸጣቸዉን የተረጋገጠ መሆኑን፣እነኚህን 5 ክፍል ሰርቪስ ቤቶችን ተጠሪ ከወላጆቻቸዉ በስጦታ ባገኙት ቦታ ላይ በግላቸዉ እንደሰሩ በማስረጃ መረጋገጡን፣አመልካች የቤቶቹን ስመ ሀብት ወደ ሥማቸዉ ያዛወሩት ተጠሪ ዉል ይፍረስልኝ በማለት ክስ ከመሰረቱ በኋላ መሆኑ መረጋገጡን፣ይህም የተጠሪ ቤት ሆነ ተብሎ ተቀላቅሎ እንደተሸጠ እንደሚያሳይ፣ተጠሪ በዉሉ ላይ በምስክርነት መፈረማቸዉም የራሳቸዉ ሰርቪስ በቶች ተቀላቅለዉ እንደተሸጡ እያወቁ ምስክር ሆነዉ መፈረማቸዉን ምስክሮቹ የሰጡት ምስክርነት ቃል አሳማኝ በሆነ ሁኔታ አያሳይም፡፡ስለሆነም አመልካች ቤቱን ሲገዙ ሥልጣን ካለዉ አካል አረጋግጠዉ በቅን ልቦና ግዥ ፈጽመዋል የሚያስብል

ሁኔታ ስለሌለ የተጠሪ ንብረት በሆነዉ 5 ክፍል ሰርቪስ ቤት ላይ የተደረገዉ ዉል የሕግ መሰረት ስለሌለዉ ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1808/2 ፈርሷል ሲል ወስኗል፡፡በመቀጠል አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዉ ችሎቱ በመ/ቁጥር 375013 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 08/10/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 21/11/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡- ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት በቀን 06/07/2008ዓ/ም በተደረገ ዉል የገዛሁት በስር 1ኛ ተከሳሽ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝና የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እየተዘጋጀለት እንደሆነና በቅርብ እንደሚሰጣቸዉ ከመከሙሪ ከተማ መሬት አስተዳደር መረጃ ጠይቄ በተገለጸልኝ መሰረት ነዉ፡፡ስመ ሀብቱም በቀን 15/07/2008ዓ/ም በስሜ ተመዝግቦልኛል፡፡ቤቱን ለመግዛት ስሄድ ተጠሪ ከወንድማቸዉ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር እንደሚኖሩ ስለተገነዘብኩ ቤቱ የማን መሆኑን ስጠይቃቸዉ በይዞታዉ ላይ የሚገኙ ቤቶች ከነሰርቪስ ቤቶቹ የወንድሜ ነዉ በማለት ለዚህም በምስክርነት እንደሚፈርሙልኝ ስለገለጹልኝና በምስክርነትም ስለፈረሙ ጭምር በማመን በቅን ልቦና ቤቱን እንድገዛ አድርገዉኛል፡፡ከወረዳ ሰነዶችን በማረጋገጥ ጭምር የፈጸምኩት ዉል ነዉ፡፡የይዞታ ማረጋገጫ ያገኘሁት በቀን 15/07/2008ዓ/ም ቢሆንም ማስረጃዉን ስወስድ መጥሪያ ስላልደረሰኝ ተጠሪ ክስ እንደመሰረቱብኝ አላዉቅም፡፡ስለሆነም ተጠሪ በሸያጭ ዉሉ ላይ በምስክርነት በመፈረም ካረጋገጡ በኋላ ቤቱ ተቀላቅሎ ተሸጥብኛል በማለት ዉል እንዲፈርስ ያቀረቡትን ክስ የስር ፍርድ ቤቶች ተቀብለዉ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡እንዲሁም ዉሉ ይፈርሳል ከተባለም መፍረስ የሚገባዉ ተጠሪ የእኔ ነዉ ያሉትን 5 ክፍል ሰርቪስ ቤችን በተመለከተ እንጂ ዋናዉን ቤት በተመለከተ ሊሆን ስለማይገባ ከዚህም አንጻር የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ በቀን 06/07/2008ዓ/ም የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል ተጠሪ በተገኙበትና ምስክ ሆነዉ በፈረሙበት ሁኔታ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ዉሉ እንዲፈርስ የተወሰነበት አግባብ ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 04/05/2014 ዓ/ም የተጻፈ መልሳቸውንን ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡-አመልካችና የስር 1ኛ ተከሳሽ የቤት ሽያጭ ዉል ሲፈራረሙ ተጠሪ የእኔ ቤት ጭምር እንደተሸጠ እያወቅሁ መፈረሜ አልተረጋገጠም፡፡አመልካች የቤት ሽያጭ ዉሉን ባደረጉበት ጊዜ 5 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ጭምር የስር 1ኛ ተከሳሽ ስለመሆናቸዉ ከተጠሪም ሆነ ከከተማ አስተዳደሩ አላረጋገጡም፡፡ከከተማ

አስተዳደሩ ያረጋገጡ ስለመሆኑ የሚያሳይ የጽሁፍ ማረጋገጫ አላቀረቡም፡፡ዉሉ የእኔን ሰርቪስ ቤቶችን ጨምሮ እንደተደረገ ሳዉቅ ዉሉ እንዲፈርስ መጠየቀ ተገቢ ነዉ፡፡ቤቱ በአመልካች ስም በቀን 15/07/2013ዓ/ም የተመዘገበዉ ተጠሪ ክስ መስርቼ በቤቱ ላይ በቀን 14/07/2013ዓ/ም እግድ ካሰጠሁ በኋላ ነዉ፡፡ተጠሪ ሻጭ ሆኘ 5ቱን ክፍል ቤቶች ሳልሸጥ አመልካች የቅን ልቦና ገዥ ነኝ ማለት አይችሉም፡፡አመልካች ዉሉ ሊፈርስ የሚገባዉ እነዚህን 5 ክፍል ቤቶችን ብቻ በተመለከተ ሊሆን ይገባል የሚል ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያላቀረበ ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም በማለት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ጭብጥ መሰረት በማድረግ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ በአመልካችና በስር 1ኛ ተከሳሽ ላይ በመሰረቱት ክስ ከወላጆቻቸዉ በስጦታ አገኘሁ ባሉት 150 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የሰሩትን 5 ክፍል ሰርቪስ ቤቶችን የስር 1ኛ ተከሳሽ ካላቸዉ መኖሪያ ቤት ጋር ቀላቅለዉ ለአመልካች በሽያጭ ማስተላለፋቸዉን ገልጸዉ ዉል እንዲፈርስ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡አመልካችና የስር 1ኛ ተከሳሽ ባሰሙት ክርክር በዉሉ ለአመልካች የተላለፈዉ ዋናዉ ቤትም ሆነ 5 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች የስር 1ኛ ተከሳሽ ንብረት እንደሆነና በዉሉም ላይ ተጠሪ በምስክርነት በመፈረም ይህንኑ ስላረጋገጡ ዉሉ እንዲፈርስ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡የግራ ቀኙ ክርክር ይህ እስከሆነ ድረስ በጭብጥነት ተይዘዉ በማስረጃ ተረጋግጦ ዉሳኔ ሊሰጥባቸዉ የሚገቡ ጭብጦች የስር 1ኛ ተከሳሽ ቤታቸዉን ለአመልካች በሽያጭ ሲያስተላልፉ የተጠሪን 5 ክፍል ሰርቪስ ቤቶችን ጨምረዉ አስተላልፈዋል ወይ ?አመልካች የሽያጭ ዉሉን ከመዋዋላቸዉ በፊት 5 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ጭምር የስር 1ኛ ተከሳሽ ንብረት መሆናቸዉን ተገቢዉን ጥንቃቄ አድርገዉ አረጋግጠዋል ወይስ አላረጋገጡም? 5 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች የተጠሪ መሆናቸዉ ከተረጋገጠ ተጠሪ በሽያጭ ዉሉ ላይ በምስክርነት መፈረማቸዉ በዉሉ ሰርቪስ ቤቶቹን አስተላልፈዋልና ዉሉ ፀንቶ ሊቀጥል ይገባል የሚያስብል ምክንያት ነዉ ወይስ አይደለም? የሚሉ ጭብጦች ናቸዉ፡፡

በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 258-260 እና በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2001 ስር እንደተደነገገዉ እና አንድን ፍሬ ነገር ማስረጃ አቅርቦ የማስረዳት ሸክምን ከሚመለከተዉ መሠረታዊዉ መርህ (Basic Principle of Burden of Proof) መረዳት እንደሚቻለዉ አንድ አከራካሪ ፍሬ ነገር አለ ወይም የለም ብሎ

የሚከራከር ሰዉ ፍሬ ነገሩ መኖሩን ወይም አለመኖሩን በማስረጃ የማስረዳት ሸክም(ግዴታ) አለበት፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ተገቢዉን ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት የሚጠበቅባቸዉ የስር 1ኛ ተከሳሽ በሽያጭ ያስተላለፉት 5 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች የእሳቸዉ ንብረት መሆኑን ሲሆን አመልካች ማስረዳት የሚጠበቅባቸዉ ደግሞ በሽያጭ ከስር 1ኛ ተጠሪ የገዙት ዋናዉ ቤት ብቻ ሳይሆን 5 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ጭምር የስር 1ኛ ተከሳሽ ባለሀብት የሆኑበት እንደሆኑ ተገቢዉን ጥንቃቄ አድርገዉ አረጋግጠዉ መግዛታቸዉን ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ስር እንደተመለከተዉ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ሥልጣን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ዉሳኔ እንዲያርም ነዉ፡፡በዚህ መልኩ በተሰጠዉ ሥልጣን ይህ ችሎት ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃ ለመቀበል፣ ለመስማትና ለመመዘን ሥልጣን ለተሰጣቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች ያቀረቡትን ማስረጃዎች የመመዘን ጉዳይ ዉስጥ በመግባት ማስረጃዎችን በመመርመርና በመመዘን አከራካሪ የሆነ የፍሬ ነገር ጭብጥ መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ አይችልም፡፡ሆኖም የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትን፣ ተቀባይነትን እና ማስረጃ አቅርቦ አንድን ፍሬ ነገር የማስረዳት ሸክም መርህ (Production, relevancy, admissibility and burden of proof of evidence)እንዲሁም የማስረጃ ምዘናን ወይም የማስረዳት ደረጃን (standard of proof or weight of evidence) የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች ተጥሶ የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ሲኖር መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሚሆን በሰበር ሰሚ ችሎት የሚታረም ይሆናል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ማስረጃን የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን የተሰጠዉ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት 5 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች የተጠሪ ንብረት እንደሆኑ እና የስር 1ኛ ተከሳሽ የራሳቸዉን ዋና ቤት ሲሸጡ እነዚህን 5 ክፍል ሰርቪስ ቤቶችን ጨምረዉ መሸጣቸዉን እንዲሁም አመልካችም 5ቱ ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ጭምር የስር 1ኛ ተከሳሽ መሆናቸዉን በአግባቡ ከሚመለከተዉ አካል ማረጋገጫ ሳያገኙ እንደገዙ ያረጋገጣቸዉ ፍሬ ነገሮች ናቸዉ፡፡ አመልካች 5ቱ ክፍል ሰርቪስ ቤቶች የስር 1ኛ ተከሳሽ ንብረት ስለመሆናቸዉና ይህንንም ከሚመለከተዉ አስተዳደር አካል በተሰጣቸዉ ማስረጃ አረጋግጠዉ መግዛታቸዉን የሚያሳይ ተጠሪ ካቀረቡት ማስረጃዎች በተሻለ ሁኔታ የሚያሳምን ማስረጃ አቅርበዉ ተቀባይነት ማጣታቸዉን ወይም በዚህ ረገድ ያቀረቡት ማስረጃ ተገቢዉ ዋጋ ተሰጥቶ ሳይመዘን የታለፈባቸዉ ስለመሆኑ በግልጽ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ እንዲሁም አመልካችም ቤቱን ከስር 1ኛ ተከሳሽ ሲገዙ በተለይም የ5 ክፍል ሰርቪስ ቤቶት ባለሀብት የስር 1ኛ ተከሳሽ መሆናቸዉን የሚያሳይ ምን ምን ማስረጃዎችን እንደተመለከቱና ለስር ፍርድ

ቤትም እነዚህን ማስረጃዎች በማስረጃነት እንዳቀረቡ ክርክራቸዉ በግልጽ ስለማያሳይ ቤቱን ተገቢዉን ጥንቃቄ አድርገዉ ገዝተዋል ለማለት አያስችልም፡፡ስለሆነም በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል ከማስረጃ አቀባበልና ምዘና መርሆዎች አተገባበር አንጻር የተፈጸመ ስህተት አልተገኘም፡፡

በተጨማሪም አንድ ሰዉ በዉርስ እና በሌላ ሕግ በልዩ ሁኔታ በተደነገገዉ አግባብ ካልሆነ በስተቀር ባለሀብት የሆነበትን ንብረት በልዩ ልዩ መንገድ ማስተላለፍ የሚችለዉ በራሱ እና የዉክልና ሥልጣን በሰጠዉ በሌላ ሰዉ አማካኝነት ነዉ፡፡ በተለይም ንብረቱ በሽያጭ ሲተላለፍ ራሱ ወይም የዉክልና ሥልጣን የተሰጠዉ ሰዉ ስለእርሱ በመሆን ተዋዋይ ካልሆነ በስተቀር ንብረቱን በሽያጭ አስተላልፏል ሊባል አይችልም፡፡ አመልካች ንብትነታቸዉ የተጠሪ የሆኑትን 5 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች የስር 1ኛ ተከሳሽ የሸጡልኝ በተጢ ስም በተጠሪ በተሰጣቸዉ የዉክልና ስልጣን ነዉ በማለት ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡እንዲሁም ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ የሽያጭ ዉል ላይ ተጠሪ ተዋዋይ(ሻጭ) በመሆን ተሳትፈዋል የሚል ክርክር በአመልካች አልቀረበም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ እንዲፈርስ በጠየቁት ዉል ላይ ተዋዋይ ወገን እስካልሆኑ ድረስ ሰርቪስ ቤቶቹ ተጨምረዉ በተሸጡበት የቤት ሽያጭ ዉል ላይ በምስክርነት መፈረማቸዉ በሰርቪስ ቤቶቹ ላይ ያላቸዉን የባለሀብትነት መብት በሽያጭ አስተላልፈዋል የሚያሰኝ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል አንድ ሰዉ አንድን ንብረት በሽያጭ ለሌላ ሰዉ ሊያስተላልፍ የሚችለዉ በንብረቱ ላይ ትክክለኛ ሕጋዊ ባለመብት ሲሆን ወይም በሕጉ አግባብ የንብረቱ ሕጋዊ ባለመብት የሆነዉ ሰዉ ንብረቱን የመሸጥና የመለወጥ የዉክልና ወይም በሕግ የሚታወቅ ሌላ ሥልጣን የሰጠዉ እንደሆነ ነዉ፡፡በዚህ አግባብ የንብረቱ ባለሀብት ሳይፈቅድ የሌላዉን ሰዉ ንብረት ንብረቱ ነዉ ብሎ መሸጥ በሕግ ተቀባይነት ስለማይኖረዉ ዉሉን ፈራሽ የሚደርግ ነዉ፡፡ገዢዉ በሙሉም ሆነ በከፊል ከንብረቱ የሚነቀለዉ ወይም ለሕጋዊ ባለመብቱ እንዲለቅ የሚደረገዉም በዚህ ምክንያት ነዉ፡፡የተሸጠዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሻጩ ሀብት ሳይሆን የሌላ ሰዉ ሀብት ሆኖ ከተገኘ ገዢዉ የሚኖረዉ መብት ሻጩን መጠየቅ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2884 እና 2285 ስር የተደነገገዉ ያስገነዝባል፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ከእንዲህ አይነት ጉዳይ ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁጥር 51034(ቅጽ 11 ላይ እንደታተመዉ) ላይ እና በሰ/መ/ቁጥር 216482(ያልታተመ) ላይ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተጠሪ ንብረት በሆኑት 5 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች በተመለከተ የተደረገዉ የዉሉ ክፍል ዉሉ እንዲፈርስ ወስኖ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የጸናዉ ዉሳኔ ሕግንና ተጠቃሾቹን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ያደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል ስህተት የተፈጸመበት አይደለም፡፡ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 324590 ላይ በቀን 25/06/2013ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 375013 ላይ በቀን 08/10/2013ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንተዋል፡፡

2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

ት እ ዛ ዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 211647

ግንቦት 24 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ወ/ሮ ላምሮት ዘለቀ - ከጠበቃ ተፈሪ ከበደ ጋር ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ መንበረ ወንድምኩን- ቀርቧል

2ኛ. አቶ አበራ ተክሌ- አልቀረቡም

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በአመልካች እና 2ኛ ተጠሪ መካከል ጥር 12 ቀን 2002 ዓ/ም በተደረገ የጋብቻ ውል 2ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ከመጋባቱ በፊት በስጦታ ያገኘውን ቤትና ይዞታ እንዲሁም በጋብቻ ውስጥ እያሉ የሚያፈሩት ንብረት የጋራ መሆኑን በአመልካች እና 2ኛ ተጠሪ መካከል ግልጽ የጋብቻ ስምምነት ውል መኖሩ ባልተካደበትና ይህንኑ ለማስረዳት የቀረበው የሰውና የሰነድ ማስረጃ በአግባቡ ሳይመረመር የአመልካችን መብትና ጥቅም እንዲሁም የንብረት ባለቤትነት በማሳጣት የሥር ፍርድ ቤቶች ለአንድ ወገን ብቻ ያጋደለ በሚመስል መልኩ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት በሰበር ለማሳረም ሐምሌ 22 ቀን 2013 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት መዝገቡ ለችሎት ሊቀርብ ችሏል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጉዳዩ በተጠሪዎች መካከል የነበረው እንደባልና ሚስት ግንኙነት በመቋረጡ የግንኙነቱ ውጤት የሆነው የንብረት ክርክር ተደርጎ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ አመልካች ፍርዱን በመቃወም ባቀረቡት አቤቱታ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጀመረ ክርክር ሲሆን ፤ የአመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ይዘት በአጭሩ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ጥር 12 ቀን 2002 ዓ/ም በሀገር ባህል ጋብቻ ሲፈፅሙ በዚሁ ዕለት በተደረገ የጋብቻ ውል 2ኛ ተጠሪ ከጋብቻው በፊት በስጦታ ያገኙትን በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 በ226 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ያረፈ 20 ቆርቆሮ ቤት እና ከጋብቻ በኋላ የሚያፈሩትን ንብረት የጋራ ለማድረግ ስምምነት ማድረጋቸውንና በጋብቻ ውስጥ እያሉ ብድር ወስደው ተጨማሪ 9 ክፍሎች እና የውጭ በር ማስራታቸውን በመግለፅ የተጠሪዎች የጋራ ሀብት ነው በማለት ፍርድ ያረፈበት ቤትና የቤት ቁሳቁስ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያፈሩት ንብረት በመሆኑ እነዚህን ንብረቶች አስመልክቶ ፍትሐዊ ውሳኔ ይሰጠኝ የሚል ነው፡፡ 1ኛ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን በማስቀደም በፍሬ ነገር ክርክሩም በሰጡት መልስ የብድር ውል በማለት የቀረበው ሰነድ እውነት ቢሆን ኖሮ 2ኛ አመልካች ጋር አስቀድሞ ባደረጉት ክርክር በማስረጃነት ሊቀርብ ይችል የነበረ ሲሆን አመልካች ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ ክርክር 2ኛ ተጠሪ እውቅና ሰጥቶት ያላነሳው የጋብቻ እና የብድር ውሉ በተጠሪዎች መካከል የነበረው ክርክር ውሳኔ ካገኘ በኋላ የተፈረመ በመሆኑና ጽሑፉም በተመሳሳይ የዕጅ ጽሑፍ የተፃፈ እና የቆየ ሰነድ ባለመሆኑ ውሉሎቹን በመንተራስ አመልካች ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪም በመልሳቸው ከአመልካች ጋር ጥር 12 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ክሱ እስከ ቀረበበት ጊዜ ድረስ በህጋዊ መንገድ ተጋብተው የሚኖሩ መሆኑ በማስረጃ ተደግፎ የቀረበ መሆኑና አመልካች ባለቤታቸው በመሆኗ በሁለቱም ስም በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤትም ካርታ ተሰርቶ መኖሩን ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በ1ኛ ተጠሪ በኩል የቀረበው የመጀመሪ ደረጃ መቃወሚያን ወድቅ ካደረገ በኋላ ለክርክሩ ዕልባት ለማስጠት ያስችለኛል ያለውን ጭብጥ ይዞ ማስረጃ ሰምቶና ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት አድርጎ መዝገቡን እንደመረመረው 2ኛ ተጠሪ በስጦታ ያገኙት እና ከአመልካች ጋር ጋብቻ ሲፈጽሙ የጋራ ካደረጉት በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ልዩ ስሙ ፀደ በተባለ ቦታ የሚገኝ በ226 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ያረፈ 20 ቆርቆሮ ቤት ውጪ ተጠሪዎች ከ1996 ዓ/ም - 2002 ዓ/ም ድረስ እንደባልና ሚስት አብሮ ሲኖሩ 6(ስድስት) ክፍል ቤቶችን መሥራታቸው በምስክር የተረጋገጠ ሲሆን ከየካ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማት ማኔጅመንት ጽ/ቤት የይዞታ አስተዳደር ሽግግር መስተንግዶ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የቀረበው ማስረጃ በአመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ስም ካርታ እየተዘጋጀ መሆኑንና በካርታው ላይ ከሚታዩ ቤቶች ውጪ ሌሎች ቤቶች መኖራቸውን በ1997 ዓ/ም እና 2003 ዓ/ም የተነሳው የአየር ካርታ የሚያመለክት መሆኑን ጠቅሶ ሪፖርት ማድረጉን ገልፆ ፤ ተጠሪዎች ከ1996 ዓ/ም - 2002 ዓ/ም ድረስ እንደባልና ሚስት አብሮ ሲኖሩ 2ኛ ተጠሪ በስጦታ ባገኙት ይዞታ ላይ ከላይ 3(ሶስት) እና ከታች 3(ሶስት) 6(ስድስት) ተደራራብ ክፍል ቤቶችን መሥራታቸው በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች አስቀድሞ ተጠሪዎች ያፈሩትን ንብረት የመጋራት መብት የሌላቸው በመሆኑ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 አስተዳደር በ2ኛ ተጠሪ ስም ካርታ በዝግጅት ላይ የሚገኘው በ226 ካ.ሜ ይዞታ

ላይ ያረፈው 6 ክፍል መኖሪያ ቤት ከላይ 3 ከፍል ከታች 3 ክፍል የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ነው በማለት አስቀድሞ የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል። ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራካሮ እና የካ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማት ማኔጅመንት ጽ/ቤት ጉዳዩን እንዲያጣራ በሰጠው ትዕዛዝ በ1997 በተነሳው አየር ካርታ 6 ክፍሎች መኖራቸውን እንደሚያሳይ በመግለጽ ሪፖርት ማድረጉን ጠቅሶ የሥር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል።

አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት በሰበር ለማሰረም ያቀረቡትን በፍርዱ መግቢያ ላይ የተመለከተውን የሰበር አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ በአመልካች የመቃወሚያ አመልካችነት በመጀመሪያ ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 358(2) መሠረት ከተሻሻለ የአመልካችን ድርሻ አስመልክቶ ምንም ሳይባል የመታለፉ አግባብነት መጣራት አላበት በማለቱ 1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ፡- በአመልካች እና 2ኛ ተጠሪ መካከል ተደርጓል ተብሎ የቀረበው የጋብቻ ውል በተጠሪዎች መካከል የንብረት ክፍፍል ከተደረገ በኋላ በተመሳሳይ የእጅ ጽሑፍ የ1ኛ ተጠሪን መብት ለማጣበብ በሀሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሰነድ መሆኑን ፣ አከራካሪው ቤት ተጠሪዎች እንደባልና ሚስት አብሮ በኖሩበት ከ1995 ዓ/ም እስከ 2002 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ የተሰሩ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ከማስረጃ ሚዘና አንፃር የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ባለመኖሩ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ፀንቶ ወጪና ኪሳራ በቁርጥ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል። 2ኛ ተጠሪ የፍርድ ቤት መጥሪያ መኖሪያ ቤታቸው ላይ መለጠፉ ማረጋገጫ ቀርቦና ተጠሪውም መጋቢት 27 ቀን 2014 ዓ/ም መልስ ሳይዙ ፍርድ ቤት ቀርበው የነበረ መሆኑ ተረጋግጦ በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል። አመልካች በሰጡት የመልስ መልስ ክርክር በተነሳበት 226 ካ.ሜ ይዞታ ላይ የተሰሩ ቤቶች ብዛት 12 ክፍሎች ሲሆኑ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ አስቀድሞ የሰጠውን ውሳኔ አሻሽሎ ስድስቱ ክፍሎች የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ነው በማለት ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም ፤ ቀሪዎቹ 6 ክፍሎች የማን እንደሆኑ ሳይወስን ማለፉ ስህተት ሲሆን የጠየቁት ዳኝነት በዝምታ መታለፉን በመቃወም ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታም በይግባኝ ሰሚው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ታልፎ የሥር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን መጽናቱ አግባብነት የለውም በማለት ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፊ ሲል የተመለከተውን ሲመለከት ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን የሰበር ቅሬታው ያስቀርባ ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው ተመርምሯል። አመልካች በተጠሪዎች መካከል የነበረው እንደባልና ሚስት ግንኙነት በመቋረጡ የግንኙነቱ ውጤት በሆነው የንብረት ክርክር ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥዓት ሕጉ ቁጥር 358 መሠረት የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ሲያቀርቡ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በባህል ሥርዓት ጥር 12 ቀን 2002 ዓ/ም ጋብቻ ሲፈፅሙ በፅሉቱ በተደረገ የጋብቻ ውል ለ2ኛ ተጠሪ በስጦታ የተላለፈላቸው በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 አስተዳደር በ226 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ያረፈው 20 ቆርቆሮ ቤት የጋራ በማድረግ በጋብቻ ውስጥ እያሉ ብድር ወስደው ተጨማሪ 9 ክፍል ቤቶችን ያሰሩ መሆኑና የውጪ በር ማሰራታቸውን በመግለጽ አስቀድሞ በተጠሪዎች መካከል በተደረገው ክርክር ውሳኔ ያረፈበት ንብረት

ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የጋራቸው መሆኑን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ አለን የሚሉት ንብረት ከጥር 2002 ዓ/ም በተደረገ የጋብቻ ውል የጋራ የሆነውንና በትዳር ውስጥ እያሉ አፈራን የሚሉትን ንብረት ሲሆን ፤ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ከ1996 ዓ/ም - 2002 ዓ/ም ድረስ እንደባልና ሚስት አብሮ ሲኖሩ 2ኛ ተጠሪ በስጦታ ባገኙት ይዞታ ላይ ከላይ 3(ሶስት) እና ከታች 3(ሶስት) በድምሩ 6(ስድስት) ክፍል ተደራራብ ቤቶችን መሥራታቸው በማስረጃ አረጋግጦ አመልካች አስቀድሞ ተጠሪዎች እንደባልና ሚስት አብሮ በሚኖሩበት ጊዜ ከተፈራው ንብረት ላይ መብት የላቸውም በማለት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ካለመሆኑም በላይ አመልካችም በዚህ አግባብ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ የላቸውም፡፡ የአመልካች ቅሬታ በመልስ መልሳቸው ላይ በግልጽ እንዳስቀመጡት ለክርክሩ ምክንያት በሆነው 226 ካ.ሜ ይዞታ ላይ የተሰሩ ቤቶች ብዛት 12 ሲሆኑ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እሳቸው ባቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ አስቀድሞ የሰጠውን ውሳኔ አሻሽሎ 6 ክፍል ቤቶችን የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ነው በማለት ውሳኔ ሲሰጥ በቀሪዎቹ 6 ክፍሎች ላይ ውሳኔ ሳይሰጥ መታለፉና ውሳኔው አመልካች ባቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ቢሻሻልም የእሳቸውን መብት በሚመለከት ግልጽ ውሳኔ አለመሰጠቱ ተገቢነት የለውም በሚል ነው፡፡ አመልካች የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ነው ከተባሉት 6 ክፍሎች ውጪ ውሳኔ ያላረፈባቸው ተጨማሪ 6 ክፍሎች አሉ በማለት ያቀረቡት ክርክር የማስረጃ ድጋፍ ያለው መሆኑን መዝገቡ አያመለክትም፡፡ አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ጥር 12 ቀን 2002 ዓ/ም መጋባታቸውና በዚሁ ዕለት በተደረገ የጋብቻ ውል 2ኛ ተጠሪ ከጋብቻው በፊት የነበራቸውን ንብረት የጋራ ማድረጋቸው እንዲሁም በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ ስም ካርታ እየተዘጋጀ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ከመሆኑ አንፃር ፤ ምንምእንኳን የጋብቻ ውሉ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር አስቀድሞ ባፈሩት ንብረት ላይ አመልካችን መብት የማያጎናጽፍ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ከዚህ አንፃር የሚነቀፍ ባይሆንም ፤ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ጋብቻ ሲመሰርቱ በጋብቻ ውሉ ያገኙትን መብት በውሳኔው የሚያጡበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በተጠሪዎች መካከል በተደረገ የንብረት ክርክር መጋቢት 30 ቀን 2008 ዓ/ም የተሰጠው ፍርድ ላይ አመልካች ታህሳስ 27 ቀን 2009 ዓ/ም ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ታይቶ ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በተሰጠ ውሳኔ የቀድሞ ውሳኔ መሻሻሉ ቢገለፅም ፤ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ጥር 12 ቀን 2002 ዓ/ም ሲጋቡ ከተደረገ የጋብቻ ውል አንፃር ያላቸው መብት በግልጽ መቀመጥ ሲገባው በደፈናው አስቀድሞ መጋቢት 30 ቀን 2008 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል ተብሎ ከምን አንፃር የቀድሞ ውሳኔ እንደተሻሻለ በግልጽ አለመቀመጡ ስህተት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 237566 ሐምሌ 7 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ እንዲሁም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 99876 ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው የሰጠው ፍርድ ፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ***ተሻሽሏል***፡፡

2. በተጠሪዎች መካከል በተደረገው የንብረት ክርክር በመዝገብ ቁጥር 99876 ላይ መጋቢት 30 ቀን 2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት የተሰጠው ውሳኔ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ጥር 12 ቀን 2002 ዓ/ም ሲጋቡ በተደረገ የጋብቻ ውል ያገኙትን መብት የሚያሳጣ አይደለም፡፡
3. ተጠሪዎችን የሚመለከተው ቀሪው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
4. በዚህ መዝገብ ላይ መስከረም 11 ቀን 2014 ዓ/ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
5. በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁ. 211654
ቀን ፡- የካቲት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- መዓዛ አፈወርቅ የእንጨት መሰንጠቂያ፣ የቤትና የቢሮ እቃዎች ማምረቻ ድርጅት፡- ጠበቃ ጋሻዬ አወቀ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ስማቸው ባዩህ፡- ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ በግል የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር የሥራ ውል መቋረጡ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ከ2007 ዓ/ም ጀምሮ ተቀጥሬ ስሰራ የ2010 ቅጥረኛ ፎርም እንድሞላ በመጠየቅ ለዚህም ፈቃደኛ ባለመሆኔና መብቴን በመጠየቄ አመልካች የሥራ ውሌን ከሕግ ውጭ ስላቋረጠ ካሣ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ክፍያ፣ ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት እና የዓመት ዕረፍት ክፍያ እንዲከፍላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ያቀረበው መልስ የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው የድርጅቱ ሥራ በመቀነቀዙና ሁኔታው ለተጠሪ ተገልጾና

ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ እንዲሁም የአገልግሎት ክፍያ ተከፍሎ የተፈጸመ የሥራ ውል ማቋረጥ ተግባር ስለሆነ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 90858 የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት የአመልካች ምስክሮች የድርጅቱ ሥራ መቀዛቀዙን አስረድተዋል፡፡ የተጠሪ ምስክሮች የተሰናበቱት ውል ፈርሙ በመባላቸው መነሻነት ስለመሆኑ ያስረዱ ቢሆንም ምስክሮች በአመልካች ድርጅት ሲሰሩ የነበሩና የለቀቁ ከመሆናው አንጻር እምነት የሚጣልበት አይደለም፡፡ አመልካች በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሀ) መሠረት የሠራተኛ ቅነሳ ተግባር መፈጸሙ ሕጋዊ ነው በማለት ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡትን ይግባኝ የተቀበለው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮ እና ማስረጃውን በድጋሜ መዝኖ የተጠሪ ምስክሮች ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት ደመወዝ ቀንሰው የሥራ ውል ፈርሙ በመባላቸውና ፈቃደኛ ባለመሆናቸው መሆኑን አስረድተዋል፤ ምስክሮቹ ቀደም ሲል የአመልካች ድርጅት ተቀጣሪ ሠራተኛ መሆናቸው እምነት እንዳይጣልባቸው የሚያደርግ አይደለም፡፡ አመልካች ይህን ማስረጃ አላስተባበለም፡፡ የአመልካች ምስክሮች የድርጅቱ ሥራ ስለመቀዛቀዙ ያስረዱ ሲሆን ስራው በመቀዛቀዙ የተሰናበቱ ሠራተኞች ስም ዝርዝርም በሠነድ ማስረጃነት ቀርቧል፡፡ ነገር ግን የቀረበው ማስረጃ የድርጅቱን ሠራተኛ አቅርቦ ሥራው ቀዝቅዟል ከማለት ባለፈ ሥራው በትክክል ስለመቀዝቀዙና በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሀ) መሠረት ተጠሪን ከሥራ ሊያስቀንስ የሚችል ሁኔታ መከሰቱን በአግባቡ አላስረዳም፡፡ የሥራ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው፤ ተጠሪ የሥራ ውላቸው ሲቋረጥ የሥራ ስንብት ክፍያ የተከፈላቸውና ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው በመሆኑ ያልተከፈላቸው የስድስት ወር ደመወዘ በካሣ መልክ ብር 26,520.00 አመልካች ሊከፍላቸው ይገባል በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሯል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም ነበር፡፡ የድርጅቱ ተፈላጊነትን መቀነስን አስረድተን በሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ እያለ ሕገ-ወጥ ስንብት መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የማስረጃ ምዘና መርሕ ስህተት ያለበት ነው የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የሥራ ስንብቱ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28 አንጻር አግባብነቱን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ያዘዘ ሲሆን ባቀረቡት መልስ የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታው ምክንያቱና ማስረጃው ተመዝኖ በአግባቡ የተወሰነ ነው፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃ ምዘናን አይመለከትም፡፡ ከሥራ የተሰናበትኩት የደመወዝ መጠኑ ተቀንሶ ውል እንድፈርም በማዘዙና ባለመቀበሌ ስለመሆኑ በሚገባ አስረድቻለሁ፤ አመልካች የድርጅቱ ሥራ ስለመቀዛቀዙ አለማስረዳቱ ተረጋግጦ የተወሰነ ውሳኔ ስለሆነ ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የተጠሪዎች የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

በመጀመሪያ አመልካች ከይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ጋር አያይዞ ያቀረበውን ክርክር እንደተመለከትነው የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ራሱ ችሎ አቤቱታ ቀርቦበት ከይግባኙ መዝገብ በተለየ ፋይል ቀርቦ የሚወሰንና በውሳኔውም ላይ እንደሁኔታው የይግባኝ ሆነ የሠበር አቤቱታ ሊቀርብበት የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ይግባኝ ማስፈቀጃ አቅርበው የተፈቀደላቸው ስለመሆኑ ከግራቀኙ ክርክር የተገነዘብን ቢሆንም ውሳኔው ከዚህ የሰበር አቤቱታ ጋር ተያይዞ ያልቀረበና የሠበር አቤቱታው መነሻ ያደረገው የሥረ-ነገሩ ክርክር ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በመሆኑ አመልካች ከይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ጋር በተያያዘ ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

የጉዳዩን ሥረ-ነገር እንደመረመርነው ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ከ2007 ዓ/ም ጀምሮ ተቀጥሬ ስሰራ የ2010 ቅጥረኛ ፎርም እንድሞላ በመጠየቅ ለዚህም ፈቃደኛ ባለመሆኔና መብቴን በመጠየቄ አመልካች የሥራ ውሌን ከሕግ ውጭ አቋርጧል የሚል ሲሆን አመልካች በበኩሉ የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው የድርጅቱ ሥራ በመቀዛቀዙና ሁኔታው ለተጠሪ ተገልጾና ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ እንዲሁም የአገልግሎት ክፍያ ተከፍሎ የተፈጸመ የሥራ ውል ማቋረጥ ተግባር ስለሆነ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሠረት የሥራ ውል የሚቋረጠው አንደኛው በሕግ ወይም በሥምምነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተዋዋይ ወገኖች አነሳሽነት ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 24 በሕግ መሠረት ውል የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች ተዘርዝረዋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 25 ደግሞ በሥምምነት ውል ስለሚቋረጥበት ሁኔታ ይገልጻል፡፡ በአሠሪው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበት ሁኔታ በአዋጁ ከአንቀጽ 26-30 በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 31 እና 32 ደግሞ በሠራተኛው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበትን ሁኔታ ደንግጓል፡፡ የአዋጁ ድንጋጌ አንቀጽ 31 በአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ለአሠሪው በመስጠት ሠራተኛው ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል የሚገልጽ ነው፡፡ ሌላው በሠራተኛው አነሳሽነት የሚፈጸም የሥራ ውል ማቋረጥ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 32(1)(ሀ እስከ ሐ) የተመለከተ ሲሆን በሕጉ የተዘረዘሩት ምክንያቶች አሠሪው የሠራተኛውን ሠብዓዊ ክብርና ሞራል መንካቱ፣ በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር በሠራተኛው ላይ መፈጸም፣ ለሠራተኛው ደኅንነት ወይም ጤንነት አደጋ ሊያደርስ የሚችል ምክንያት እያለ አሠሪው ተገቢውን እርምጃ ካልወሰደ ወይም ሌላ አሠሪው ለሠራተኛው መፈጸም ያለበትን ግዴታ በመደጋገም ካልፈጸመ ሠራተኛው ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ማቋረጥ የሚችልበትን ሁኔታ አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ ማዕቀፎች ውጭ አሠሪው ሠራተኛን ከሥራ ሲያሰናብት ሕገ-ወጥ የሥራ ስንብት ይሆናል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት የአመልካች ምስክሮች የድርጅቱ ሥራ መቀዛቀዙን አስረድተዋል፤ የተጠሪ ምስክሮች የተሰናበቱት ውል ፈርሙ በመባላቸው

መነሻነት ስለመሆኑ ያስረዱ ቢሆንም ምስክሮች በአመልካች ድርጅት ሲሰሩ የነበሩና የለቀቁ ከመሆናው አንጻር እምነት የሚጣልበት አይደለም፤ አመልካች በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሀ) መሠረት የሠራተኛ ቅነሳ ተግባር መፈጸሙ ሕጋዊ ነው በማለት ክሱን ውደቅ ያደረገ ሲሆን ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በበኩሉ ማስረጃውን በድጋሜ መዝኖ የተጠሪ ምስክሮች ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት ደመወዝ ቀንሰው የሥራ ውል ፈርሙ በመባላቸውና ፈቃደኛ ባለመሆናቸው መሆኑን አስረድተዋል፤ ምስክሮቹ ቀደም ሲል የአመልካች ድርጅት ተቀጣሪ ሠራተኛ መሆናቸው እምነት እንዳይጣልባቸው የሚያደርግ አይደለም፡፡ አመልካች ይህን ማስረጃ አላስተባበለም፤ የአመልካች ምስክሮች የድርጅቱ ሥራ ስለመቀዛቀዙ ያስረዱ ሲሆን ስራው በመቀዛቀዙ የተሰናበቱ ሠራተኞች ስም ዝርዝርም በሠነድ ማስረጃነት ቀርቧል፤ ነገር ግን የቀረበው ማስረጃ የድርጅቱን ሠራተኛ አቅርቦ ሥራው ቀዝቅዟል ከማለት ባለፈ ሥራው በትክክል ስለመቀዝቀዙና በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሀ) መሠረት ተጠሪን ከሥራ ሊያስቀንስ የሚችል ሁኔታ መከሰቱን በአግባቡ አላስረዳም፤ የሥራ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ሲል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ በፍትሐ ብሔር ክርክር የምንከተለው የማስረዳት ደረጃ ከሁለቱ ወገን የተሻለ ያስረዳው ማን ነው (preponderance of evidence) የሚለውን በመለየት፣ የማስረጃ ተገቢነት (relevancy test)፣ የማስረጃው ተቀባይነትን (admissibility) ደንቦችን መከተል እና ለማስረጃው የሚሰጠውን ክብደት (weight of evidence) በመለየት የመወሰን ኃላፊነት ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ቤቶች ዋና ተግባር ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃ ለመመዘን በተሰጠው ኃላፊነት ተጠሪ የተሰናበቱት ደመወዝ ቀንሰው የሥራ ውል ፈርሙ በመባላቸውና ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ስለመሆኑ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የማስረጃ ምዘና ሂደት የተፈጸመ የማስረጃ ሕግና ማስረጃ ምዘና መርሕ ጥሰት መኖሩን የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡ ስለሆነም የተጠሪ የሥራ ውል ከሕግ ውጭ ስለተቋረጠ ካሣ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 267829 ሰኔ 22 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

❖ የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

- አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠ እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ን

የሰ/መ/ቁጥር 211689
ግንቦት 29 ቀን 2014ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የደቡብ ክልል ዐ/ሕግ

ተጠሪዎች፡-1) በረከት በየነ

2) ተስፋዬ ጋልቾ

የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 34474 ግንቦት 6ቀን 2013ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንዲታረምለት አመልካች በመጠየቁ ነው፡፡

ጉዳዩ የሰው መግደል ወንጀል የሚመለከት ክስን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነበር፡፡ የአሁን አመልካች ጳጉሜ 4ቀን 2011ዓ/ም በተፃፈ ክሱ 1ኛ ተጠሪን 3ኛ ተከሣሽ 2ኛ ተጠሪን ደግሞ 5ኛ ተከሣሽ በማድረግ ተጠሪዎች ከሌሎች ተከሣሾች ጋር ሆነው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ) እና 540 የሚደነግገውን ተላልፈው የካቲት 24ቀን 2011ዓ/ም ከምሽቱ በ2ሰዓት አረካ ከተማ ቀበሌ 04 ትምህርት ቤቶች ፅ/ቤት ፊት ለፊት ሟች አዲሱ በለጠን 4ኛ ተከሣሽ ስሙን ጠርቶ እንዲቆም አድርጎ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ለስላምታ የሚችን እጅ ጨብጦ እንደያዘው፤ 1ኛ ከሣሽ ከኋላ በኩል በፌሮ ብረት የኋላ ጭንቅላቱን 2 ጊዜ ሲመታው፤ 2ኛ ተከሣሽ በጌጠኛ ድንጋይ (ኮብል ስቶን) የግራ ጭንቅላቱን 3ኛ ተከሣሽ(1ኛ ተጠሪ) የሚችን ጀርባ በክራንች ሁለት ጊዜ፤ 5ኛ ተከሣሽ(ሁለተኛ ተጠሪ) ሚቹ እንደወደቀ ጉረሮውን እና ሆዱን ከረገጠው በኋላ ሮጠው ማምለጣቸውን ሚች በድብደባው ስለደከመ በዱቦ ሆስፒታል ሲታከም ቆይቶ መጋቢት 5ቀን 2011ዓ/ም መሞቱን በመዘርዘር የሰው መግደል ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ክስ አቅርቦባቸዋል። ተጠሪዎችና ሁሉም ተከሣሾች ክደው በመከራከራቸው አመልካች ክሱን ለማስረዳት ምስክሮቹንና የሕክምና ማስረጃ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪዎ በበኩላቸው መከላከያ ምስክሮችን አቅርበዋል።

ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የግራቀኙን ማስረጃ መርምሮ የ0/ህግ ምስክሮች በወንጀሉ ቦታ ነበር ብለው ተከሣሾች

እያንዳንዳቸው የፈፀሙትን ድርጊት የገለፁ ቢሆንም የሰጡት ምስክርነነት ቃል ልዩነት ያለበት ተመሣሣይ አለመሆኑን ለአብነት ያህልም፡- አንደኛ ምስክር የካቲት 23 ሄደው አድረው የካቲት 24 እንደተመለሱ ሲመሰክር ሁለተኛ ምስክር ደግሞ የካቲት 24 ሄደው በእለቱ መመለሣቸውን፤ 1ኛ ምስክሯ ለቤቱ ምርቃት የደስ ደስ ቅቤ ይዛ መሄዷን ሚች አንድ ሽህ ብር እንደሰጠ ሌሎች ግን አለመስጠታቸውን ስትመሰክር ሁለተኛ ምስክሩ ደግሞ ሁሉም ገንዘብ ብቻ እንደሰጡ መስክራቸው ለልዩነቱ ማሣያነት ተጠቅሰዋል። በሌላ በኩል ጩኸት ተሰምቶ የመጡትን የአካባቢው ሰዎች በጨለማ ምክንያት ለመለየት አለመቻላቸውን ከገለፁ በኋላ የተጠሪዎችን ግን መለየታቸውን መመስከራቸው እንዲሁም የፈፃሚዎችን ማንነት ለይተው በእለቱ ለፖሊስ ማስመዝገባቸውን የመሰከሩ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ባደረገው ማጣራት ለፖሊስ አለማስመዝገባቸው ማረጋገጡ ተዓማኒነታቸውን የሚያጠራጥር መሆኑን ጠቅሶ በጥቅሉ የአመልካች ምስክሮችም የሚች ወንድም እና እህት መሆናቸውም ተጠቃሎ ሲታይ በመመሳከር የመሰከሩ መሆናቸውን ማመኑን ተጠሪዎች በበኩላቸው ባቀረቧቸው መከላከያ ምስክሮች የአመልካችን ምስክሮች ማስተባበላቸውን ጠቅሶ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 149(2) መሰረት በነፃ እንዲሰናበቱ ወስኗል።

ይህን ውሣኔ መሰረት በማድረግ በአመልካች ይግባኝ ባይነት ጉዳዩ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት 1ኛና 2ኛ ተከሣሾች የነበሩት መልስ ሰጪዎች በሌሉበት የአሁን አመልካችንና ተጠሪዎችን የይግባኝ ክርክር እንዲሁም ማጣሪያ ምስክር አዳምጦ ከመረመረ በኋላ አንደኛ ተጠሪ በእግሩ ላይ ቀዶ ጥገና ተደርጎለት እናቱ ቤት የነበረ ስለመሆኑ በመከላከያ ማስረጃ አረጋግጣለሁ ብሎ ጭብጥ አስይዞ መከላኪያ ምስክሮች የሰጡት ቃል እና የሕክምና ማስረጃው በሌላ ቀን እንደተመረመረ የሚገልፅ መሆኑን የሚያሳይ ነው ሲል የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሮ ይግባኝ ያልተጠቀበት 4ኛ ተከሣሽ ሲቀር ሌሎችን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ)ና 540 ጥፋተኛ ብሎ የአሁን አንደኛ ተጠሪ በአስር ዓመት ፅኑ እስራት ሁለተኛ ተጠሪ ደግሞ ተሣትፎውን መሰረት በማድረግ በአምስት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል።

ይህ ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ያሉት ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ችሎቱ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮ በተጠሪዎች ላይ የጥፋተኝነት የመወሰኑን አግባብት ከማስረጃ ምዘና አንፃር ከመረመረ በኋላ

በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የተደመጡት ሁለት ማጣሪያ ምስክሮች የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሊያስለውጥ የሚችል ምስክርነት አለመስጠታቸውን፣ ችሎቱም ያረጋገጡለትን ፍሬ ነገር በፍርዱ ላይ አለማስፈሩን፤ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የዐ/ሕግ ምስክሮች የሰጡት ቃል ከመመዘን ይልቅ ተጠሪዎች መከላከያ ምስክሮች ላይ ማተኮሩን፤በስር ፍርድ ቤት 4ኛ ተከሣሽ የነበረው መጀመሪያ ለሚች በተደጋጋሚ ስልክ ደወለ በኋለም እጅን ይዞ ማስመታቱ በዐ/ህግ ምስክሮች ተረጋገጠበት የተባለው ተከሣሽ ወንጀሉ ሲፈፀም ቦታው እንዳልነበረ ተከላክሏል በሚል በስር ፍርድ ቤት የተወሰነውን ውሣኔ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አጽንቶ ሌሎችን ጥፋተኛ ናቸው ያለበትን ምክንያት በግልፅ አለመመዘገቡን፤ እንዲሁም ወንጀሉ ተፈፀመ በተባለበት ሰዓት አሚች ጋር ነበሩ የተባለው አምስት ወንድም እና እህቶች ሚች ሲደበደብ በፍርሀት ምክንያት እየሮጡ ወደ ቤታቸው መግባታቸውን የገለፁትን ምስክርነት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ማመኑ፤ተጠሪዎች በኩል ሚች ጠጥቶ ዲች ውስጥ ውድቆ እንደሞተ በክተማው መወራቱን በመከላከያነት ያላቀረቡት ቢሆንም ሚችና ተጠሪዎች ለድብድብ የሚያበቃ ፀብ ያልነበራቸው መሆኑ ተደምሮ ሲታይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማስረጃውን በአግባቡ ሣይመዝን ጥፋተኛ ማለቱ ገቢነት የለውም ሲል የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሮ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰላፀናው አመልካች ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል።

አመልካች ሐምሌ 21ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው በማስረጃ ምዘና መርህ የዐ/ህግ ማስረጃ ሊመዘን የሚገባው ሙሉ ይዘቱ እንጅ ለክሱ መሰረታዊ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ የተፈጠረ ልዩነቶች ላይ ብቻ አተኩሮ ማስረጃን በመመዘን ተከሣሾች በነፃ እንዲሰናበቱ መወሰኑ የማስረጃ ምዘና መሰረታዊ መርሆዎ ችን መሰረት ያላደረገ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መሆኑን ዘርዝሮ እንዲታረምለት ጠይቋል።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ከቀረበባቸው ክስ ተከላክለዋል ሲል በነፃ ያሰናበተበትን አግባብነት ከወ/ሕ/ቁጥር 23(2)ና 540 ድንጋጌ አኳያ እንዲመረመር ጉዳዩ ቀርቦልናል። ተጠሪዎች በበኩላቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይሁን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፈፀሙት መሰረታዊ የሆነ የማስረጃ ምዘና የለም ሲሉ ተከራክረዋል።

ክፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥ፣ የአመልካችን የሰበር ቅሬታ እና በማስቀረቢያ ነጥቡ ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ነበር። በመሆኑም አመልካች ከሚያቀርበው ክርክር በመነሣት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪዎች ከቀረበባቸው ክስ በነፃ እንዲሰናበቱ በሰጡት ውሣኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ለመወሰን ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው ተምርምሯል።

እንደተመረመረው ተጠሪዎች ከሌሎች ተከሣሾች ጋር በመሆን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ የሰው መግደል ወንጀል ፈፅመዋል ሲል ክስ አቅርቦባቸው ክደው ተከራክረዋል። በአመልካች ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት የሚች ቤተሰብ የሆኑ ሁለት ምስክሮችን እና የሕክምና ማስረጃ አቅርቧል። በቀረበው የወንጀል ክስ ላይ የተካደ ፍሬ ነገርን በማስረጃ አጣርቶ ማስረጃውንም መዝኖ እንዲወስን የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሲመዝን ምስክሮች በእለቱ ለፖሊስ

አስመዝግበናል ሲሉ የሰጡት ምስክርነት ሐሰነት መሆኑ በፖሊስ መረጋገጡን፣ ምስክሮች በሰጡት ምስክርነት የፈጠሩት ልዩነትን፣ ምስክሮች ከሚች ጋር ካላቸው ቅርብ የስጋ ዝምድ በአንድ በኩል በሌላ በኩል የተጠሪዎች መከላከያ ምስክሮች ወንጀሉ ተፈፀመ በተባለበት ጊዜ ተጠሪዎች በቦታው አለመኖራቸውን እምነት ሊጣልበት በሚችል አከኋን ማስረዳታቸውን መሰረት በማድረግ ተከላክለዋል ሲል በነፃ አሰናብቷል።

ይህን ውሣኔ በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በራሱ ያዳመጣቸውን ማጣሪያ ምስክሮች ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር በዝርዝር ሣይገልፅ የተጠሪዎች መከላከያ ምስክሮች በሰጡት ምስክርነት ተፈጥሯል የተባለውን ልዩነት መሰረት በማድረግ ተጠሪዎች አልተከላከሉም ሲል የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሯል። ሰበር ሰሚ ችሎቱ በበኩሉ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመሻር በስር ፍርድ ቤት የተሰሙት ምስክሮች የሰጡትን ምስክርት መዝኖ የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢነት የለውም፤ ይልቁንም ሰበር ሰሚ ችሎቱ የስር ፍርድ ቤት የአመልካች ምስክሮች የሰጡት ምስርነት ቃል በመመካከር ላይ የተመሰረተ ነው ሲል ከያዛቸው ምክንያቶች በተጨማሪ የራሱን ምክንያት በመጨመር የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሣኔ አፅንቷል።

በየደረጃው የሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የነበረውን ክርክር መርምረው የሰጡት ውሣኔ ቢለያዩም ለውሣኔቸው መሰረት የሆነው ግን በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ማስረጃ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። በመሆኑም ፍርድ ቤቶች የተለያዩት በማስረጃ ምዘና እንጅ በሌላ የሕግ አተረጓጎም ወይም በክርክር አመራር ወይም መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሊባሉ በሚችሉ ጉዳዮች አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

እንደሚታወቀው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን የመጨረሻ ውሣኔ በተሰጣቸው ማናቸውም ጉዳዩች ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተትን ማረም እንደሆነ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3) ይደነግጋል። አንድ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ጉዳይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚያሰኘው በአዋጅ ቁጥር 1234/2014 አንቀጽ 2(4) የተዘረዘሩት መመዘናዎችን የሚያሟላ ስህተት ሲገኝ ብቻ ነው።

በዚህ የሕግ መመዘኛ መሰረት የአመልካች ክርክር በየደረጃው የሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ምዘና ላይ የደረሱበትን መደምደሚያ መለያዬት መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 1234/2014 አንቀጽ 10(ሐ) እንደተደነገገው የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚጥስ ውሣኔ መሆኑን ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል የሰጠውን አስገዳጅ ውሣኔ የሚጥስ ውሣኔ መሆኑን አለያም በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 2(4)(ለ) እንደሚደነግገው ሕግን አላግባብ በመተርጎም ወይም ለጉዳዩ ተገቢነት የሌለውን ሕግ በመጥቀስ የተሰጠ ውሣኔ ስለመሆኑ የሚያሣይ ክርክር አላቀረበም። በመሆኑም ተከታዩን ውሣኔ በአብላጫ ድምጽ ተወስኗል።

ውሣኔ

1) የደ/ብ/ብ/ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 34474 ግንቦት 6ቀን 2013ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ በወ/መሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(ለ)(2)(ለ መሰረት ፀንቷል።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

ማ/አ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ 211693

ቀን፡- 30/11/2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሽምሱ ሲርጋጋ

ዓለማየሁ ሹናራ

ዋዚሞ ዋሲራ

አመልካች/ቾች/፡- ወ/ሮ ፀሐይነሽ ወርቁ ጠበቃ ራሄል ከፍያለው ቀረቡ

ተጠሪ ፡- እነ አቶ አርአያ በዛብህ

መዝገቡ ከቀጠሮ በፊት ሊቀርብልን የቻለው አመልካች/ቾች 23/11ቀን 2013 ዓ.ም የሰበር አቤቱታው ታይቶ ውሳኔ እስኪሚያገኝ ጊዜ ድረስ በፊደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት በመ/ቁ 268732 በ15/11/2013 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ አፈፃፀሙ ታግዶ እንዲቆይ ይታዘዝልን የሚል አቤቱታ በቃለ መሃላ አስደግፈው ስላቀረቡ ነው፡፡

አንድ ጉዳይ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የሚችለው ቅሬታ የቀረበበት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተገኘበት እንደሆነ ብቻ መሆኑን አዋጅ ቁጥር 25/88 ዓንቀፅ 22/1/ ይደነግጋል፡፡ ፍርድ እንዲታይ ትእዛዝ የሚሰጠውም ተከራካሪ ወገኖች በክርክር ባሉበት ጊዜ ነገሩ እስከሚሰማ ድረስ መሆኑን በወንጀልና በፍትሐብሔር ስነ ሰርዓት ህጎች ተደንግጓል፡፡

በዚህ መሠረት የቀረበውን የእግድ ጥያቄና የሰበር አቤቱታው መነሻ በማድረግ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል የተባሉትን ውሳኔዎች አግባብ ካለው ሕግ ጋር ማገናዘብ መርምረናል፡፡ አመልካችንም አነጋግረን ተከታዩን ትዕዛዝ ሰጥተናል፡፡

ት እ ዛ ዝ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔዎች መሰረታዊ የህግ ስህተት ተሰርቷል ለማለት ባለመቻሉ የቀረበውን ዕግድ ጥያቄ አልተቀበልነውም፡፡ ጉዳዩም ለሰበር ችሎት አያስቀርብም ብለናል፡፡ ይግፍ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰበር መ/ቁ/211987

ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ ሐጂ ይማም መሀመድ

ተጠሪ፡ አቶ በላቸው /አብዱልሰመድ/ አደም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ የደቡብ ብ/ብ/ህ/ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በዚህ ችሎት እንዲታረም በሚል ነዉ፡፡

ጉዳዩ የዋስትና ዉል የሚመለከት ነዉ፡፡የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ክርክሩ የተጀመረው በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ በቤንች ሸኮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሳሽ በመሆን በአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ተጠሪ ዋስ ጠርቶኝ ብር 278,000 እቁብ ገንዘብ ወስዶ ብር 153,000 ሳይከፍል በማቋረጡ በገባሁት የዋስትና ግዴታ መሰረት ተጠሪ ያልከፈለውን ገንዘብ የከፈልኩኝ ስለሆነ ተጠሪ ዋናውን ገንዘብ ብር 153,000 ፣የ6ዓመት ከ7 ወር ህጋዊ ወለድ ብር 92,259 እና ኪሳራ ብር 164,583 በድምሩ ብር 409,842 እንዲከፈለኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ተጠሪ በበኩሉ በሰጠው መልስ አመልካች ዋስ ሆኖልኝ በደረሰብኝ ችግር ያቋረጥኩት የእቁብ ገንዘብ ብር 153,000 መክፈሉ እውነት ነው፣ይህንን ገንዘብ ለመተካት

ፍቃደኛ ነኝ፤ ነገር ግን ወለድ እና ወጪና ኪሳራ ሊከፍለው አይገባም፣በዕቁብ ገንዘብ የገዛሁት መኪና ተገልብጦ ኪሳራ ውስጥ ገብቼ የሚሰራውን ስራ አጥቼ በጋምቤላ ክልል በደመወዝ ተቀጥሬ መስራቴን አመልካች ያውቃል፡፡አመልካች ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ ባልሰጠበት ሁኔታ ወጪና ኪሳራ መጠየቁ ህጋዊ መሰረት የለውም፤ከሁለት ዓመት በፊት ዋና ገንዘቡን ለመክፈል በሀገር ሽማግሌዎች ፊት ብለምን እኔ የተጠሪ ቤት ስለያዝኩኝ ገንዘቡን አልቀበልም በማለት ወዲያውኑ ገንዘቡን መቀበል ወይም ክስ መክፈት ሲገባቸው ከ6 ዓመት ከ7 ወር በኋላ በተጠሪ ላይ ጫና ለመፍጠር ያቀረቡት ወጪና ኪሳራ ውድቅ እንዲሆንልኝ በማለት መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ጉዳዩን በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን በዊክልና የተመለከተዉ የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን መርምሮ አመልካች የተጠሪን ዕቁብ ክፍሎ ያጠናቀቀው በቀን 10/09/2006 ዓ.ም መሆኑ የዕቁቡ ማህበር መግለጹን፤አመልካች እዳውን አጠቃሎ ከከፈለበት ከቀን 10/09/2006 ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪን አልጠየቀም ወይም ማስጠንቀቂያ አልሰጠም ወይም የዕቁቡ ማህበር ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ ስለመስጠቱ ያቀረበው ሰነድ ማስረጃ ባለመኖሩ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1940(3) ላይ ዋሱ የቀረበበትን ክስ ለዋናው ባለዕዳ ካስታወቀበት ጊዜ ጀምሮ ባለው ኪሳራ ብቻ ካልሆነ በቀን በሌላ ወጪ በባለዕዳው ላይ አቤቱታ ለማቅረብ አይችልም፡፡ስለዚህ አመልካች ለተጠሪ ባላሳወቁበት የ6 ዓመት ከ7 ወር ወለድ ወጪና ኪሳራ ይከፈለኝ ሲል ያቀረበው ጥያቄ ተገቢነት የለውም በማለት የወለድ እና ወጪና ኪሳራ ውድቅ በማድረግ ዋናውን ገንዘብ ብር 153,000 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙን ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ጉዳዩ አያስቀርብም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካች ይህ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞታል እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ሲታይ፡- በፍ/ብ/ህ/ቁ 1940 እና ተከታዎች እዳን የከፈለ ዋስ በዋናው ባለዕዳ ላይ ዋና ገንዘብ፣ ወለዱንና ወጪና ኪሳራ ጨምሮ መጠየቅ እንደሚችል እና እዳው በባለዕዳ ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ከሆነ ከባለእዳ ላይ ኪሳራ መጠየቅ እንደሚቻል ደንግጓል፡፡በዚሁ መሰረት ዋና ገንዘብ ብር 153,000፣ ወለድ ብር 92,259 እና ኪሳራ ብር 164,583 እንዲከፈለኝ ጠይቄአለሁ፡፡ወጪ ግን አልጠየኩም፡፡ወለድ እና ኪሳራ ለመጠየቅ የማሳወቅ ግዴታ ወይም ቅድመ ሁኔታ የለም፡፡የማሳወቅ ግዴታ ተፈፃሚ የሚሆነው በእዳው ምክንያት ያወጣውን ወጪ ለመጠየቅ በፈለገ ጊዜ ነው፡፡ዋስ ለባለዕዳው የማሳወቅ ግዴታ

ያለበት ወጪ እንዲተካለት ለባለዕዳው ስለመከሰሱ ካስታወቀበት በኋላ ያወጣውን ወጪ እንጂ ካሳወቀበት በፊት ያወጣውን ወጪ አይደለም፡፡የስር ፍ/ቤት ወለድ እና ኪሳራ ጥያቄ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ህ/ቁ 1940(3) በመጥቀስ ወለድና ኪሳራ ጥያቄዬን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡አመልካች ያለብኝ ግዴታ ለተጠሪ የማሳወቅ ሳይሆን እዳው በተጠሪ ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ምክንያት የተከፈለ መሆኑን ብቻ ሲሆን በስር ፍ/ቤት ተጠሪ እቁቡን ወስዶ መኪና ገዝቶበት ሲሰራ ቆይቶ መኪናው ሲወድቅ መኪናውን ሸጦ ከቦታው ተሰውሮ የቆየ መሆኑን እና ይህ ደግሞ በተጠሪ ቸልተኝነት መሆኑ የሚያስረዱ የምስክሮች ዝርዝር አቅርቤ ተከራክረአለሁ፣ስለዚህ የስር ፍ/ቤት የወለድና ኪሳራ ጥያቄዬን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ ወለድና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ ወይም በማስረጃ ተረጋግጦ ውሳኔ እንዲሰጥ ለስር ፍ/ቤት እንዲመለስ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የአመልካች ወለድ እና ኪሳራ ዳኝነት ጥያቄ ውድቅ የተደረገበት አግባብነት ከፍ/ሕ/ቁ 1940(2) አንፃር ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

የተጠሪ ጠበቃ በቀን 25/04/2014ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የዕቁቡን ገንዘብ መክፈል ያልቻልኩት በእቁቡ ገንዘብ የገዛሁት መኪና ተገልብጦ ከጥቅም ውጪ በመሆኑ ምክንያት መሆኑ አመልካች ያውቅ ነበር፣በክርክርም አልካደም፣ስለዚህ እቁቡን ሳይከፍል የቀረሁት በተጠሪ ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ነው የሚያስብል እውነታ የሌለ መሆኑ በስር ፍ/ቤትም ተረጋግጧል፡፡አመልካች የእቁቡን እንዳ እንዲከፍሉ ከማህበሩ ማስጠንቀቂያ እንደደረሳቸው ለተጠሪ ባላሳወቁበት ሁኔታ ወጪና ኪሳራ መጠየቃቸው በፍ/ህ.ቁ 1940(3) እና 1941 አኳያ አግባብ ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ተጠሪ ዋና ገንዘቡን ለመክፈል በሀገር ሽማግሌዎች ፊት ብጠይቅም አመልካች እኔ የተጠሪ ቤት ስለያዝኩኝ ገንዘቡን አልቀበልም በማለት ወዲያውኑ ገንዘቡን መቀበል ወይም ክስ መክፈት ሲገባቸው ከ6 ዓመት ከ7 ወር በኋላ በተጠሪ ላይ ጫና ለመፍጠር በክፉ ልቦና ያቀረቡት ወጪና ኪሳራ ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ተገቢነት ያለው ውሳኔ ነው፡፡በተጨማሪ አመልካች እቁቡ በመክፈሉ የደረሰበት ኪሳራ ስለመኖሩ በቂና ተጨባጭ መከራከሪያም ሆነ ማስረጃ ባላቀረበበት ሁኔታ ወለድ እና ኪሳራ መጠየቁ ተገቢ አይደለም ተብሎ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበትን ሞጉጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ ለክርክሩ መነሻ ሆነዉ ጉዳይ የዋሰትና ዉል ነዉ፡፡ተጠሪ እቁብ ገንዘብ ሲቀበል አመልካችን ዋስ በማድረግ ስለመሆኑና ተጠሪ ክፍያ ሳያጠናቅቅ ማቋረጡን ተከትሎ አመልካች እና ሌላኛዉ ዋስ ቀሪዉን ገንዘብ ባጠቃላይ ብር 153,000 ስለተጠሪ ሆነዉ እቁብ ገንዘብ መክፈላቸዉ አላከራከረም፡፡ ተጠሪም ይህንኑ ገንዘብ ለአመልካች የመክፈል ግዴታዉ መሆኑን አምኖ ሌሎቹን የዳኝነት ጥያቄዎች በመቃወም መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡ፍርድ ቤቶቹም የግራቀኝ ክርክር መርምረዉ እና አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር አገናዝበዉ ኪሳራ እና ወለድ ጥያቄ ተገቢነት የለዉም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ በመሆኑ በዉሳኔዉ ላይ የተፈጸመ ህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከሰበር ችሎት ስልጣን አንጻር መመርመር አስፈላጊ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ የሰበር ስርዓት የተዘረጋበት ዋና ዓላማ በህግ አተገባበር ወይም አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም ወጥ የህግ አተረጓጎም እና አተገባበር እንዲኖር ማስቻል ነዉ፡፡የሰበር ችሎቱ ስልጣንም የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠባቸዉ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ይህንኑ በማረም ላይ የተገደበ መሆኑን ከሰበር ስርዓት መሰረታዊ ዓላማ የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ ይዘትና መንፈስ ይህንኑ የሚያመለክት ሲሆን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በሰበር ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሚያሰኙት ሁኔታዎች ምንድናቸዉ ለሚለዉ ትርጉም መሰጠቱ (አንቀጽ 2/4/ ይመለከታል) ሰበር ሰሚ ችሎት የተቋቋመበትን ዓላማ ማለትም ወጥ የህግ አተረጓጎም እንዲኖር እና የዉሳኔዎችን ተገማችነት በማረጋገጥ ረገድ አገራዊ ፋይዳ ያላቸዉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት እንዲሰራ የሚያስችል ነዉ፡፡መሰረታዊ ህግ ስህተት ምንድነዉ? ለሚለዉ በአዋጁ አንቀጽ 4 ስር ከሀ-ሸ የተመለከተ ሲሆን በሰበር ችሎቱ ሊታዩ የሚችል የመጨረሻ ዉሳኔ፣ፍርድ፣ብይን ወይም ትእዛዝ ላይ ህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ህግን አለ አግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ሞጉጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ሞጉጥ ተይዞ የተወሰነ፣በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣በፍርድ አፈጻጸም ሂደት ከዋና ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትእዛዝ የተሰጠበት፣ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣የአስተዳደር አካል

ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ዉሳኔ ጉዳይ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ስለዚህም ለሰበር የቀረበዉ ጉዳይ ከእነዚህ ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

አመልካች አሁንም አጥብቆ የሚከራከረዉ ዋሱ ኪሳራም ሆነ ወለድ ለመጠየቅ ለተጠሪ ማስታወቅ የሚገደደዉ ከተከሰሰ በኋላ ያወጣዉን ወጪ ለመጠየቅ እንጂ ከክሱ በፊት ያወጣዉን ወጪ ለመጠየቅ አይደለም በማለት ነዉ፡፡ክርክሩ የዋስ እና የባለእዳዉን ግንኙነት የሚመለከት ነዉ፡፡በመሰረቱ የዋስትና ዉል **(contracts of suretyship)** ለአንድ ግዴታ አፈጻጸም ዋስ የሆነ ሰዉ ባለእዳዉ በዉል የገባዉን ግዴታ ያልፈጸመ እንደሆነ ዋሱ ባለእዳዉን ተክቶ ለባለገንዘቡ ለመፈጸም የሚገደድበት ዉል ነዉ፡፡(የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1920 ይመለከታል)፡፡የዋስትና ዉል ከሌሎች ዉሎች የሚለይበት አንዱ ባይርይ ለባለገንዘቡ ወይም ለሌላ አንድ ወገን ጥቅም ተብሎ የሚገባ የችሮታ ዉል መሆኑ ነዉ፡፡ይህም ማለት በዋናነት ዋሱ ከዉለ የተለየ ጥቅም የሚያገኝበት አለመሆኑን የሚያሣይ ነዉ፡፡ይሁን እንጂ ዋስትና ግዴታ ያስከተለበትን ሃላፊነት ከባለእዳዉ የመጠየቅ መብት **(indemnity claim)** እንዳለዉ በህጉ ተመልክቷል፡፡የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1940(1/2) ላይ እንደተመለከተዉ ዋሱ ባለእዳዉን ተክቶ ለባለገንዘቡ ግዴታዉን ከፈጸመ ባለእዳዉ ዋናዉን ገንዘብ፣ወለዱንና ወጪ ኞምር እንዲከፍለዉ መጠየቅ ይችላል፡፡ይህ የሚሆነዉ ከባለገንዘቡ ጋር ክርክር ተደርጎ ዋሱ ከዋና ገንዘብ በተጨማሪ ወለድ እና ወጪ ጨምሮ ለባለገንዘቡ መክፈሉ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡በሌላ በኩል ዋሱ እዳዉን ለባለገንዘቡ የከፈለዉ በባለእዳዉ ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ከሆነ ከባለእዳዉ ላይ ኪሳራ መጠየቅ እንደሚችል እና የኪሳራዉ ልክ የሚወሰነዉ ስለኪሳራ አወሳሰን በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1790-1805 የተደነገጉትን ተመርኩዞ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1941 ደንግጓል፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ ዋሱ ከዋና ገንዘብ በተጨማሪ ወለድና ወጪዎቹን መጠየቅ መብት የሚኖረዉ ይህንኑ ለባለገንዘቡ የከፈለ ሲሆን በሌላ በኩል ኪሳራ ጥያቄ ሊያቀርብ የሚችለዉ ግን በባለእዳዉ በኩል የተፈጸመ ጥፋት ወይም ቸልተኝነት መኖሩን ኞምር በማስረዳት ነዉ፡፡ስለሆነም አንቀጽ 1940(1/2)፣ 1940(3) እና 1941 ጣምራ ንባብ መገንዘብ የሚቻለዉ ወጪ **(cost incurred)** የሚለዉ ቃል ዋሱ ከባለገንዘቡ ጋር ባደረገዉ ክርክር ያወጣዉን ወጪ የሚመለከት ሲሆን ኪሳራ **(Damage)** ግን ባለእዳዉ ግዴታዉን እንዲወጣ ዋሱ ካስታወቀዉ በኋላ ባለእዳዉ ግዴታዉን ባለመፈጸሙ ዋሱ ላይ ያስከተለዉን ኪሳራ የሚመለከት መሆኑን ነዉ፡፡በሌላ አገላለጽ ባለገንዘቡ ባለእዳዉን ኪሳራ ለመጠየቅ የሚችለዉ ባለእደዉ ግዴታዉን እንዲወጣ ያስታወቀ እንደሆነና በባለእዳዉ ጥፋት

ወይም ቸልተኝነት ሳይፈጸም የቀረ ሲሆን ነዉ፡፡የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1771 እና 1795 ድንጌ ይዘትም ይህንኑ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡

በተያዘዉም ጉዳይ አመልካች ከዋና ገንዘብ በተጨማሪ ያቀረበዉን የኪሳራ ጥያቄ የስር ፍርድ ቤት ዉድቅ ያደረገዉ ተጠሪ ግዴታዉን እንዲወጣ አመልካች ባለማስታወቁ ከመሆኑም በተጨማሪ በተጠሪ በኩል የተፈጸመ ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ስለመኖሩ አመልካች ባለማስረዳቱ ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ተችሏል፡፡ወለድን በሚመለከት አመልካች የጠየቀዉ ገንዘቡን ከከፈለበት አንስቶ ክስ እስካቀረበበት ድረስ ያለዉ የ6ዓመት ከ7 ወር አስቦ ሲሆን አመልካች በበኩሉ በዚህ ረገድ ማስጠንቀቂያ ያልደረሰዉ ከመሆኑም ባሻገር አመልካች ዋናዉን ገንዘብ እንዲቀበል በሽማግሌ ጭምር አስለምኖ በአመልካች እምቢተኝነት ሳይከፈል የቆየ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ገንዘብ የመክፈል ግዴታ ያለበት ባለእዳ ወለድ እንዲከፍል የሚገደደዉ ገንዘቡን እንዲከፍል ማስታወቂያ ደርሶት ግዴታዉን አለመፈጸሙ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1803 እና 1772 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡በዚህም ጉዳይ ተጠሪ ያለበትን እዳ እንዲከፍል ማስታወቂያ ስለመስጠቱ አመልካች አለማስረዳቱን የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ጉዳይ ነዉ፡፡ስለሆነም አመልካች እንደክርክሩ አቀራረብ የማስረዳት ግዴታዉን ባልተወጣበት ሁኔታ ተጠሪ ኪሳራ እና ወለድ እንዲከፍል የሚገደድበት ምክንያት ባለመኖሩ በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤቶች ጥያቄዉን ዉድቅ ማድረጋቸዉ የምነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ ከዋና ገንዘብ በተጨማሪ ወለድ እና ኪሳራ እንዲከፍል በማለት እቁቡ ተከፍሎ ካለቀበት ግንቦት ወር 2006ዓ.ም ጀምሮ ክስ እስካቀረበበት ጊዜ ያለዉን በማስላት አመልካች ያቀረበዉን ዳኝነት ጥያቄ የስር ፍርድ ቤቶች መርምረዉ የሰጡት ዉሳኔ የክርክሩን ይዘት እና አግባብነት ያለዉን ህግ ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር በአዋጅ ቁጥር1234/2013 አንቀጽ 2/4/ እና 10(1/ሠ) ድንጋጌዎች መሰረት ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን አንጻር ሲታይ በዉሳኔዉ ላይ ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1ኛ/በዚህ ጉዳይ የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቤንች ሸኮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት በመ/ቁ/09480 ላይ በቀን 30/11/2013ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡ይጻፍ

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

አ/መ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

የሰ.መ.ቁ 212309

ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. አቶ ጎሳ ፍቃዴ

2. አቶ ጉተማ ድሬሳ

3. አቶ አንዱአለም ታዬ ቤተሰብ የሆኑ ሻሚል ከማል ቀረቡ

4. ምርትነሽ አለሙ

5. ገነት ኤልያስ

6. እየሩስ ጅብሪል

ተጠሪ፡- በጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዓቃቤሕግ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ ከባድ የሰው ግድያ ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካቾች ነሐሴ 03 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የቀረበው በጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ክልላዊ መንግስት የጋምቤላ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 20704 ጥር 03 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 02849/2013 ጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 00971/13 ሐምሌ 9 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጋምቤላ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካቾች ላይ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካቾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1(ሀ)፤ 37 እና 539/1(ሀ) ድንጋጌን በመተላለፍ በጋምቤላ ከተማ 05 ቀበሌ ውስጥ ባሮ ማዶ ተብሎ በሚጠራበት አካባቢ በቀን 03/12/2012 ዓ.ም ከቀኑ 5፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 10፡00 ሰዓት ድረስ 2ኛ አመልካች፣ የስር 3ኛ ተከሳሽ፣ 3ኛ አመልካች፣ የሥር 5ኛ ተከሳሽ እና 5ኛ አመልካች በግንት ኤልያሥ ግሮሰሪ ከግል ተበዳይ ጋር አብረው መጠጥ ሲጠጡ የነበሩ መሆኑን፣ 1ኛ አመልካች ንብረትነቱ የፍቅር ፔንሲዮን የሆነውን ድርጅት ኃላፊ እና የጥበቃ ተቆጣጣሪ መሆኑን፣ 4ኛ እና 6ኛ አመልካቾች ደግሞ የፍቅር ፔንሲዮን ሰራተኞች ሆነው በክሱ በተገለፀው ቦታ፣ ሰዓትና ቀን 2ኛ አመልካች፣ የስር 3ኛ ተከሳሽ፣ 3ኛ አመልካች እና የስር 5ኛ ተከሰሽ ሆነው በ3ኛ አመልካች ስልክ ወደ ግል ተበዳይ ስልክ ቁጥር በመደወል ወደ ፍቅር ፔንሲዮን ቤርጎ ቁጥር 2 በማስገባት ደብድበው በማነቅ እና በማፈን ከአልጋ ክፍል አውጥተው ወደ ጓሮ ወስደው የደበደቧት መሆኑንና የግል ተበዳይ የድረሱልኝ ጥሪ ስታሰማ የነበር መሆኑንና የግል ተበዳይን ልብስ አውልቀው ታርጋ ቁጥር በሌለው ባጃጅ አስከሬኑን ጭነው ወደ አፔኖ ቴክኒክና ሙያ አካባቢ ወስደው የጣሏት መሆኑን፣ ቤርጎ ቁጥር 2 ውስጥ የግል ተበዳይ የአንገት ጨሌ የተገኘ መሆኑን በመግለጽ 1ኛ፣ 4ኛ እና 6ኛ አመልካቾች የፍቅር ፔንሲዮን ሰራተኞች ሲሆኑ የግል ተበዳይ የድረሱልኝ ጥሪ ስታሰማ እየሰሙ ዝም በማለታቸው የዚህ ወንጀል ድርጊት አባሪ ተባባሪ መሆናቸውን፣ ሌሎች አመልካቾች ደግሞ በዋና ወንጅል አድራጊነት በፈጸሙት ጨለማን ተገን በማድረግ የከባድ ግፍ ግድያ ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡

አመልካቾች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ መቃወሚያ የሌላቸው መሆኑን ገልጸው የእምነት ክሕደት ቃላቸውን ሲጠየቁ ድርጊቱን አልፈጸምንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ፍርድ ቤቱ የዓቃቤሕግን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካቾችም መከላከያ ምስክሮቻቸውን አስቀርበው አሰምተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ በስር 3ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች የመከላከያ ምስክሮቻቸው የቀረበባቸውን ክስ አስተባብለውላቸዋል በማለት በነፃ የለቀቋቸው ሲሆን አመልካቾችን በሚመለከት ግን የግል ተበዳይ መሞታቸው በፎቶ ግራፍ ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን፣ ሟች የግል ተበዳይ ፍቅር ፔንሲዮን ውስጥ ስለመገደላቸው የዓ/ህግ ማስረጃ የሚያረጋግጥ መሆኑን፣ 1ኛ

አመልካች የድርጅቱ ጥበቃ ሆነው እየሰሩ በመሆኑ የሰዎችን ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነት እያለባቸው ዝም በማለት ከገዳዮች ጋር አብረው ስለመሆናቸው የሚያስረዳ መሆኑን፣ 4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾች ደግሞ በድርጅቱ ውስጥ ወንጀል ተሰርቶ እያለ ለሚመለከተው አካል አለማሳወቀቸው የወንጀሉ ድርጊት ተባባሪ መሆናቸውን የሚያሳይ መሆኑን በመግለጽ ከ1-3 ድረስ የተዘረዘሩት አመልካቾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ከ4-6 ያሉትን አመልካቾች ደግሞ በአባሪ ተባባሪነት ጥፋተኛ በማለት ከ1-3 የተጠቀሱትን አመልካቾች በ 25 ዓመት ጽኑ እስራት፣ ከ4-6 ያሉትን አመልካቾች ደግሞ በ18 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል። ይህ ውሳኔ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚና በክልሉ ሰበር ችሎት ፀንቷል።

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው። አመልካቾች ነሐሴ 03/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የሕግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል። ፍሬ ቃሉም የተከሰሱበት የሕግ ድንጋጌና የተከሰሱበት የወንጀል ፍሬ ነገር የማይገናኝ መሆኑን፣ ሟችን የገደሉበት መሳሪያ ሳይገለጽ፣ ሟችን ለመግደል አመልካቾች ምንም ዓይነት ሀሳብ እንዳላቸው ሳይረጋገጥ በደፈናው የተጠሪ ማስረጃዎች በበቂ ሁኔታ ሳያስረዱ የስር ፍ/ቤት ጥፋተኛ በማለት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን፣ 2ኛ አመልካች ለሟች ስልክ ድውሏል በሚል ብቻ ዋና ወንጀል አድራጊ ተብለው የተቀጡ መሆኑንና ከኢትዮ ቴሌኮም የቀረበ ማስረጃ የሌለ መሆኑን፣ የመ/ምስክሮች በደንብ ያልታዩላቸው መሆኑን፣ አመልካቾች ከሟች ጋር አብረው ያልነበሩና ሟች ሌላ ሰው ጋር የነበሩ መሆኑን፣ የዓ/ህግ ምስክር ጨለማ በመሆኑ ገዳዮችን ያለዩዋቸው መሆኑን፣ ቅጣቱም የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን ያልተከተለ መሆኑን ጠቅሰው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ የተሰጠውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ አግባብነትን ለማጣራት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል።

ተጠሪ በቀን ጥቅምት 19/2014 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት መልስ በስር ፍ/ቤት በዓ/ህግ የቀረበው የወንጀል ክስ በሰውና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጦ ከጥርጣሬ በላይ የተመሰከረባቸው ስለሆነ በተጠቀሰው የወንጀል ህግ ውሳኔ መሰጠቱ ትክክል መሆኑን፣ የዓ/ህግ የወንጀል ማመልከቻ በወንጀል ህግ ቁጥር 23 መሰረት የተሟላ መሆኑን፣ የዓ/ህግም ሆነ የአመልካቾች ምስክሮች በሚገባ የተሰሙ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማት ተከራክሯል።

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣

ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ በወንጀል ጉዳይ የሚሰጥ ውሳኔ በተከሳሽ ነጻነት ወይም ሕይወት ላይ የሚሰጥ ውሳኔ በመሆኑ በተከሳሽ ላይ የሚቀርበው ክስ ተከሳሽ የወንጀሉን ድርጊት ስለመፈፀሙ ብቻ ሣይሆን ወንጀሉ የተፈፀመበትን ጊዜ፣ወንጀሉ እንዴት እንደተፈፀመና ወንጀሉ በማን እንደተፈፀመ በዝርዝር መግለጽ ያለበት ስለመሆኑ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግም በሚያቀርበው ማሥረጃ በክስ አቤቱታው ላይ የተገለፀው የወንጀል ድርጊት የተፈጸመ ስለመሆኑ እና የወንጀል ድርጊቱን ፈጻሚ ማንነት በትክክል ለይቶ ማሳየት እና በቂ እና አሳማኝ ሊባል በሚችል ሁኔታ የማስረዳት ሸክም (Burden of proof) እንዳለበት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 111፣ 141 እና 149 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ዓቃቤሕግ ክሱን የማስረዳት ሸክሙን ተወጥቷል የሚባለውም ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ይዘት እርስ በእርሳቸው የሚፋለሱ ፍሬጉዳዮችን ያልያዙ፣ወጥነት ያላቸው ተደጋጋፊ እና ተመሣሣይ ጉዳይ ማሥረዳት የሚችሉ እና ተዓማኒነት ያላቸው ሆነው ሲገኙ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ተከሳሽ እንዲከላከል ብይን ሊሰጥ የሚችለውም ዓቃቤሕግ ባቀረባቸው ማሥረጃዎች ተከሳሽ ወንጀል መፈፀሙን እና ተፈፀመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በተከሳሽ መፈፀሙ በበቂና በአሳማኝ ሁኔታ ያስረዳ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 (2)እና(4)፣57፣58(1) እና ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 እና 142 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ዓቃቤሕግ ባቀረበው ክስ አመልካች ሚችን ለመግደል ያነሳሳውን ምክንያት ያልጠቀሰ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ዓቃቤሕግ ክሱን ለማስረዳት በፍርድ ቤቱ ቀርበው ከተሰሙት ምስክሮች ውስጥ 1ኛ ምስክር በእለቱ ከ2ኛ አመልካች እና ፍሬው ከተባለ ሰው ጋር ሲጠጡ እንደነበር ምስክሩ ትቶአቸው ቀድሞ እንደሄደ፣ በማግስቱ 2ኛ አመልካች ደውሎ ከእኛ ጋር የነበረችው ሴት ሰው ገድሎታል ፖሊሶች ከያዙህ አትንዘባዘብ እንዳለው በመቀጠልም ወደ አዲስአበባ እንሂድ ስለእኔ ከተናገርክ እገድልሃለሁ እንዳለው የመሰከረ ነው፣ 2ኛ ምስክር ጨምሮት ሰምቼ ስወጣ ድምጽ አለ ከፍ ተደርጎ የተከፈተ የሚዘፍን ሞባይልም አለ ሚች የተገደለችበት ቦታ መብራት ነበር ደብዳቢዎቹን ግን ከሩቅ ቦታ ስለነበር አላየኋቸውም በማለት የመሰከረች ነች፣ 3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ምስክሮች ደግሞ ጨሌ በቤርጎ ቁጥር 2 ተንጠልጥሎ ያገኙ እና ጨሌውም የሚች መሆኑን በመግለጽ ከመመስከራቸው በቀር በእርግጥም በክሱ በተገለጸው ሁኔታ አመልካቾች የግድያ ወንጀሉን ሲፈጽሙ አይተናል በማለት የተሰጠ የምስክርነት ቃል የለም፡፡ ይህም ከመነሻውም ቢሆን ዓቃቤሕግ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸሙ በቂ እና አሳማኝ ሊባል በሚችል ማስረጃ ያላስረዳ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል ጉዳዩ ወንጀል ከመሆኑ እና ተከሳሽ የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸሙ በቂ እና አሳማኝ ሊባል በሚችል ማስረጃ ሊረጋገጥ የሚገባው ከመሆኑ አኳያ በፍቅር ፔንሲዮን ቤርጎ ቁጥር 2 የአንገት ጨሌ የተገኘ መሆኑን፣ 4ኛ አመልካች ለሚች ስልክ ደውሎ የነበረ መሆኑ እና 2ኛ አመልካች ለ1ኛው

የዓቃቤሕግ ምስክር ደውሎ ከእኛ ጋር የነበረችው ሴት ሰው ገድሎአታል ፖሊሶች ከያዙሁ አትንዘባዘብ ወደ አዲስአበባ እንሂድ ስለእኔ ከተናገርክ እገድልሃለሁ ማለቱ ብቻውን አመልካቾች በእርግጥም ወንጀሉን ፈጽመዋል ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ከመነሻውም ቢሆን አመልካቾች ክሱን እንዲከላከሉ ብይን መሥጠቱ አግባብ አልነበረም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ይህንኑ መሠረት በማድረግ አመልካቾችን ክሱን መከላከል ሳይስፈልጋቸው ከተከሰሱበት ክስ በነጻ ማሰናበት ሲገባቸው በአመልካቾች ላይ ያስተላለፉት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. በጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጋምቤላ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 20704 ጥር 03 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝን እና የቅጣት ውሳኔ፣ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 02849 ጥር 13 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 00971/13 ሐምሌ 09 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡

2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካቾች ከተከሰሱበት ክስ በነጻ ሊሰናበቱ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

ትዕዛዝ

- የሚመለከተው ማረሚያ ቤት በስር ፍርድ ቤቶች በአመልካቾች ላይ የተላለፈው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተሽሮ አመልካቾች ከተከሰሰበት ክስ በነጻ የተሰናበቱ መሆኑን አውቆ አመልካቾችን በዛሬው ዕለት ከእሥር እንዲለቅ ታዟል፡፡ በትዕዛዙ መሠረት ማስፈጸም ይቻለው ዘንድም የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ይድረሰው፡፡

- በየደረጃው ያሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በዚህ ችሎት የተሻረ መሆኑን እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡- 212313

ቀን፡-30/03/2014ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ሁሴን ሙክታር

ተጠሪዎች፡-1. ወ/ሮ ብዙነሽ ፋፋ

2.ወ/ሪት ውብዓለም ታረቀኝ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁ.275565 በቀን 28/11/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች በምዕራብ በኩል 1 ሜትር ወደ ተጠሪዎች ይዞታ በመግባት በመያዝ የፈጠረው ሁከት ሊወገድ ይገባል በማለት የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት ብይን መስጠቱ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይኸው ስህተት እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ መነሻ በማድረግ ሲሆን አመልካች በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት 2ኛ ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን ተጠሪዎች ከሳሾች ነበሩ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት በአመልካች እና በስር 1ኛ ተከሳሽ ላይ ባቀረቡት ክስም በን/ስ/ላ/ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 የቤት ቁጥር ኮድ 44 የሆነ በ180 ካሜ ላይ ያረፈ የመኖሪያ ቤት ከሚች ባለቤቱ አቶ ታረቀኝ አላምረው ጋር በመሆን ነሀሴ 04 ቀን 1991 ዓም በተደረገ የሽያጭ ውል ከአቶ አረብሳ ማሞ እና ወ/ሮ መስታወት ሀይሌ በመግዛት ተረክበን ስንኖር አመልካች በስተምዕራብ በኩል ወደ ይዞታችን ጥሶ በመግባት ህገወጥ ግንባታ የፈፀመ እና በጥር ወር 2011 ዓም አጥር በማፍረስ ሁከት የፈጠረብን በመሆኑ ይዞታችንን ለቅቆ እንዲያረክበን ይወሰንልን በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካች በሰጡት መልስም ተጠሪዎች ይዞታውን ስለመግዛታቸው እና ስለመረከባቸው የሚያስረዳ ማስረጃም ሆነ በይዞታው ላይ ስለመገበራቸው ያቀረቡት ማስረጃ ስለሌለ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤አመልካች ከተጠሪዎች 10 አመት አስቀድሜ ክርክር የተነሳበትን ይዞታ በእጄ አድርጌ ቤቶች ሰርቼ እየኖርኩ እያለ 1ኛ ተጠሪ የዛሬ 17 ዓመት ወደ ይዞታው የመጣችና በድንበሯ ላይ ጨርሳ ቤት ሰርታ የሰራችና ፍሳሽ ወደ አመልካች በማድረጓ በሽምግልና ታይቶ ፍሳሹን ወደምትኖርበት ይዞታ እንድታደርግ ጉዳዩ ሲታይ የነበረ በመሆኑና አመልካች ወደ ተጠሪዎች ይዞታ ያልገባሁ በመሆኑና ምን ያህል ካሜ እንኳ እንደያዝኩ ክሱ ተብራርቶ ያልቀረበ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው የሚለውን ማጣራት አድርጎ የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቶ በሰጠው ውሳኔም የክፍለ ከተማውና የከተማው የይዞታ አስተዳደር ፅ/ቤቶች በተለያየ ጊዜ አጣርተው በሰጡት ምላሾች ትክክለኛውን የተጠሪዎችን ይዞታ ስፋት ማወቅ ያልተቻለ መሆኑን ነገር ግን የተጠሪዎች ይዞታ በግራም በቀኝም በኩል እየጠበበ መምጣቱን በእስኬች አስደግፎ መግለፁን፤የተጠሪዎች ምስክሮች በምዕራብ በኩል 1 ሜትር የሚያክል ይዞታ አመልካች መያዛቸውን ሲያስረዱ የአመልካች ምስክሮች የአመልካች ይዞታ ምን ያህል እንደሆነ እንደማያውቁ ወደ ተጠሪዎች ይዞታ ስለማለፋቸው የማያውቁ መሆኑን ማስረዳታቸውን በመጥቀስ አመልካች በምዕራብ በኩል 1 ሜትር ወደ ተጠሪዎች ይዞታ በመግባት በመያዝ የፈጠሩት ሁከት ሊወገድ ይገባል ፤አመልካች ወደ ተጠሪዎች ይዞታ 1 ሜትር በመግባት ያከናወኑትን ግንባታ በማፍረስ ለተጠሪዎች ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ በተደረገው ማጣራት 3 ምላሾች የቀረቡ ሆኖ ባለሙያውም በችሎቱ ቀርቦ ማብራሪያ እንዲሰጥ ተደርጎ በቀረበው አጠቃላይ ውጤት በ1997 ዓም ሆነ በ2003 ዓም በተነሳው የአየር ካርታ የግራ ቀኙችን ይዞታ በአንድ ጊቢ ውስጥ የሚታይና ስንት ካሬ ሜትር እንደሆነ ለማወቅ የማይቻል መሆኑን፤ተጠሪዎች በአመልካች ይዞታ ውስጥ ይዞታ አለኝ ቢሉም በእጃቸው ያልያዙት መሆኑን ፤በግራ ቀኙችን መሃል የድንበር መገፋፋት አለ ለማለት የሚያስችል ማስረጃ እንደሌለ የሚገልፅ ሆኖ እያለ፤የስር ፍርድ ቤት ይህንን

መግለጫ ወደ ጎን በመተው የሰጠው ውሳኔ በሰበር መዝገብ ቁጥሮች 97132፣48608 የተሰጡትን አስገዳጅ የህግ ትርጉሞች መሰረት ያላደረገ የባለሙያን ማብራሪያ ባለመቀበል የሰው ምስክርን ቃል በመቀበል የተሰጠ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊሻር ይገባል በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካች የተጠሪዎችን ይዞታ ገፍተው አለመያዛቸው በክፍለ ከተማው የይዞታ አስተዳደር በተገለፀበት ባለሙያ ያልሆኑ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል መሰረት በማድረግ አመልካች 1ሜትር ላይ የገነቡትን ግንባታ አፍርሰው ለተጠሪዎች እንዲለቁ የተወሰነበትን አግባብ ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት መልስም መልሳችንን ስናቀርብ ከሰው ምስክሮች በተጨማሪ ከ1988 ዓም ጀምሮ የግብር ማህደር ያለን ለመሆኑ፣በ1993 ዓም ካዳስተር ቢል ላይ የተጠሪዎች ይዞታ የቦታ ስፋት 155 ካሜ የነበረ ስለመሆኑና በ2009 ዓም የቦታው ስፋት 83 ካሜ ብቻ እንደቀረ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 09 ያረጋገጠበትን የሰነድ ማስረጃ ያቀረብን ስሆን የክፍለ ከተማው ይዞታ አስተዳደር ለፍርድ ቤቱ በሰጠው ምላሽም የ1988፣1997 እና 2003 ዓም የአየር ላይ ካርታ ምልከታ ስኬች በመላክ በሶስቱም የአየር ካርታ ላይ የተጠሪዎች ይዞታ ከጊዜ ወደ ጊዜ ያሳየውን ልዩነት ያሳየ በመሆኑ አመልካች የተጠሪዎችን ይዞታ ጥሶ በመግባት ይዞታችንን በሀይል እና በህገወጥ መንገድ ስለመያዙ የሰነድ የባለሙያ እና የሰው ማስረጃዎችን ያቀረብን በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡በመሰረቱ አንድ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አወሳሰን የጠራ ፍሬ ነገር የሌለ መሆኑን ከተገነዘበ ይኸው ፍሬ ነገር እንዲጣራ ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት ሁሉ ማድረግ እንደሚችል ከፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.136፣137፣272 እና 345 ድንጋጌዎች ለመረዳት የሚቻል ሲሆን ለጉዳዩ አወሳሰን መሰረት የሚሆንን ፍሬ ነገር በማስረጃ ሳያጣሩ መወሰን አግባብ ባለመሆኑ በክርክሩ የቀረቡት ማስረጃዎች በቂ ባልሆኑበት ጊዜ እና እነዚህን ማስረጃዎች ብቻ መሰረት አድርጎ መወሰን ፍትህን የሚያዛባ ከሆነ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት ተጨማሪ ማስረጃ ወይም ምስክር እንዲቀርብ መታዘዝ ያለበት ስለመሆኑ በሰበር መዝገብ ቁጥሮች 72980፣22603 እና በሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎች በአመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት ክሳቸውን ያቀረቡት ከይዞታቸው በስተምዕራብ በኩል ጥሰው በመግባት ግንባታ የፈፀሙ መሆኑንና በጥር ወር 2011 ዓም አጥር በማፍረስ ሁከት የፈጠሩ መሆኑን በመጥቀስ ሲሆን አመልካች ወደ ተጠሪዎች ይዞታ በመግባት የፈጠሩት ሁከት የሌለ መሆኑን በመጥቀስ መከራከራቸውን የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክር ያሳያል፡፡በመሰረቱ የግራ ቀኙ ይዞታ

ሰነድ አልባ መሆኑ ግራ ቀኙ የተማመኑበት ነጥብ ሲሆን የአስተዳደር አካላቱ ምላሽም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡የአስተዳደር አካላቱ ይህንን መነሻ በማድረግ በሰጡት ምላሽ የግራ ቀኙን ይዞታ ትክክለኛ ስፋት ማወቅ እንዳልቻሉ የገለፁ ሲሆን ከዚህ ምላሽ ጋር አያይዘው በሰጡት መግለጫ የተጠሪዎቸ ይዞታ በግራ እና በቀኝ በኩል እየጠበበ መሆኑን እንደገለፁ የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ ያመለከተ ሲሆን ይህ ምላሽ በእስኬች የተደገፈ መሆኑን ፍርድ ቤቱ በውሳኔው ላይ ገልጿል፡፡ይህ ምላሽ በግራ ቀኝ በኩል የተጠሪዎች ይዞታ እየጠበበ መምጣቱን ቢያመለክትም መሰረታዊ በሆነ የአቅጣጫ ማመልከቻ ጠበበ ያለውን ይዞታ በማመልከት፣ክስ ከቀረበበት ከተጠሪዎች ይዞታ ምዕራብ አቅጣጫ አንፃር ይህ የይዞታ መጥበብ መኖር አለመኖሩን አያመለክትም፡፡

የግራ ቀኙን ይዞታ ስፋት ልክ ማወቅ ያልቻለ ከሆነ የይዞታውን በሂደት መጥበብ በምን እንደተገነዘበ፣ይህ የይዞታ በየጊዜው መጥበብ ከመቼ ጀምሮ እንደመጣ (አመልካቾች በጊዜ አገኘን ካሉ በኋላ ይሁን በፊት) ፣አመልካች በተጠሪዎች ይዞታ መጥበብ ላይ ድርሻ ያላቸው መሆን አለመሆኑን በማብራራት የሠጠው ምላሽ ስለመኖሩ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡

በተለያዩ ጊዜያት በተነሱት የአየር/መስመር ካርታዎች የተጠሪዎች ወይም ለተጠሪዎች መብቱን ያስተላለፉት አቶ አረብሳ ማሞ እና ወ/ሮ መስታወት ሀይሌ በይዞታው ላይ ያከናወኑት ግንባታ ልክ እና ይህንን መሰረት በማድረግ የሚታወቀው የይዞታ ልክ እና/ወይም በተቃራኒው የአመልካች በይዞታው ላይ ያከናወኑት ግንባታ ልክ እና ይህንን መሰረት በማድረግ የሚታወቀው የይዞታ ልክ ምን ያህል እንደሆነ፣ ከዚህ በማለፍ በተጠሪዎች ይዞታ በምዕራብ በኩል አመልካች የያዙት የተጠሪዎች ይዞታ መኖር አለመኖሩ፣ካለም ምን ያህል እንደሆነ ከተገቢው የአስተዳደር አካል መጣራቱን የስር ፍርድ ቤት አያጣራም፡፡ይህ ባልሆነበት የስር ፍርድ ቤት ለግራ ቀኙ አዋሳኝ የሆኑትን አስቀርቦ ሳይሰማ የተጠሪዎች ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል ብቻ መሰረት በማድረግ የደረሰበት መደምደሚያ እና ይህንን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ሊያርም ሲገባ ማፅናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለው ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.279049 በ06/0122012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና ይህንን ፍርድ በማፅናት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.259509 በ21/07/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት የጉዳዩን መዝገብ በማንቀሳቀስ ከተገቢው የአስተዳደር አካል በተለያዩ ጊዜያት በተነሱት የአየር/መስመር ካርታዎች የተጠሪዎች ወይም ለተጠሪዎች መብቱን ያስተላለፉት አቶ አረብሳ ማሞ እና ወ/ሮ መስታወት ሀይሌ በይዞታው ላይ ያከናወኑት ግንባታ ልክ እና ይህንን መሰረት በማድረግ የሚታወቀው የይዞታ ልክ እና/ወይም በተቃራኒው

የአመልካች በይዞታው ላይ ያከናወኑት ግንባታ ልክ እና ይህንን መሰረት በማድረግ የሚታወቀው የይዞታ ልክ ምን ያህል እንደሆነ፣ ከዚህ በማለፍ በተጠሪዎች ይዞታ በምዕራብ በኩል አመልካች የያዙት የተጠሪዎች ይዞታ መኖር አለመኖሩ፣ካለም ምን ያህል እንደሆነ እና መቼ እንደያዙት በማጣራት እንዲሁም ስለጉዳዩ በጥልቀት ሊያውቁ የሚችሉትን የግራ ቀኙን አዋሳኞች አስቀርቦ በመስማት በዚህ አግባብ የሚቀርበውን ምላሽ ከግራ ቀኙ ምስክሮች ቃል ጋር በመመዘን በህጉ አግባብ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡

3. **በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር** 294015 **በተያዘው አፈፃፀም ላይ ነሀሴ** 05 **ቀን** 2013 **ዓም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡**
4. **ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡**

<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

የሰ/መ/ቁ 212533

ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ወ/ሮ ፅጌ ዋስይሁን፡-ከጠበቃ ኢሳያስ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሚካኤል እምሩ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በቀን 06/12/2013 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 105702 በቀን 24/06/2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 268854 በቀን 08/11/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልን በማለት ስለጠየቁ ነው። ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

ከሳሽ በቀን 26/11/2011 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ ከተከሳሽ ጋር ከጥር 2002 ዓ.ም እስከ መስከረም 2011 ዓ.ም ድረስ እንደ ባልና ሚስት ስንኖር ሁለት ልጆችና የተለያዩ ንብረቶችን በጋራ ያፈራን ሲሆን በመካከላችን በተፈጠረ አለመግባባት በግንኙነቱ መቀጠል ስላልፈለኩ ተከሳሽ በቂ የልጆች

ቀለብ እንዲሰጠኝና በጋራ ያፈራናቸውን ንብረቶች ድርሻዬን እንዲያካፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሽ በሰጡት መልስ ከከሳሽ ጋር እንደ ባልና ሚስት አልኖርንም፤ ንብረትም በጋራ አላፈራንም፤ ከ16/10/2001 ዓ.ም እስከ 03/11/2008 ዓ.ም ድረስ አዲስ አበባ ከተማ በሚገኝ ሚክሊላንድ ኮንዶሚኒየም የቤ.ቁ 27/68 ውስጥ እንዲሁም ከ03/11/2008 ዓ.ም እስከ 09/01/2009 ዓ.ም ድረስ ሰሚት ኮንዶሚኒየም የቤ.ቁ 16 ውስጥ ብቻዬን ስኖር ስለነበረ ከከሳሽ ጋር አልኖርኩም፡፡ ከነሐሴ 2009 ዓ.ም ጀምሮ የንግድ ፈቃድ አውጥቼ በእቃ አስመጭነት ስራ ተሰማርቼ እገኛለሁ፡፡ ከሳሽ ከእኔ ጋር ሳትኖርና ሳትሰራ አብረን ያፈራነው ንብረት ሳይኖር ያቀረበችው ክስ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ብለዋል፡፡ ሁለት ልጆች ማፍራታቸውን ግን በቃል ክርክር ወቅት ግራ ቀኙ ተማምነዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የከሳሽ ምስክሮች ከሳሽና ተከሳሽ እንደባልና ሚስት መኖራቸውን አስረድተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከመቼ ጀምሮ እስከ መቼ እንደኖሩ ተመሳሳይና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ አላስረዱም፡፡ በሌላ በኩል ተከሳሽ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ሂለን ከምትባል ጓደኛው ጋር እንደ ባልና ሚስት መኖራቸውን የተከሳሽ ምስክሮች አስረድተዋል፤ ይህም የሚያሳየው በከሳሽና ተከሳሽ መካከል ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ እንደ ባልና ሚስት ግንኙነት የሌለ መሆኑን ነው፡፡ ትዳር ሳይኖር እንደ ባልና ሚስት የመኖር ግንኙነት በንብረት ላይ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው ከ3 አመት ያላነሰ ግዜ አብረው ሲኖሩና ንብረቱም በግንኙነቱ ጊዜ የተፈራ መሆኑ ሲታወቅ ሲሆን በዚህ ጉዳይ ግን እንደ ባልና ሚስት የመኖር ግንኙነት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በንብረት ላይ የሚያመጣው ውጤት አይኖርም፡፡ በመሆኑም ከሳሽና ተከሳሽ እንደ ባልና ሚስት አልኖሩም፡፡ በሌላ በኩል ከሳሽና ተከሳሽ ሁለት ልጆች ማፍራታቸውና ልጆቹም ከሳሽ ጋር እንዲኖሩ ግራ ቀኙ ተስማምተዋል፤ የልጆች ቀለብን በተመለከተ የግራ ቀኙን ሀሳቦች ከነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ተከሳሽ በየወሩ 6500.00 (ስድስት ሺህ አምስት መቶ) ብር እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ውሳኔው ጸንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው።

አመልካች በቀን 06/12/2013 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ አመልካችና ተጠሪ እንደ ባልና ሚስት ስለመኖራቸው የቤት አከራይ ከሆኑት ግለሰብ በተጨማሪ በበርካታ ምስክሮች ተረጋግጦና በተለያዩ የመንግስትና የህይማኖት ተቋማት ውስጥ ባልና ሚስት ስለመሆናቸው በሰነድ ጭምር ተመልክቶ ይገኛል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ አመልካችና ተጠሪ ሁለት ልጆች በጋራ የወለዱ መሆናቸው በራሱ ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ተዳምሮ ግራ ቀኙ እንደ ባልና ሚስት አብረው የኖሩ መሆናቸውን በበቂ ሁኔታ የሚያስረዳ ነው፡፡ ተጠሪም ልጆች በጋራ መውለዳችንን የሚክደው

አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ይህን ሳይቀበሉና በፍርድ ሀተታቸው ላይ ምንም ሳይሉ ማለፋቸውና እንደ ባልና ሚስት አልኖሩም ሲሉ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የቀለብ መጠንን በተመለከተ ለሁለቱ ህጻናት የተወሰነው በአጠቃላይ በወር ብር 6500.00 (ስድስት ሺህ አምስት መቶ) ሲሆን አመልካች ምንም አይነት ገቢ የሌለኝ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪ ግን በአንድ ግዜ ብቻ እስከ 16,000,000 (አስራ ስድስት ሚሊየን) ብር ድረስ ክፍያ ሊያገኝበት የሚችለው የንግድ ስራ የሚሰራና የተለያዩ መኪኖችና G+3 ህንጻ በአሁን ሰአት በእጁ ይዞ የሚገኝ ሲሆን አመልካች ከቤት የወጣሁት ምንም ንብረት በእጄ ሳልይዝ ነው፡፡ በአጠቃላይ አመልካችና ተጠሪ እንደ ባልና ሚስት ኖረዋል ተብሎ እንዲወሰንና ለሁለት ልጆች ቀለብ የሚሆን በየወሩ ብር 15,000 (አስራ አምስት ሺህ) እንዲወሰንልኝ በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች ጋብቻ ሳይኖር ከተጠሪ ጋር እንደ ባልና ሚስት አብረው ስለመኖራቸው በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል የተወሰነበትን አግባብነት ከቀረቡት የሰውና ሰነድ ማስረጃዎችና ከመሰረታዊ የክርክር አመራር ሥነ ሥርአት እና የማስረጃ ምዘና መርህ አንጻር ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ባቀረቡት መልስ በስር ፍ/ቤት ያቀረብኳቸው ምስክሮች በአግባቡ እና ወጥነት ባለው መልኩ ከአመልካች ጋር እንደ ባልና ሚስት ያልኖርኩኝ መሆኑን፣ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ከሄለን ኃ/ሚካኤል ጋር እየኖርኩኝ መሆኑን መስክረው እያለ አመልካች ከተጠሪ ጋር እንደ ባልና ሚስት ኖረናል በማለት ያቀረቡት ተገቢነት እና የህግ መሰረት የሌለው ክርክር ነው፡፡ የቀለብ መጠን የተወሰነው በስር ፍ/ቤት በተደጋጋሚ ጊዜ በአመልካች የይሻሻልልኝ ጥያቄ ቀርቦ የተወሰነ ስለሆነ እንጂ በተጠሪ በኩል ምንም አይነት ገቢ የሌለኝ፣ ድርጅቱም በኪሳራ ምክንያት የተዘጋ መሆኑን ጠቅሼ ማስረጃ አቅርቤየለሁ፣ በአመልካች የተጠቀሰው ቤትም በግንባታ ላይ የሚገኝ እና ሰው የማይኖርበት በመሆኑና የምኖረው በኪራይ ቤት በመሆኑ በአሁን ሰአት ምንም አይነት ስራ የሌለኝ መሆኑ እየታወቀ ቀለብ በወር 6500.00 (ስድስት ሺህ አምስት መቶ) አነሰ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ክርክራቸውን አጠናክረዉ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የስር ፍርድ ቤቶች በክርክር አመራር ረገድ የፈፀሙት የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀው ጉዳዩ የቤተሰብ ክርክርን የሚመለከት በመሆኑ ክርክሩ ሊመራ የሚገባው አግባብነት ባላቸው የቤተሰብ ህጉን እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ጋብቻ ሳይፈፅሙ እንደባልና ሚስት አብረው ይኖራሉ የሚባለው ምንም እንኳ በህጉ አግባብ የተጋቡ ባይሆኑም የተጋቡ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩ እና ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሰቡ እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው ሲገምቷቸው ስለመሆኑ በቤተሰብ ህጉ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም ግራቀኙ እንደባልና ሚስት አብረው ኖረዋል ወይስ አልኖሩም የሚለውን የፍሬ ነገር ክርክር መወሰን የሚቻለው ማስረጃውን ከዚሁ የቤተሰብ ህጉ አነጋገር ጋር አያይዞ በመመርመርና በመመዘን ነው፡፡

በሌላ በኩል ፍርድ ቤቱ ለክርክሩ አግባብነት የለውም ወይም ከነገሩ ጋር ግንኙነት የለውም የሚለውን ክርክርና ማስረጃ ሁሉ አለመቀበል የሚችል ቢሆንም ይህንን ሲወስን ግን ምክንያቱን በመዝገቡ ላይ በጽሁፍ መግለጽ እንዳለበት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 223፣ 234፣ 136-138 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶች ተከራካሪዎች የሚያቀርቡትን የፍሬ ነገር ክርክርና ክርክራቸውን ለማስረዳት የሚያቀረቧቸው ማስረጃዎች መታየት አለመታየታቸውን፣ እንዲሁም ተቀባይነት የለውም የሚባል የፍሬ ነገር መከራከሪያ እና ማስረጃ ቢኖር እንኳ ምክንያቱን በውሳኔው ሳይገለፅ አልፎ ፍርድ መስጠት ጉዳዩ የሚመራበትን የስነ ስርዓት ህግ የተከተለ ባለመሆኑ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

እነዚህን ከፍሲል የተመለከቱ የህጉን ድንጋጌዎች በተያዘው ጉዳይ ከቀረበው ከክርክር እና በስር ፍርድ ቤቶች ከተሰጠው ውሳኔ አንፃር እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

አመልካች ባቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር ከ2002 ዓ.ም እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ እንደ ባልና ሚስት መኖራቸውና በግንኙነታቸው ሁለት ልጆች እንዲሁም ንብረት ማፍራታቸውን ገልፀው ግንኙነቱ ስለተቋረጠ የልጆች በቂ ቀለብ እንዲቆረጥ እና ንብረት በድርሻቸው እንዲያካፍላቸው እንዲወሰንል ጠይቀዋል፡፡ ክርክራቸውን ለማስረዳት ከተጠሪ ጋር ተከራይተው ይኖሩበት የነበረው ቤት አከራይ የሆኑትን 2ኛ ምስክራቸውን በማቅረብ ግራቀኝ በቤታቸው ለአራት አመት መኖራቸውንና ቤት ገዝተናል ብለው መውጣታቸውን ከማስመስከራቸውም በተጨማሪ ሌሎች ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃ አቅርበዋል ፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ሁለት ልጆች ማፍራታቸውን ሳይክዱ ነግር ግን እንደ ባልና ሚስት አብረው እንዳልኖሩና ንብረትም በጋራ እንዳላፈሩ ተከራክረው እንዲያውም ከ2008 ዓ.ም በኃላ ከሌላ ሰው ጋር እንደሚኖሩ ሁሉ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡

ግራቀኙ በዚህ አግባብ ቢከራከሩም የስር ፍርድ ቤት ባሳለፈው ውሳኔ የአመልካች ማስረጃዎች እንደባልና ሚስት መኖራቸውን ማስረዳታቸውን ተቀብሎ ወረድ ብሎ ደግሞ ተጠሪ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ሄለን ከምትባል ጓደኛው ጋር እንደሚኖር በምስክሮች ስላስረዳ በአመልካችና ተጠሪ መካከል ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ እንደ ባልና ሚስት ግንኙነት የሌለ ስለመሆኑ ወስኗል፡፡ ይሁንና በፍርዱ የላይኛው ክፍል ግንኙነቱ እንደነበር ፍርድ ቤቱ መቀበሉ ተመልክቶ ዝቅ ብሎ ደግሞ ግንኙነቱ የለም በሚል መወሰኑ ሲታይ ፍርድ ቤቱ በምክንያት የተደገፈ ውሳኔ አለመሰጠቱንና ፍርዱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ

182(1) ስር በተመለከተው አግባብ አለመሰጠቱን የሚያሳይ ነው፡፡ ቀለብን በተመለከተም በተመሳሳይ ዝርዝር የማስረጃ ምዘና ሳይደረግና እና የግራቀኙ ገቢና የመክፈል አቅም ከማስረጃው አንፃር ተመርምሮ በምክንያት የተደገፈ ውሳኔ ሊሰጥ ሲገባ እንዲሁ ሀሳባቸውን ከነባራዊ ሁኔታው ጋር አገናዝቤያለሁ በማለት በየወሩ 6500.00 (ስድስት ሺህ አምስት መቶ) ብር እንዲከፈል መወሰኑ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡

በአጠቃላይ ግራቀኙ ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃ በዝርዝር መታየት አለመታየቱን፤ ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃ ተቀባይነት የለውም የሚባል ቢሆን እንኳ ምክንያቶቹ በግልጽ በውሳኔው ተመልክተው ፍርድ መሰጠቱን ውሳኔው አያሳይም፡፡ ይህ ደግሞ ከፍሲል የተጠቀሰውን ክርክሩ የሚመራበትን ስርዓት የተከተለ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

ስለሆነም ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር በአግባቡ ታይቶና ከማስረጃው ጋር ተመርምሮ ህጉን መሰረት ያደረገ በዝርዝር ምክንያት የተደገፈ ውሳኔ ሊሰጥ ሲገባ በዚህ አግባብ ሳይታይ እና ሳይመረመር የሚሰጥ ውሳኔ የህግ መሰረት ያለው ባለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በየደረጃው የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 105702 በቀን 24/06/2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 268854 በቀን 08/11/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤ የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የግራቀኙን ክርክር ካቀረቡት ማስረጃ አንፃር በመመርመርና አስፈላጊ ከሆነም በተጨማሪ ማስረጃዎች በማጣራት

፤ተቀባይነት የለውም የሚባል ክርክርና ማስረጃ ቢኖር ምክንያቱን በውሳኔው በግልፅ በማስፈር፤ የቀለብ ክፍያውን በተመለከተም ገቢያቸውን በአግባቡ አጣርቶ በምክንያት የተደገፈ ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይድረሰው፡፡

3. በዚህ ፍርድ ቤት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ.መ.ቁ 212598

ቀን ግንቦት 25 2014ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡ ወ/ሮ ያስሚን ፉአድ አብዱላሂ

ተጠሪ፡ አቶ ነጂብ አብዱላሂ ዩሱፍ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ በኮ/መ/ቁ 37065 በ21/11/12ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ 259337 በ18/10/13ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ7/12/13ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካች ከተጠሪ ጋር በ6/6/00ዓ.ም የተፈጸመው ጋብቻቸው በ21/4/09ዓ.ም በፍቺ ውሳኔ መፍረሱን ተከትሎ በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት የንብረት ክፍፍል ክስ በቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 03 ውስጥ የሚገኝ የቤ.ቁ 94/96 የሆነ ባለአምስት ፎቅ ህንጻ በጋብቻ ወቅት የተፈራ በመሆኑ የጋራ ነው ይባልልን፣ ተጠሪ በዚሁ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ላይ ከ1/8/08ዓ.ም ጀምሮ ለብቻው የሚኖር በመሆኑ አላግባብ የበለጸገበትን ግማሽ ገንዘብ ለአመልካች እንዲከፍል እንዲወሰንልኝ በማለት

ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ሌሎች ንብረቶችንም በመዘርዘር ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችንም አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የተጠሪን መልስ ከተቀበለ፤ ግራቀኙን በቃል ካከራከረ እና የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ከሰነድ ማስረጃዎች ጋር ጉዳዩን መርምሮ በተጠሪ ስም ተመዘግቦ የሚገኘው በቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 03 የቤ.ቁ 94/96 የሆነው ህንጻ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሀብት ነው፤ ቤቱን እንዲካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ተጠሪ በህንጻው ላይ በመኖር አላግባብ የበለጸገ በመሆኑ ኪራዩ ታስቦ ይከፈለኝ ያሉትን በተመለከተ ተጠሪ በህንጻው ላይ በመኖሩ ምክንያት ለአመልካች ኪራይ ታስቦ ሊከፍል ስለማይገባ ጥያቄው ተገቢነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ በሌሎች ጉዳዮች ላይም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ከላይ በተገለጸው የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሀብት ነው በተባለው ህንጻ 5ኛ ፎቅ ላይ ተጠሪ በመኖር አላግባብ የበለጸገ በመሆኑ ኪራዩ ታስቦ ይከፈለኝ ሲሉ ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በሰጠው ውሳኔ፤ ወጪና ኪሳራን በተመለከተ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት እንዲሁም በክፍያዎች ላይ ወለድ ይከፈል መባል ነበረበት በሚል ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ተጠሪ ህንጻውን ይዞ የሚኖር ስለሆነ የኪራይ ገቢ ብር 32,000.00 እንዲሆን ከንብረት አስተዳዳሪ ጋር የተስማሙ በመሆኑ ከመስከረም ወር 2013ዓ.ም ጀምሮ ያለው የኪራይ ገንዘብ ግማሹና ተጠሪ ከሚኖሩበት የኪራይ ገቢ ላይ ብር 848,000.00 ይካፈሉ መባል ሲገባው የስር ፍ/ቤት በዝምታ አልፎታል በማለት ተከራክረው እንዲሁም ሌሎች ቅሬታዎችን አቅርበው ፍ/ቤቱም የተጠሪን መልስ ከተቀበለ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ህንጻውን ይዞ ለኖረበት የኪራይ ገቢን በተመለከተ፤ ወጪና ኪሳራን በተመለከተ እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት፤ የጋራ ንብረት ክርክር ላይ ወለድ የሚጠቅበት የህግ ስርአት የለም በማለት እንዲሁም የስር ፍ/ቤት የሰጣቸውን ሌሎች ውሳኔዎች በከፊል በመሻር ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን በቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 03 ውስጥ የሚገኝ የቤ.ቁ 94/96 የሆነ ባለአምስት ፎቅ ህንጻ ተጠሪ በዚሁ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ላይ ከ1/8/08ዓ.ም ጀምሮ ለብቻው የሚኖር በመሆኑ አላግባብ የበለጸገበትን ግማሽ ገንዘብ ለአመልካች እንዲከፍል እንዲወሰንልኝ ሲሉ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ላይ እንዲሁም ወጪና ኪሳራ እና ወለድን በተመለከተ የተሰጡትን ውሳኔዎች በመቃወም ሲሆን ይዘቱም በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 87 እና 88 መሰረት ተጠሪ የአመልካች እና የተጠሪ ንብረት የሆነውን በቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 03 የቤ.ቁ 094/096 የሆነውን ህንጻ በተመለከተ አመልካች እና ተጠሪ አብረው ሲኖሩበት የነበረውን ቤት ከሰኔ 1 ቀን 2008ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪ ብቻውን ሲኖርበት የነበረ ሲሆን የዚህ ቤት የኪራይ ዋጋ በንብረት አስተዳዳሪው በ27/11/09ዓ.ም ተሰይሞ ንብረቱን እያስተዳደረው የሚገኝ ሲሆን የንብረት አስተዳዳሪው ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በ25/12/09ዓ.ም ሪፖርት አቅርበው በ29/12/09ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ተጠሪ ከቤቱ እንዲለቅ ወይም ኪራይ እንዲከፍል ታዟል፡፡ ይህን ተከትሎ ንብረት አስተዳዳሪ በ16/4/10ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት የቤቱ የኪራይ ዋጋ ብር 32,000.00 ስለሆነ ብር 16,000.00 ለአመልካች ታሳቢ እየተደረገ እንዲኖሩ እንዲደረግ ጠይቀው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በ21/6/10ዓ.ም በዋለው ችሎት የቤት የኪራይ ገንዘብ ታሳቢ ተደርጎ እየተመዘገበ ተጠሪ እንዲኖሩ ተፈቅዶላቸው ለወደፊቱ ትእዛዝ እንደሚሰጥበት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ፍ/ቤቱ ከቤት ኪራይ አንጻር በሰጠው ፍርድ ንብረቱ የጋራ ስለሆነ ተጠሪ ለኖሩበት ለአመልካች ሊከፍሉ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ እና በዚህ ላይ ያቀረብነውን ይግባኝ የፌ/ከ/ፍ/ቤት ምንም ሳይል ማለፉ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡

ተጠሪ ተገቢነት የሌለው ክርክር በማቅረብ ጉዳዩ ረጅም ግዜ እንዲወስድ ያደረገ በመሆኑ ለአመልካች ወጪና ኪሳራ የመክፈል ግዴታ እያለበት ተቻችሎ መባሉ አግባብ ካለመሆኑም በላይ በገንዘብ ሊከፈሉ የሚገባቸው እዳዎችን መክፈል ካለባቸው ግዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ተጠሪ ለአመልካች መክፈል ሲገባቸው የስር ፍ/ቤቶች አይከፈሉም ማለታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሻሽሎ ተጠሪ አላግባብ ለበለጸገበት እና በኪራይ ለኖረበት በወር ብር 16,000.00 ለአመልካች እንዲከፍል እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡

ይህ አቤቱታቸው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የስር ፍ/ቤት ተጠሪ የቤት ኪራይ ታስቦ የሚከፍል መሆኑ የካቲት 21 2010 በመ.ቁ 37065 ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ በመጨረሻ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም ሆነ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ሳያሳርፉበት ማለፉ አግባብ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ21/4/14ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ በ17/5/14ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲጸና ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በ4/6/14ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ፤ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የፍ/ብ/ህ/ቁ 1263 እያንዳንዱ የጋራ ባለሀብት ሀብቱ እንዲያገለግል በተመደበበት ነገር መሰረትና ከሌሎቹ የጋራ ባለሀብቶች ጋር ተስማሚ በሚሆንበት መንገድ የአንድነት በሆነው ንብረት ሊገለገል/ሊጠቀም እንደሚችል ደንግጓል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በተያዘው ጉዳይ የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካች እና ተጠሪ የንብረት ክፍፍል ክርክር ሂደት ወቅት የንብረት አስተዳዳሪ በ16/4/10ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ተጠሪ በሚኖሩበት ቤት ኪራይ እንዲከፍሉ በታዘዘው መሰረት ቤቱ ብር 32,000.00 ተገምቶ የአመልካችን ድርሻ ብር 16,000.00 ገቢ እንዲያደርጉ ተጠይቀው ስላልከፈሉ ትእዛዝ ይሰጥልኝ ሲሉ ባቀረቡት አቤቱታ ላይ ፍ/ቤቱ የግራቀኙን አስተያየት ከተቀበለ በኋላ አቤቱታውን መርምሮ በ29/12/09ዓ.ም ተጠሪ ጉዳዩ እልባት እስኪያገኝ ድረስ እየኖሩበት ያለውን ቤት ለቀው እንዲወጡ ወይም ኪራይ በመክፈል እንዲጠቀሙ በሚል ትእዛዝ መሰጠቱን ከገለጸ በኋላ የኪራዩን አከፋፈል በተመለከተ ደግሞ ተጠሪ አቅም ስለሌለኝ በየወሩ ያለው ተመዝግቦ ንብረቱ የጋራ ነው ከተባለ እንድከፍል ይደረግልኝ ሲሉ የጠየቁት አግባብነት ያለው እና የአመልካችን መብት የማይጎዳ በመሆኑ ተጠሪ በየወሩ የሚደርስባቸውን የቤት ኪራይ ገንዘብ መጠን ተመዝግቦ እንዲያዝና ወደፊት ውሳኔ እንዲያርፍበት ማድረግ የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል በማለት በ21/6/10ዓ.ም ትእዛዝ መስጠቱን ከዚህ የሰበር መዝገብ ጋር የተያያዘው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ 37065 በ21/6/10ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ይዘት የሚያስገነዝብ ነው፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የንብረት ክፍፍል ክርክሩን መርምሮ በ21/11/12ዓ.ም ውሳኔ ሲሰጥ በቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 3 የሚገኘው የቤ.ቁ 94/96 የሆነው ባለአምስት ፎቅ ህንጻ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሀብት ነው በማለት ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ቤቱ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሀብት በሆነበት ሁኔታ የጋራ ሀብታቸው በሆነው ህንጻ 5ኛ ፎቅ ላይ ተጠሪ በመኖራቸው የኪራይ ገንዘብ ይክፈሉ የሚባልበት የህግ መሰረት ባለመኖሩ ከዚህ አንጻር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች ተጠሪ በህንጻው ከ1/8/08ዓ.ም ጀምሮ ለብቻው የሚኖር በመሆኑ አላግባብ የበለጸገበትን ግማሽ ገንዘብ እንዲከፍለኝ ሲሉ ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ተጠሪ በህንጻው ላይ በመኖሩ ምክንያት ለአመልካች ኪራይ ታስቦ ሊከፍል አይገባም በማለት ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በማጽናት የሰጠውን ውሳኔ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ በኮ/መ/ቁ 37065 በ21/11/12ዓ.ም ተጠሪ በቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 3 የሚገኘው የቤ.ቁ 94/96 የሆነው ህንጻ 5ኛ ፎቅ ላይ በመኖሩ ምክንያት ለአመልካች ኪራይ ታስቦ ሊከፍል አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ 259337 በ18/10/13ዓ.ም በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንተዋል፡፡

2. ከላይ በተ.ቁ 1 ላይ ከተገለጸው ነጥብ ውጪ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ በኮ/መ/ቁ 37065 በ21/11/12ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ 259337 በ18/10/13ዓ.ም በሌሎች ጉዳዮች ላይ የሰጡት የውሳኔ ክፍልም አልተነካም፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 212603

ሰኔ 02 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- የኢትዮጵያ አየር መንገድ

ተጠሪ- አቶ ተከስተ ካሴ

መዝገቡ ተመርመሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ስንብትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ተጠሪ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ውስጥ እ.አ.አ. ከቀን 22/04/2020 ዓ.ም ጀምሮ በወር ብር 42,863.37 እየተከፈለኝ በአውሮፕላን ጥገና አሰልጣኝነት ሳገለግል ቆይቻለሁ፡፡ ከመስከረም 10 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ በድርጅቱ ውስጥ በተቋቋመው የሰራተኛ ማህበር ውስጥ ምክትል ፀኃፊ በመሆን እያለገልኩ ቆይቻለሁ፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ስለእኔ እውነት ያልሆነ መረጃ በማስተላለፍ ስም እና ዝናዬን አጥፍተሃል፣ ከሌሎች ሰራተኞች ጋር በስራ ቦታ መተባበር እና ሰላማዊ የስራ ግንኙነት እንዳይኖር አድርገሃል በማለት የስራ ውሌን አቋርጦታል፡፡ ከስራ ስሰናበት በህብረት ስምምነቱ መሠረት በተቋቋመው ኮሚቴው ውስጥ የሰራተኛ ማህበር ተወካይ አልነበረም፡፡ ስለሆነም ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ተብሎ ያልተከፈለኝ ደሞዝ ተከፍሎኝ ወደ ስራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ፤ ወደ ስራ ልመለስ የማልችልበት አግባብ ካለ ደግሞ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የሚያዝያ ወር ሙሉ ደሞዝ፣ እ.አ.አ. የ2020 ዓ.ም የዓመት እረፍት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ክፍያ እንዲከፍለኝ እና የስራ ልምድ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ።

አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ ተጠሪን ከስራ ያሰናበትናቸው የሰራተኛ ማህበር አባል በመሆናቸው ሳይሆን የመገናኛ ብዙሀንን በመጠቀም በድርጅታችን መልካም ስም እና ዝና ላይ የስም ማጥፋ ዘመቻ በማካሄዳቸውና በስራ ቦታ ላይ ሊኖር የሚገባውን መልካም የስራ ግንኙነት እና መግባባት የሚያበላሽ ተግባር በመፈፀማቸው ነው፤ ለአብነት ያህል የኛ ቲዩብ ከተባለ ሚዲያ ጋር ባደረጉት ቃለ-ምልልስ አመልካች ድርጅት ሰራተኛ ሲቀጥርም ሆነ ሲያሰናብት መርህ የለውም፣ የድርጅት ሰራተኞች ለድርጅቱ አመራሮች ብቻ ተገዢ እንዲሆኑ ነው የሚሰራው፤ ድርጅቱም ሆነ አመራሩ የሚያስበው ለውጪ ሃገር ዜጎች እንጂ ኢትዮጵያዊ ለሆነው ሰራተኛ አይደለም፤ የኮቪድ 19 ስርጭትን እንደ መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ ሰራተኞችን በመቅጣት በፍርሃትና በመርበትበት እንዲኖር እያደረገ ነው ሲሉ ስም አጥፍተዋል፤ ይህ የተጠሪ ድርጊት ከስራ የሚያስናብት በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው፤ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው እንኳን ቢባል በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው መተማመን በእጅጉ የሻከረ በመሆኑ ተጠሪ ወደ ስራ ሊመለሱ አይገባም በማለት ተከራክሯል።

ጉዳዩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ የሰጡት ቃለ-ምልልስ የአመልካች ድርጅትን ስም የሚያጠፋ፣ መልካም ስምና ዝና የሚያጎድፍ ወይም የሚያጥላላ ሳይሆን ያላቸውን የመናገር ነፃነት ተጠቅመው ያደረጉት እንደሆነ ከይዘቱ መረዳት ተችሏል፤ አመልካች በዚህ ምክንያት ተጠሪን ከስራ ማሰናበቱ ህገ-ወጥ ስለሆነ ተጠሪ የስድስት ወር ውዝፍ ደሞዝ ብር 257,174.22 ተከፍሏቸው ወደ ስራቸው ይመለሱ በማለት ወስኗል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 377 መሠረት ተሠርዞበታል። ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

አመልካች በቀን 07/12/2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው 08 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያላቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙለት ጠይቋል። የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ማህበር ጣልቃ መግባትን የሚመለከተውን ክስ ከተጠሪ ስንብት ጥያቄ ጋር አጣምረው ማቅረባቸው ተገቢ ነው ማለቱ፤ ተጠሪ ቃለ-ምልልስ ያደረጉት በግላቸው ሳይሆን ማህበሩን ወክለው ነው መባሉ፤ ቃለ-ምልልሱ የተጋነነ ቢሆንም ካለው ሁኔታ አንፃር እውነት መሆኑን መረዳት ይቻልል ሲል የስር ፍርድ ቤት በደፈናው ድምዳሜ ላይ መድረሱ፤ እንዲሁም ተጠሪ ወደ ስራ እንዲመለሱ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የአመልካች እና የተጠሪን የሻከረ የስራ ግንኙነት ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም ይገበዋል የሚል ነው።

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በግራ ቀኙ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት ተጠሪ ወደ ስራ ይመለሱ በማለት የተወሰነበት አግባብ መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል። በዚሁም መሠረት አመልካች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ በቀን 15/02/2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ ተጠሪ ንግግሩን ያደረጉት ከማህበሩ በተሰጣቸው ውክልና እንጂ በራሳቸው አይደለም፤ አመልካችም የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011

አንቀጽ 26 በመተላለፍ የሰጠው ስንብት አግባብ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ሲል ውሳኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው፤ ተጠሪ በቃለ-ምልልስ ወቅት ያነሳኋቸው ጉዳዮች እውነት መሆናቸውን በማስረጃ ጭምር በስር ፍርድ ቤት አረጋግጫለሁ፤ ተጠሪ ያደረጉት እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ከማህበሩ በተሰጣቸው ውክልና ላይ የተመሠረተ ሲሆን በግላቸው ከአመልካች ጋር ምንም አይነት የሻከረ ግንኙነትም ሆነ መቃቃር በሌለበት አመልካች የተበላሸ የስራ ግንኙነት ያለን በመሆኑ ወደ ስራ ሊመለስ አይገባም ማለቱ ተገቢ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀው ተከራክረዋል። አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቶ ተከራክሯል።

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ መሆን አለመሆኑን? ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመለሱ መወሰኑ ተገቢነቱን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል።

የመጀመሪያውን ጭብጥ እንደመረመርነው ተጠሪ በሕገ-ወጥ መንገድ አመልካች ከሥራ አሰናብቶኛል በማለት ውዝፍ ደመወዝ በመክፈል ወደሥራ እንዲመለስላቸው፤ ይህ ካልሆነም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን አመልካች በበኩሉ ተጠሪ የአመልካች ተግባር ያልሆነውን ሀሰተኛ መረጃ በመገናኛ ብዙኃን በመግለጽ መልካም ስምና ዝናውን የሚያጎድፍ ተግባር በመፈጸማቸውና ንብረት ጥቅሙ ላይ ጉዳት በማድረሳቸው ምክንያት የሥራ ውላቸው የተቋረጠ ስለሆነ የሥራ ሥንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል። በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሠረት የሥራ ውል የሚቋረጠው አንደኛው በሕግ ወይም በሥምምነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተዋዋይ ወገኖች አነሳሽነት ነው። በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 24 በሕግ መሠረት ውል የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች ተዘርዝረዋል። የአዋጁ አንቀጽ 25 ደግሞ በሥምምነት ውል ስለሚቋረጥበት ሁኔታ ይገልጻል። በአሠሪው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበት ሁኔታ በአዋጁ ከአንቀጽ 26-30 በዝርዝር ተመልክቷል። የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 31 እና 32 ደግሞ በሠራተኛው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበትን ሁኔታ ደንግጓል። የአዋጁ ድንጋጌ አንቀጽ 31 በአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ለአሠሪው በመስጠት ሠራተኛው ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል የሚገልጽ ነው። ሌላው በሠራተኛው አነሳሽነት የሚፈጸም የሥራ ውል ማቋረጥ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 32(1)(ሀ እስከ ሐ) የተመለከተ ሲሆን በሕጉ የተዘረዘሩት ምክንያቶች አሠሪው የሠራተኛውን ሠብዓዊ ክብርና ሞራል መንካቱ፣ በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር በሠራተኛው ላይ መፈጸም፣ ለሠራተኛው ደኅንነት ወይም ጤንነት አደጋ ሊያደርስ የሚችል ምክንያት እያለ አሠሪው ተገቢውን እርምጃ ካልወሰደ ወይም ሌላ አሠሪው ለሠራተኛው መፈጸም ያለበትን ግዴታ በመደጋገም ካልፈጸመ ሠራተኛው ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ማቋረጥ የሚችልበትን ሁኔታ አስቀምጧል። ከእነዚህ ማዕቀፎች ውጭ አሠሪው ሠራተኛን ከሥራ ሲያሰናብት ሕገ-ወጥ የሥራ ስንብት ይሆናል።

ሠራተኛ የአሠሪው ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያደርስ ተግባር ከፈጸመ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብተው የሚችል ድርጊት ስለመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1)(ሸ) ላይ ተመልክቷል፡፡ የአሠሪውን ሥም ማጥፋትም ሥራው ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ድርጊት በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ ማዕቀፍ ሊታይ የሚችል ነው፡፡ አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ በሠራተኛ ማሕበር አመራርነታቸው ሳይሆን በመገናኛ ብዙኃን በመቀጠም የአመልካች ደርጅት መልካም ስምና ዝና ላይ ሀሰተኛ የሥም ማጥፋት ዘመቻ የሚያካሂድ ቡድን ላይ ዋና ተዋናይ ሆነው አመልካች የሠራተኛውን ክብር የማይጠበቅ፣ ሕገ-ወጥ ፖሊሲ ተቀርጾ ሠራተኛ ላይ በደል እንደሚፈጸም፣ አመራሩ ከሕግ በላይ ነን የሚሉና በማን አለበኝነት መንፈስ የሚመሩ ግለሰቦች ናቸው፣ ሕግን ያልተከተለ የውጭ ምደባ እንደሚደረግ፣ ምደባ በሥራ አፈጻጸም ሳይሆን ከአመራር ጋር ባለ ቀረቤታና ቁርኝት እንደሚፈጸም፣ የበረራ አስተናጋጆች ከቀረጥ ነጻ የሚያስገቧቸው ዕቃዎች ላይ ያልተገባ ድጋሜ ክፍያ እንደሚፈጸም በማለት ሀሰተኛ እና ስም የሚያጠፋ መረጃ ሰጥቷል የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸውበሠራተኞች ማሕበር ውስጥ በምክትል ሊቀመንበርነት ቦታ እየሰራሁ እያለ ማሕበሩን በመወከል የተገለጸ ነው፣ የአመልካችን ስም የሚያጎድፍ ሆነ የሠራተኛውን ሰላማዊ ግንኙነት የሚያጠፋ ተግባር ባልተፈጸመበት የተሳሳተ መረጃ ሰጥተሃል፣ ሰላማዊ የሆነ የሥራ ግንኙነት እንዳይኖር አድርገሃል በማለት ከግንቦት 04 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ከስራ ማሰናበቱ ሕገ-ወጥ ስንብት ነው የሚል ነው፡፡

የማስረዳት ደረጃ ከሁለቱ ወገን የተሻለ ያስረዳው ማን ነው (preponderance of evidence) የሚለውን በመለየት፣ የማስረጃ ተገቢነት (relevancy test)፣ የማስረጃው ተቀባይነትን (admissibility) ደንቦችን መከተል እና ለማስረጃው የሚሰጠውን ክብደት (weight of evidence) በመለየት የመወሰን ኃላፊነት ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ቤቶች ዋና ተግባር ነው፡፡ ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃ ለመመዘን ኃላፊነት የተሰጠው የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ በመስማትና ተጠሪ የሰጡትን ቃለምልልስ ሲዲውን አስቀርቦ በመመልከት ተጠሪ ቃለ ምልልሱን ያደረጉት በሠራተኛ ማሕበሩ ተዋካይ በመሆናቸዉ እንጂ በግል ያደረጉት አይደለም፣ በተጨማሪም በሰዓቱ ተጠሪ ሲናገሩ የነበሩት በግላቸዉ ስለደረሰባቸዉ በደል ሳይሆን ሠራተኛዉ በአጠቃላይ ችግሮች አሉበት የሚል ይዘት ያለዉ መሆኑን እና ተተሪ በቃለ ምልልሱ የገለፃቸዉ ጉዳዮች አለመከሰታቸዉን አመልካች ያስረዳበት ሁኔታ አለመኖሩን፣ ተጠሪ በቃለ ምልልሱ የተናገሩት የግል አስተያየታቸዉ ነዉ ቢባ እንኳን የአመልካችን ድርጅት ስም የሚጠፋ እና የሚያጥላላ ሳይሆን ተጠሪ ያላቸዉን የመናገር ነፃነት ተጠቅመዉ ያደረጉት እንደሆነ ከይዘቱ መረዳቱን ጠቅሶ ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ በሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የማስረጃ ምዘና መርሕ ስህተት የፈጸመ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት በሰኔ 04 ቀን 2004 ዓ/ም በተደረገው የሕብረት ሥምምነት አባሪ ክፍል አንድ ንዑስ ክፍል ሀ ተራ ቁጥር 3 ላይ የተሳሳተ መረጃ በመስጠት ስምና ዝና የሚያጎድፍ፣

መልካም ግንኙነት የሚሻክር ከባድ ጥፋት መፈጸሙ ሆነ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1)(ሸ) ድንጋጌ መጣሱን የሚያስረዳ ሳይሆን ተጠሪ የማሕበሩ ተወካይ በመሆናቸዉ በማሕበሩ አባላት ላይ ደርሰዋል ያሉትን የመብት ጥሰቶችና ግድፈቶች በመግለጻቸው ከሥራ መሰናበታቸው ሕገ-ወጥ የሥራ ስንብት ነው በማለት መወሰኑ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አላገኘንበትም፡፡

ወደሁለተኛው ጭብጥ ስንመለስ ተጠሪ ወደሥራቸው እንዲመለሱ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በሚል የቀረበውን የሠበር አቤቱታ የሚመለከት ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 43(1)(2) የሥራ ውሉ ከሕግ ውጭ በአሠሪው የተቋረጠበት ሠራተኛ ወደሥራው እንዲመለስ ሊወሰን እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ሠራተኛው ወደሥራ ሊመለስ የማይችለው ከሥራው ጠባይ ግንኙነት የተነሳ ወይም ከክርክር ሂደት ከወሰደው ግንዛቤ በሥራ ቢቀጥል ከፍተኛ ችግር ያስከትላል ተብሎ በፍርድ ቤቱ ሲታመን እንደሆነ የአዋጁ አንቀጽ 43(3) ላይ ተደንግጓል፡፡ ከፍተኛ ችግር የሚለው የሕጉ አነጋገር ማንኛውንም ዓይነት ጉዳት ሠራተኛውን ወደሥራው እንዳይመለስ ማድረግ የማይችል መሆኑን እና የሚያስከትለው ጉዳት ጉልህ የሆነ መሆን እንዳለበት ያሳያል፡፡ ይህም ሕግ አውጭው በአንድ በኩል የሥራ ዋስትና ማረጋገጥ ለሠራተኛው ሆነ ለሀገር መሠረት የሆነውን የሠራተኛውን ቤተሰብ መጠበቅ እንዳለበት ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ሲያሳይ በሌላ በኩል የሥራ ሁኔታውን እና የኢንዱስትሪውን ሠላም ማስጠበቅ ለምርታማነት መሠረት መሆኑን በመገንዘብ በሁለቱ አሳቤዎች መካከል ጉዳዩ እንዲገዛ የፖሊሲ ውሳኔ ላይ መድረሱን እና ጉዳዩም የፍርድ ቤት ፍቅድ ሥልጣን መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ፍርድ ቤት ፍቅድ ሥልጣን ምክንያታዊ በሆነ አግባብ እንዲጠቀም ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ግራቀኙ ተከራካሪዎችም በተለይም አሠሪው ፍርድ ቤቱን ለማሳመን ሠራተኛው ወደሥራ ቢመለስ የሚስከትለውን ጉልህ የሆነ ጉዳት ማሳየት ይኖርበታል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ድርጅት የአውሮፕላን ጥገና ባለሙያ ሲሆኑ ከአመልካች አስተዳደር ጋር አለመግባባት መኖሩ ከሥራ ድርሻቸው አንጻር ወደሥራ መመለሳቸው አመልካች ላይ ጉልሕ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን የሚያሳይ አይደለም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 37454 የሠጠው አስገዳጅ ትርጉም ሠራተኛው የጥበቃ ሠራተኛ መሆኑ እንዲሁም ከአለቆቹ ጋር በተለያየ ጊዜ ግጭት የሚፈጥር መሆኑና በእጁም ትጥቅ ያለ መሆኑ የሥራ ውሉን ለማስቀጠል የማይቻል መሆኑን የሚያስረዳ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንዲሁም የአሠሪው ሠላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል ድርጅትን ጠቅላላ ንብረት ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነት ያለበት ሠው መሆኑን ግምት ወስጥ በማስገባት ወደሥራ ሊመለስ እንደማይገባ የተወሰነበት ነው፡፡ እንዲሁም በሰ/መ/ቁ. 64079 የተወሰነውም ገንዘብ ጋር ግንኙነት ያለው ሠራተኛ መሆኑን በመገንዘብና ጥፋት ፈጽሟል የተባው ከሥራ ኃለፊነቱ ጋር በተያያዘ በመሆኑ፤ ከአሠሪው ጋር ያለው መተማመን ከቀነስ ባለበት ኃላፊነት ወደሥራ መመለስ መልካም የሥራ ግንኙነት አይፈጥርም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ ከሥራ ኃላፊነቱ ጋር የተያያዘ ጥፋት ፈጽሟል ያልተባለ በመሆኑና ቀደም ሲል በዚህ ችሎት ከተወሰኑት ጉዳዮች ጋር የፍሬ ነገር ልዩነት ያለው ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ወደሥራ ቢመለሱ ሥራው ላይ ያለው ከፍተኛ ጉዳትን አመልካች ያላሳየ ስለሆነ

በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተጠሪ ወደሥራ እንዲመለሱ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም ብለናል። በሌላ በኩል በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 43(5) መሠረት ተጠሪ ወደሥራው እንዲመለስ የተሰጠው ውሳኔ በዚህ ችሎት ታይቶ የጸና በመሆኑ የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደሥራ ሊመለሱ ይገባል ብለናል።

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 117180 ላይ ህዳር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ነበዋለዉ ችሎት እንዲሁም ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በመዝገብ ቁጥር 274582 ላይ ሐምሌ 09 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል።
2. ተጠሪ የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደሥራ ሊመለሱ ይገባል በማለት ወስነናል።
3. የሰበር አጣሪ ችሎት ጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል።
4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰበር መ.ቁ 212620

ቀን፡- 18/4/2014 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ከድር አልይ

ሱልጣን አባተማም

ዋዚሞ ዋሲራ

አመልካች፡ቾች- እነ አበበ ጨዶ /26 ሰዎች/ ጠበቃ ሲሳይ ገመቹ ቀረቡ

ተጠሪ፡/ዎች- እነ አርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ አስ/ፅ/ቤት /3 ሰዎች/

መዝገቡ ለዚህ ችሎት 10/12/2013 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 35305 በ ግንቦት 18 ቀን 2013 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ገልፆ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ባቀረበው ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ በዚህ መሰረት መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ትእዛዝ ሰጥተናል፡፡

ትዕዛዝ

ለክርክሩ ምክንያት የሆኑ ይዞታዎችን አመልካቾች 1987 ዓ.ም ጀምሮ በመያዝ ከ 26 ዓመት በላይ ያለው መሆናቸው ተጣርቶ ከሚመለከተው አካላት መግለጫዎች ቀርቦ እያለ ከይዞታቸውና ከንብረቶቻቸው በሚያፈናቅል ሁኔታ እንድለቁ የተወሰነባትን አግባብ የፌ/ጠ/ፍ/ቤትሰበርሰሚችሎት በመ/ቁ 37391፣ 47252፣107217፣77983፣37184፣33945 ከሰጠው የሕግ ትርጎሞች እና መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርሆች እንዲሁም ከክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ጋር በማገናዘብ

መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ብለናል፡፡

1.መጥሪያ ለተጠሪ/ዎች/ ይድረስ ብለናል፡፡

2. ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክራቸውን በሬጅስትራር ፅ/ቤት በኩል ይቀባበሉ፡፡

3. ቀጠሮ ለ 09/05/2014 ዓ.ም ተቀጥሮአል፡፡ 5፡00 ሰዓት

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 212808

ሚያዝያ 26 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቢሲኒያ ባንክ አክስዮን ማህበር ፡- ወኪል ሰለሞን ሞገስ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ ዮናስ ለሚሳ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የኪራይ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የካቲት 2 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ክስ ከአቶ አክሊሉ አሰግደው ጋር በተደረገ የብድር እና የመያዣ ውል አመልካች በወ/ሮ ቅድስት ተፈራ ስም የተመዘገበን ህንጻ በመያዣነት በመያዝ ብር 40,000,000 (አርባ ሚሊዮን) አበድሯል፡፡ የመያዣ መብቱም በቢሾፍቱ ከተማ የመሬት ልማት እና ማኔጅመንት ኤጅንሲ ተመዝግቧል፡፡ ተባዳሪውም ብድሩን መክፈል ባለመቻሉ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት 2 ጊዜ የጨረታ ማስታወቂያ አውጥቶ ተጫራች ባለመቅረቡ ንብረቱን ሊረከብ ሲል ሌሎች

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተከራዮች የለቀቁ ቢሆንም ተጠሪ የያዘውን የህንፃውን የተወሰነ ክፍል ለመልቀቅ ፍቃደኛ ባለመሆኑ በ15 ቀናት ውስጥ እንዲለቅ አመልካች ሐምሌ 5 ቀን 2010 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥቶታል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ፍቃደኛ ስላልሆነ ቤቱን እንዲለቅ ከተጠየቀበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከተመሰረተበት ጊዜ ድረስ ያለው የ18 ወር የኪራይ ክፍያ በወር ብር 52,918.50 ታስቦ በድምሩ ብር 952,533.00 (ዘጠኝ መቶ ሀምሳ ሁለት ሺ አምስት መቶ ሰላሳ ሶስት) ቤቱን ለቆ እስኪያስረክብ ድረስ ታስቦ እንዲከፍል እና ቤቱን ለቆ እንዲያስረክብ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ የካቲት 18 ቀን 2012 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር ያቀረበ ሲሆን በመቃወሚያው አመልካች ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ከማቅረቡ በፊት በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀፅ 8(1) መሰረት የዚህ አይነቱን ጉዳይ ለማስፈጸም ስልጣን ላላው አካል ሊያቀርብ ስለሚገባ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም፤ ቤቱን አመልካች በዋስትና ከያዘበት የካቲት 13 ቀን 2009 ዓ.ም በፊት መስከረም 26 ቀን 2008 ዓ.ም እና ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ.ም ተጠሪ ከወ/ሮ ቅድስት ተፈራ ጋር በተደረገ የኪራይ ውል የያዝኩት እና የኪራይ ዘመኑን ክፍያ የፈፀምኩ ስለሆነ ልከሰስ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ በፍሬ ጉዳይ ላይ በሰጠው መልስ ተጠሪ ቤቱን በወር ብር 52,918.50 ለ10 ዓመት ከህንጻው ባለቤት ወ/ሮ ቅድስት ሽፈራው ላይ ስልጣን ባለው አካል በተመዘገበ የኪራይ ውል ተከራቼ ሙሉ የኪራይ ገንዘቡን ከፍያለሁ፤ አመልካችም ቤቱን በዋስትና ለመያዝ ሲመላለስ ተጠሪ በቤቱ ውስጥ ስራ የምሰራ መሆኑን እያወቀ በዋስትና የያዘው ስለሆነ ለክሱ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ በፍሬ ጉዳይ ላይ በሰጠው ውሳኔ የማይንቀሳቀስ ንብረት ኪራይ በ3ኛ ወገን ላይ ተፈፃሚነት የሚኖረው ስልጣን ባለው አካል ሲመዘገብ ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 2899(1) እና 1577 ላይ ተመላክቷል፡፡ የቤቱ ማህደር የሚገኝበት የቢሾፍቱ ከተማ መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት በቁጥር 8477/139/7 ጥቅምት 27 ቀን 2013 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ለክርክሩ መነሻ በሆነው የቤቱ ማህደር ውስጥ የኪራይ ውል ስምምነት የሌለ መሆኑን የገለፀ ሲሆን የከተማው ማዘጋጃ ቤትም ህዳር 11 ቀን 2013 ዓ.ም በቁጥር 07308/3628 በጻፈው ደብዳቤ ይሕንኑ በማጠናከር ማስረጃ ልኳል፡፡ ተጠሪም የኪራይ ውሉን በሚመለከተው አከል አስመዝግቤያለው በማለት የቀረጥ ቴምብር የከፈለባቸውን 2 ደረሰኞች በማስረጃነት ያቀረበ ቢሆንም ክፍያ መከፈሉን እንጂ የት እንደተከፈለ አያስረዱም፡፡ በተጨማሪም ተጠሪ ውሉ ተመዝግቧል ከሚል በቀር የት እንደተመዘገበ ገልጾ ያቀረበው መከራከሪያ ስለሌለ የኪራይ ውሉ አመልካች ላይ አስገዳጅነት ስለሌለው ቤቱን ለቆ ሊያስረክብ ይገባል፡፡ ነግር ግን ተጠሪ የኪራይ ውሉን ስልጣን ባለው አካል ተመዝግቦ ከቤቱ ማህድር ጋር እንዲያያዝ ባያደርግም በኪራይ ይዞ ሲገለገልበት የቆየ እና የኪራዩን ገንዘብ የቤቱ ባለቤት ለነበሩት ስለከፈለ አመልካች የኪራዩን ገንዘብ ከቤቱ ባለቤት ከሚጠይቅ በስተቀር ተጠሪ የኪራይ ገንዘብ ሊከፍል አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ይግባኙን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዟል፡፡

አመልካች ነሐሴ 13 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው ይህን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ ተጠሪ ከህንጻው ባለቤት ጋር ያደረገው የኪራይ ውል ስልጣን ባለው አካል አለመመዝገቡ እና በቤቱ ማህደር ውስጥ አለመያያዙ ተረጋግጦ በ3ኛ ወገን ላይ መቃወሚያ ሊያደርገው ስለማይገባ ቤቱን ለቆ ሊያስረክብ ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ ቤቱን ለቆ ማስረከብ የነበረበት በአመልካች እንዲለቀቅ ከተጠየቀበት ሐምሌ 5 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ እና በዚህ አግባብ ባለማስረከቡ አመልካች ያጣውን ጥቅም የቤቱን ኪራይ፣ ወጪ እና ኪሳራን ጨምሮ የመተካት ግዴታ የለበትም ተብሎ መወሰኑ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት በመያዣ ይዞ የብድር ገንዘብ ባለመመለሱ ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት 2 ጊዜ ጨረታ አውጥቶ ገዢ ባለመገኘቱ አመልካች ተረክቦት ተጠሪ ቤቱን ለመልቀቅ ፍቃደኛ ባለመሆኑ ምክንያት ተጠሪ የቤቱን ኪራይ ለአመልካች እንዲከፍል የቀረበን የዳኝነት ጥያቄ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ቤቱን የያዘው በኪራይ በመሆኑ የፈፀመው ጥፋት ስለሌለ የኪራይ ገንዘብ ሊከፍል አይገባም በማለት የወሰነበትን አግባብ ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልሱን እንዲያቀርብ ታዟል፡፡

ተጠሪም ጥር 2 ቀን 2014 ዓ.ም የተፃፈ መልሱን አቅርቧል፡፡ የመልሱ ይዘት ባጭሩ ክርክር የተነሳበትን ህንፃ ከአከራይ ቅድስት ተፈራ ጋር ባደረኩት ለ10 ዓመት በሚቆይ የኪራይ ውል ስምምነት የያዝኩት መሆኑን አስረድቻለሁ፡፡ የኪራይ ገንዘቡንም በቅድሚያ ለአከራይ ከፍያለሁ፡፡ በመሆኑም የቤት ኪራይ ለመክፍል ኃላፊነት ስለሌለብኝ በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ የተፈጸመ የሕግ ስህተት የለም የሚል ነው፡፡

አመልካች በበኩሉ ጥር 25 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ በስር ፍርድ ቤት ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

አመልካች በዋናነት የሚከራከረው በተጠሪ እና የቤቱ የቀድሞ ባለቤት መካከል የተደረገው የኪራይ ውል ስምምነት ስልጣን ባለው አካል ፊት የተመዘገበ ስላልሆነ ህንፃውን ለአመልካች ለቆ ሊያስረክብ ይገባል ከተባለ ተጠሪ ይህን ተግባራዊ ማድረግ ያለበት አመልካች ቤቱን እንዲለቅ ከጠየቀው ሐምሌ 5 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ እና በዚህ አግባብ ቤቱን ለአመልካች ስላላስረከበ የኪራይ ገንዘቡን እንዲከፍል ሊወሰን ይገባ ነበር በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ቤቱን የያዝኩት የቤቱ ባለቤት ከነበሩት ከወ/ሮ ቅድስት ተፈራ ጋር

ባደረኩት የኪራይ ውል ስምምነት ስለሆነ እና የኪራይ ገንዘብም ለኪራይ ዘመኑ በቅድሚያ ስለከፈልኩ በድጋሚ የኪራይ ገንዘብ ለአመልካች የመክፍል ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

ማንኛውም ሰው ሌላኛውን ወገን በኃፊነት ተጠያቂ በማድረግ ክፍያ እንዲፈፅም ወይም ሌላ ግዴታን እንዲወጣ መጠየቅ የሚችለው ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ መብት ሲኖረው መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1675፣ 2027 ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ ተመላክቷል፡፡

ከክርክሩ ሐደት መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ የህንፃው የቀድሞ ባለቤት ከሆኑት ወ/ሮ ቅድስት ተፈራ ጋር መስከረም 26 ቀን 2008 ዓ.ም እና ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ.ም በተደረገ የኪራይ ውል በጠቅላላው ለ10 ዓመት በኪራይ ይዞ እንዲገለገል መስማማታቸው፤ ይህ ውል የቤቱ ማህደር በሚገኝበት የቢሾፍቱ ከተማ የመሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ፅህፈት ቤት አለመመዝገቡ እና በቤቱ ማህደር ውስጥ አለመያያዙ እንዲሁም አመልካች ለአቶ አክሊሉ አሰግደው በሰጠው ብድር መነሻነት በዋስትና መያዙን፤ ግለሰቡ ብድሩን መክፈል ባለመቻሉ ምክንያት አመልካች ቤቱን በጨረታ ለመሸጥ 2 ጊዜ የጨረታ ማስታወቂያ አውጥቶ ተጫራች ባለመቅረቡ ቤቱን መረከቡ፣ ከዚህ በኋላ ተጠሪ ቤቱን እንዲያስረክብ ተጠይቆ ፍቃደኛ አለመሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረው በኪራይ የያዝኩት የህንጻ ክፍል ኪራይ ለቀድሞ አከራይ ስለከፈልኩ እና ይህም ስላልተካደ ለአመልካች የኪራይ ገንዘብ ልከፍል አይገባም በማለት ሲሆን አመልካች በበኩሉ የኪራይ ውሉ ስላልተመዘገበ 3ኛ ወገን ላይ አስገዳጅ አይደለም ከተባለ እንዲለቅ ካሳወቅኩበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ኪራይ እንዲከፍል መወሰን ነበረበት በማለት ተከራክሯል፡፡ ነገር ግን ተጠሪው የሕንፃ ክፍሉን ለ10 ዓመት ተከራይቶ ሙሉ ክፍያውን የቀድሞ የህንጻው ባለቤት ለነበሩት ወ/ሮ ቅድስት ተፈራ የከፈለ መሆኑን ጠቅሶ የሚያቀርበውን መከራከሪያ አመልካች ክዶ የሚያቀርበው መከራከሪያ የለም፡፡ ማንኛውም ሰው ሌላኛውን ወገን በኃላፊነት ተጠያቂ በማድረግ ክፍያ እንዲፈፅም ወይም ሌላ ግዴታን እንዲወጣ መጠየቅ የሚችለው ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ መብት ሲኖረው መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1675፣ 2027 ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ ተመላክቷል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች ህንጻውን በዋስትና በመያዝ የሰጠው ብድር ስላልተመለሰለት ህንጻውን በመረከብ ባለቤት የሆነበት በመሆኑ ተጠሪ የተከራየውን የህንጻ ክፍል የማስለቀቅ መብት እንዳለው በውሳኔ የተረጋገጠ ቢሆንም አመልካች ህንጻውን ከመረከቡ በፊት ተጠሪ ከቀድሞ የህንጻው ባለቤት ጋር የኪራይ ውል አድርጎ አስቀድሞ የኪራይ ገንዘብ መክፈሉ እስከተረጋገጠ ድረስ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች እስኪያስረክብ ላለው ጊዜ በድጋሚ ለአመልካች የኪራይ ገንዘብ እንዲከፍል የሚገደድበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ተጠሪ ቤቱን እንዲያስረክብ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሰረት ባለማስረከቡ አመልካች ያጣው ገቢ ቢኖር እንኳን አስቀድመው ቤቱን በማከራየት የኪራይ ገንዘብ የተቀበሉትን የቀድሞው የህንጻ ባለቤት እንዲከፍሉት ከሚጠይቅ በስተቀር ተጠሪ በድጋሚ የኪራይ ገንዘብ የሚከፍልበት አግባብ አይኖርም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በውል መነሻነት በወቅቱ ህጋዊ መብት ላላቸው የሕንፃው ባለቤት የከፈለውን የኪራይ ገንዘብ በድጋሜ እንዲከፍል የሚገድበት አግባብ ስለሌለ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች የኪራይ ገንዘብ እንዲከፈለው ያቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

<u>ውሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምስራቅ ምድብ ቋሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 329922 ህዳር 28 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 201877 ሰኔ 11 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348 መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ 212943

ግንቦት 22 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ወ/ሮ ፈለቀች ወንድማገኘሁ፡- ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ምስክር ወንድማገኘሁ፡- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በቀን 13/12/2013 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 374773 በቀን 19/09/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው።

ክርክሩ የጀመረው በስር የሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ ነው። የአሁን አመልካች በዚህ መዝገብ የሌሉት ብዙነህ ወንድማገኘሁ ተከሳሽ ነበሩ።

ተጠሪ በቀን 13/06/2011 ዓ.ም በጻፉት አቤቱታ ተከሳሾች የደም ዝምድና ሳይኖረንና እኔ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ሆኜ እያለሁ በሀሰት የወራሽነት ማስረጃ በመ/ቁ 54989 በቀን 20/03/2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት በመውሰድ ሻሸመኔ ከተማ አዋሾ ቀበሌ የሚገኝ ስፋቱ 350 ካ.ሜ የሆነ ቦታ ላይ የተገነባ ቤት ላይ መብቴን

በመጉዳት ላይ በመሆናቸው የተሰጣቸው የወራሽነት ማስረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 998 መሰረት እንዲሻርልኝ በማለት ጠይቀዋል።

የስር ተከሳሾች በቀን 12/09/2011 ዓ.ም በሰጡት መልስ ከሳሽ የሟች እናትና አባታችን ልጅ ሳይሆን እናቱ አቅመ ደካማ በመሆኗ 1ኛ ተከሳሽ ወደ ቤት አስገብታው እየረዳችው የወር ደሞዝ እየላከች ስታግዝ የነበረ እንጂ የሟች ልጅ አይደለም። ስለሆነም ከሳሽ ይህን አቤቱታ ለማቅረብ መብት ስለሌለው ክሱ ውድቅ እንዲደረግ። ከዚህ በተጨማሪም ከሳሽ ከዚህ ቀደም የወራሽነት ማስረጃ በመ/ቁ 54821 ወስዶ በሟች ስም በኢትዬጵያ ንግድ ባንክ ሻሸመኔ ቅርንጫፍ የሚገኘውን ገንዘብ ወጪ ያደረገ በመሆኑ ምን ያህል እንደሆነ ተጣርቶ ከሳሽ እንዲመልስ፤ ለከሳሽ የተሰጠው የወራሽነት ማስረጃም እንዲሻርልን በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ክርክሩንና የግራቀኙን ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃዎች መርምሮ ውሳኔ ሰጥቷል። በሰጠው ውሳኔ ተከሳሾች የሟች ልጅ መሆናቸው እና ከሟች መወለዳቸውን የቀረቡት የተከሳሾች ምስክሮች ከከሳሽ ምስክሮች በበለጠ አረጋግጠዋል። ከመዝገቡ ጋር የተያያዘው የሰነድ ማስረጃ የትምህርት ቤት እና ከእድር የቀረበ ማስረጃ ሲሆን 2ኛ ተከሳሽ በአቶ ወንድማገኝ እሸቱ ስም እንደምትጠራ የሚያሳይ እና የምስክሮችን ቃል የሚያጠናክር ነው። ስለሆነም የከሳሽ መስክሮች ቃል ከተከሳሾች ማስረጃ በልጦ የተከሳሾን የወራሽነት ማስረጃ ለማሻር የሚችል ባለመሆኑ ከሳሽ የቀረበው ክስ ውድቅ ተደርጓል። ተከሳሾች በመልሳቸው እንደ መስቀለኛ ክስ የጠቀሱትና ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የዳኝነት ክፍያ ያልተከፈለበትና የወራሽነት ማስረጃ በተሰጠበት መዝገብ ላይ የሚቀርብ ነው በማለት ውድቅ አድርጓል።

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ከመረመረ በኃላ የተጠሪ ምስክሮች የሟች ልጅ መሆናቸውን በአግባቡ መስክረዋል፤ ግራቀኙ በአንድ ቤት ውስጥ ያደጉ መሆናቸውም ተረጋግጧል፤ አባት (ሟች) ልጆቼ ብሎ በግልፅ የሞላው የሰነድ ማስረጃ የለም፤ የቀረቡት ማስረጃዎች በጠቅላላው ሲመዘን ግራቀኙ የሟች ወንድማገኝ እሸቴ ልጆች መሆናቸውን የሚያስገነዝብ ነው እንጂ አንድ ሰው ብቻ ልጅ መሆኑን ፍርድ ቤቱን ሊያሳምን በሚችል መልኩ ያረጋገጡት ነገር የለም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል።

ተጠሪ በዚህ ውሳኔም ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል። ፍርድ ቤቱ ክርክሩን መርምሮ በሰጠው ውሳኔ በምስክሮች 1ኛ ተከሳሽ በ1967 ዓ.ም፣ 2ኝኛ ተከሳሽ በ1967 ዓ.ም የተወለዱ መሆኑንና ከሟችና ባለቤታቸው መወለዳቸው ተመስክሯል፤ ነገር ግን 1ኛው ምስክር በወቅቱ የ10 ዓመት ልጅ የነበረ በመሆኑ ተከሳሾች ከሟች መወለዳቸውን ያውቃል የሚለው የሚያሳምን ሆኖ አልተገኘም፤

በስር ፍርድ ቤት ከጡረታ ኤጀንሲ ቀረበው የጽሁፍ ማስረጃም ሚች በመንግስት ሥራ ላይ ከ1943 ጀምሮ እስከ 1977 ዓ.ም ቆይተው ጥሮታ የወጡ ሲሆን በሞሉት የጥሮታ ቅጽ ላይ ተከሳሾች ልጆቼ ናቸው በማለት ያልሞሏቸው በመሆኑ ከሚች መወለዳቸው ጥርጣሬ የሚፈጥር ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉትን ውሳኔሽሯል።

ጉዳዩ በመጨረሻ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ችሎት በበኩሉ የአሁን አመልካችና የስር 2ኛ ተከሳሽ የሚች ወንድማገኝ እሸቴን ወራሽነት አስመልክቶ ያወጡት ማስረጃ መሰረዙ በአግባቡ ነው፤ ነገር ግን የሚች ባለቤት ወ/ሮ ጥሩነሽ ሆማን ወራሽነት አስመልክቶ ያወጡት ማስረጃን በተመለከተ ግን ተጠሪ የወ/ሮ ጥሩነሽ ሆማ ልጅ አለመሆኑና እናቱ 1ኛ ምስክሩ በመሆናቸው የሚቿ ልጅ ሳይሆን የወራሽነት ማስረጃ ለማሰረዝ ህጋዊ መብት የሌለው በመሆኑ ወ/ሮ ጥሩነሽ ሆማን አስመልክቶ ለአመልካችና ለስር 2ኛ ተከሳሽ የተሰጠው ማስረጃ መሰረዙ አላግባብ ነው በማለት ውሳኔውን አሻሽሏል።

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው። አመልካች ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ አመልካችና ተጠሪ በስር ፍ/ቤቶች በነበረን ክርክር ሚች ወላጅ አባቴ እንዲሁም ሚች ወላጅ እናቴ ጋብቻ መስርተው መኖር ከጀመሩ አንስቶ እስከ እለተ ሞታቸው ድረስ ሳይፋቱ እንዲሁም ሌላ ትዳር ሳይመሰርቱ መኖራቸውን ተማምነናል፤ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ከሚች ወላጆቼ እናቴ እና አባቴ መወለዴን ነው የሚያሳየው፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች የሚች ወላጅ አባቴ እና እናቴ ልጅ እና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆኔን በስር የሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት እንዲሁም ከፍተኛው ፍ/ቤት በማስረጃ ተረጋግጦ የተወሰነውን ውሳኔ በማጽናቱ ውሳኔውን መሻር ሲገባው አመልካች የወላጅ እናቴ ልጅ መሆኔን አስመልክቶ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሚች ወላጅ አባቴ ልጅ አለመሆኔን የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት የወሰነውን ውሳኔ ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው። በስር ፍ/ቤት ምስክሮች በሚች አባቴ ስም እንደምጠራ፣ እየተንከባከቡ ያሳደጉኝና በወላጅ እየተጠራሁኝ የተማርኩኝ ከመሆኔም በላይ በህይወት እያሉ ጋብቻ ስመሰርት በሽምግልና ተጠይቆ በወግ ማእረግ የዳረኝ መሆኔን በሚገባ አስረድተዋል። ከዚህም በተጨማሪም አመልካች በወላጅ አባቴ ስም በተመዘገበው እድር በቤተሰብ አባልነት የተመዘገብኩኝ መሆኔ እና በስሙ እንደምጠራ የሰነድ ማስረጃ በማቅረቤ እና ተጠሪው ይህን ማስተባበል ባለመቻሉ አመልካች ያስወሰንኩበት ውሳኔ ሊሻር አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ ከፍተኛው ፍ/ቤት በድጋሚ በሰው ምስክሮች ተረጋግጦ ያጸናውን ውሳኔ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከማስረጃ ምዘና ውጭ በአግባቡ ሳይመለከት አመልካች ያቀረብኳቸው የሰው ምስክር ተአማኒነት የሌለው እና አመልካች በሚች የጡረታ ሰነድ ላይ አልተመዘገበችም

በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና ስህተት የተፈጸመበት ነው። ምክንያቱም አመልካች በስር ፍ/ቤት ባቀረብኳቸው የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች በቤተሰብ ህጉ መሰረት አስረድቼ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በቂና አሳማኝ ምክንት ሳይገልጽ ያጠራጥራል በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ መሻሩ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መ/ቁ 38844 ውሳኔን ያልተከተለ በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ አመልካች የሚች ወላጅ አባቴ ልጅ እና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆኔ ተረጋግጦ የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል እንዲባልልኝ። የስር ክልል ጠ/ፍ/ቤት አመልካች ያቀረብኩት 2ኛ ምስክር የእድሜውን ሁኔታ እና አድራሻ እንደ ምክንያት በመጠቀም እንዲሁም አመልካች በሚች አባቷ ጡረታ ፎርም ላይ አልተመዘገበችም በማለት የሚች ወንድማገኘሁ ልጅ እና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ነች በመባል በስር ፍ/ቤቶች የተወሰነውን ውሳኔ የሻረበት አግባብ እና ሰበር ሰሚ ችሎት ሙሉ ለሙሉ መታረም ሲገባው በከፊል ብቻ መታረሙ ስህተት ነው። በመሆኑም ውሳኔው ተሽሮ አመልካች የሚች አባቴ ልጅ እና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆኔን አስመልክቶ የተሰጠው ውሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል።

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በግራ ቀኙ ከቀረበው ክርክርና ማስረጃ አንጻር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎችን በመሻር ሚች አቶ ወንድማገኘሁ እሸቱ በመንግስት ሰራተኛነት ሲኖሩ በጡረታ ቅጽ ላይ አመልካችን በልጅነት አልሞሉም በማለት አመልካች የሚች ልጅ አይደሉም በማለት የተሰጠው የወራሽነት ማስረጃ ሊሰረዝ ይገባል ሲል ሰበሩም ያጸናበትን አግባብ ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል።

ተጠሪ በቀን 22/07/2014 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በስር ፍ/ቤት የተሰጠውን የወራሽነት ማስረጃ የሻረው ሚች አቶ ወንድማገኘሁ እሸቱ በመንግስት ሰራተኛነት ሲሰሩ በጡረታ ቅጽ ላይ አመልካችን በልጅነት አልሞሉም በሚል ብቻ ሳይሆን በግራ ቀኛችን የቀረቡትን ምስክሮች ቃል በአግባቡ መዝኖና የአመልካች ምስክር ቃልን የማይታመን መሆኑን አትቶና የጡረታ ቅጹንም በሰነድ ማስረጃነት በማየት የአሁን አመልካችም ሆኑ ሌላኛው በስር ፍ/ቤት ተከራካሪ የነበረው አቶ ብዙነህ ወንድማገኘሁ ተወለድን የሚሉት የጡረታ ቅጹ ከተሞላበት ከ1977 ዓ.ም በፊት በመሆኑና በጡረታ ቅጹ ላይ ልጅ ናቸው ተብለው አለመሞላታቸው ከሚች ስለመወለዳቸው ጥርጣሬን የሚፈጥር ስለሆነ ከሚች መወለዳቸው አልተረጋገጠም በማለት ስለመሆኑ ውሳኔው ያሳያል። ተጠሪ የተወለድኩትም የጡረታ ቅጹ ከተሞላ በኋላ በ1980 ዓ.ም በመሆኑ በቅጹ ላይ እንድሞላ አይጠበቅም። የዘመድ ልጆች የሆኑት በሚች አባቴ ቤት ያደጉትና በአባቴ ስም የሚጠሩት የአሁን አመልካችና በስር ፍ/ቤት ተከራካሪ የነበረው አቶ ብዙነህ

ወንድማገኘሁ ተወልደናል የሚሉት የጡረታ ቅጹ ከመሞላቱ በፊት በ1964 ዓ.ም እና 1967 ዓ.ም እንደመሆኑ ሚች አባቴ አቶ ወንድማገኘሁ የወለዳቸው ቢሆኑ ኖሮ በጡረታ ቅጹ ላይ ልጆቼ ብሎ የማያስመዘግብበት አንዳችም ምክንያት የለም። ስለሆነም ውሳኔው ስህተት የለውም። በእናት በኩል ያለውን በተመለከተ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ ሰበሩ የሻረውና የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ያጸናው አመልካች የሚች ወ/ሮ ጥሩነሽ ዋማ ልጅ ነች በሚል ሳይሆን እኔን ተጠሪን የሚች ልጅ ስላልሆንክና እናትህ ሌላ ስለሆነች የወ/ሮ ጥሩነሽ ዋማን የወራሽነት ማስረጃ ለማሻር የህግ መብት የለህም በማለት ነው። የህግ ስህተት ፈጽሟል ከተባለም በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ መሰረት በእናት በኩል ያለ ተወላጅነት በማናቸውም ባለጉዳይ በማንኛውም ግዜ ሁሉ ክርክር ሊቀርብበት የሚችል ስለመሆኑ የተደነገገ በመሆኑ የወ/ሮ ጥሩነሽ ዋማን የወራሽነት ማስረጃ ለማሻር የሚከለክለኝ ህግ ሳይኖር መብት የለህም ማለቱ ነው፤በዚህ ጉዳይ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ አቤቱታ ባቀርብም ውድቅ የተደረገ በመሆኑ የአመልካች ቅሬታ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል። አመልካችም በመልስ መልሳቸው አቤቱታቸውን በማጠናከር አቅርበዋል።

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል።

እንደሚታወቀው የበላይ ፍርድ ቤቶች በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎችን ለመሻር እንደሚችሉ በህጉ ስልጣን የተሰጣቸው ቢሆንም ይኸው የመሻር ስልጣን በህጉ አግባብ እና በምክንያት ተደግፎ ሊፈፀም ይገባል። የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 182 እና 348 እንዲሁም ተያያዥ ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡትም ይህንኑ ነው።

በተያዘው ጉዳይ የወረዳው ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃዎች አስቀርበው ሰምተው በሰጡት ውሳኔ የአሁን አመልካች (የስር ተከሳሾች) የሚች ልጅ መሆናቸው እና ከሚች መወለዳቸውን በቀረቡት ምስክሮች በአግባቡ መረጋገጡን፤ የሰነድ ማስረጃውም ይህንኑ የሚያጠናክር መሆኑን፤ ግራቀኙ በአንድ ቤት ውስጥ ያደጉ መሆናቸውም መረጋገጡን፤ ከሳሽንም ሆነ ተከሳሾችን አባት (ሚች) ልጆቼ ብሎ በግልፅ የሞላው (የጡረታ ሰነዱን ጨምሮ) የሰነድ ማስረጃ አለመኖሩን፤ የቀረቡት ማስረጃዎች በጠቅላላው ሲመዘኑ ግራቀኙ የሚች ወንድማገኝ እሸቴ ልጆች መሆናቸውን የሚያስገነዝብ እንጂ ተጠሪ ብቻ ልጅ መሆኑን የሚያሳይ አለመሆኑ መረጋገጡን በመጥቀስ የያዙት የወራሽነት ማስረጃ ለማሻር የሚቻልበት ምክንያት ባለመኖሩ በተጠሪ የቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ እንደሚገባ ወስነዋል።

በአንጻሩ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት 1ኛው የአመልካች ምስክር በወቅቱ የ10 ዓመት ልጅ የነበረ መሆኑን እንዲሁም ተከሳሾች የጥሮታ ቅጽ ላይ ያልተሞሉ መሆኑ ከሚች መወለዳቸው ጥርጣሬ የሚፈጥር ነው

በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉትን ውሳኔ ሽሯል። ይሁንና አመልካች በሚች ቤት ተወልደው በሚች ስም እና እንክብካቤ ያደጉ መሆኑ በተረጋገጠበትና ይህን የሚያስተባብል ማስረጃ በተጠሪ በኩል አለመቅረቡ በስር ፍርድ ቤቶች በተረጋገጠበት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቂ የሚባል ምክንያት ሳይኖረው የአንዱን ምስክር እድሜ እና ለጉዳዩ አወሳሰን የጎላ ቦታ ሊሰጠው የማይገባውን የጥሮታ ቅጽ በምክንያትነት በመጥቀስ ውሳኔውን መሻሩ ምክንያታዊ ሆኖ አላገኘነውም። ህጉንም የተከተለ አይደለም። የክልሉ ሰበር ችሎትም ውሳኔውን ሙሉ በሙሉ ሊሽረው ሲገባ ማሻሻሉ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም።

ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ያሳለፉት ውሣኔ የሚነቀፍ ነው ብለናል። ተከታዩንም ወስነናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 374773 በቀን 19/09/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል።

2. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 325898 በቀን 10/06/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል።

3. የሻሸመኔ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 54989 በቀን 17/02/2012 ዓ.ም እና የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 40824 በቀን 04/03/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል።

4. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም